# የኢትዮጵያ
# ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)

## በኢትዮጵያ የሰሜኑ ክፍል ያለውን የትጥቅ ግጭት ተከትሎ በአማራ እና በአፋር ክልሎች ውስጥ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች

(ከታሕሳስ 08 ቀን 2014 ዓ.ም - የካቲት 01 ቀን 2014 ዓ.ም የተሰራ የምርመራ ስራ)

## 151ኛ ልዩ መግለጫ

ነሐሴ 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

## ማውጫ


በትጥቅ ግጭቱ የተካለሉ ክልሎች በኢትዮጵያ ካርታ 3

1. መግቢያ 5

1.1. የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ 5

1.2. የልዩ ዘገባው ወሰን 5

1.3. የልዩ ዘገባው ዓላማ 6

1.4. የምርመራ ሥራው ስነ-ዘዴ 6

1.5. የምርመራ ሥራው ውስንነቶች እና ያጋጠሙ ችግሮች 7

2. መነሻ ታሪክ 8

2.1. ሐገራዊ እና ክልላዊ አውድ 8

2.2. የግጭቱ አጀማመር እና ምንነት 9

2. የምርመራ ሥራው ዋና ዋና ግኝቶች 12

ግድያ እና የአካል ጉዳት 13

አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 15

አፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 39

ጾታዊ ጥቃት 47

አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 48

ንብረት ውድመት 52

የጭካኔ፣ ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ እና ቅጣት 57

የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች 58

እገታ ወይም የአፈና ተግባር 61

አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 62

በሸኔ ታጣቂ ቡድን የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች 62

የህግ ትንታኔ 63

መደምደሚያ 68

ምክረ ሐሳብ 69

## የኢትዮጵያ ካርታ



**ዋና ጽ/ቤት፡ አዲስአበባ**

**አ.አ ስታዲየም አጠገብ፣ላሊበላ ሬስቶራንት ጎን፣ ሣኅለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ፣ቢሮ ቁጥር 19**

**ኢ-ሜይል:[info@ehrco.org](mailto:info@ehrco.org)**

**ድረገጽ: www.ehrco.org**

**ፌስቡክ፡[https://www.facebook.com/ehrco1/](https://www.facebook.com/ehrco1/)**

**ትዊተር፡ [https://www.twitter.com/ehrcoethio](https://www.twitter.com/ehrcoethio)**

**ቴሌግራም፡ https://t.me/ehrco**

**የፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432**

**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

**የሰብዓዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ መምሪያ፡ አዲስ አበባ**

**ስልክ: (+251) 011 558-2387**

**ኢሜይል:info@ehrco.org**

**ቀጠና / ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች**

**ደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ሐዋሳ - ስ.ቁ (+251) 046 220-4500፣ ፖ.ሳ.ቁ 360**

**ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና፡ባሕርዳር- ስ.ቁ (+251) 058 220-0240፣ ፖ.ሳ.ቁ 1115**

**ጎንደር-ስ.ቁ (+251) 058 2 11 39 06)**

**ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ነቀምቴ - ስ.ቁ (+251) 057 660-2664፣ ፖ.ሳ.ቁ 463**

**ጋምቤላ- ስ.ቁ**

**ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ድሬደዋ - ስ.ቁ (+251) 025 411 6845፣ ፖ.ሳ.ቁ 2596**

**ጂግጂጋ- ስ.ቁ (+251) 025 2 78 42 40**

**ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና፡አዲስ አበባ- ስ.ቁ (+251)011 551-7704፣ ፖ.ሳ.ቁ 2432**

## 1. መግቢያ

### 1.1. የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ

**የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ - ኢሰመጉ** በበጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሠረት ሐገር በቀል ድርጅት ሆኖ በ 1984 ዓ.ም የተመሠረተና በምዝገባ ቁጥር 1146 ከ 02/11/11 ዓ.ም ጀምሮ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ ዳግም ተመዝግቦ በሕጋዊነት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅት ነው:: ኢሰመጉ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ሲሆን፣ ዓላማውም በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የበኩሉን አስተዋጽዖ ማድረግ ነው:: ኢሰመጉ የተቋቋመበት ዋነኛ ዓላማው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የጎለበተባት፣ የሕግ የበላይነት የሰፈነባት እና ሰብዓዊ መብቶች የሚከበሩባት ኢትዮጵያን ማየት ነው:: በሥራውም ከማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የኃይማኖት ተቋም፣ የብሔረሰብ ቡድን፣ ማኅበራዊ መደብ ወዘተ የማይወግን፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ነው። ኢሰመጉ ላለፉት 30 ዓመታት በቆመላቸው ዐበይት ዓላማዎች ላይ በመመርኮዝ ሁለንተናዊ፣ ሐገራዊና ሕዝባዊ ተልዕኮ በመያዝ በነደፋቸው በርካታ የመርሐ -ግብር ተግባራት አማካኝነት ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የሕግ የበላይነትና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲሰፍንና በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲኖር የበኩሉን አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ ይገኛል።

የኢሰመጉ ዋነኛ ተግባሩ የኢትዮጵያን የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝና ሁኔታ መከታተል፣ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በማጣራትና በመተንተን በማስረጃ የተደገፉ መግለጫዎችን ማውጣት ነው። ኢሰመጉ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ሁሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ የጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁና ወንጀል ሠርቶ በነጻ የመኖር ልማድ እንዲያበቃ፣ ከእያንዳንዱ ክስተት ትምህርት ተወስዶ ለወደፊቱ ጥንቃቄና ተገቢው የፖሊሲና የአፈጻጸም እርማት እንዲደረግ ሲወተውትና ሲጠይቅ ቆይቷል፣ አሁንም በመጠየቅ ላይ ነው፤ ለወደፊትም በዚሁይቀጥላል። ከኢሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ክትትል ተግባራት መካከል፣ የሕግ ታራሚዎችን መጎብኘትና ሰብዓዊ መብቶቻቸው መጠበቃቸውን መከታተል፣ የፍርድ ቤቶችን ሒደት ፍትሐዊነት መከታተል እንዲሁም በመንግሥት የወጡና የሚወጡ ሕጎችን ይዘትና አፈጻጸማቸውን ከሰብዓዊ መብቶች አንጻር መመርመር ይገኙበታል። ከእነዚህ በተጓዳኝ ኢሰመጉ በተለይ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሰለባ ለሆኑ ሰዎች የተለያየ ደረጃና መልክ ያለው የሕግ ድጋፍ ይሰጣል።

በእስካሁኑ ቆይታው ኢሰመጉ 39 መደበኛ መግለጫዎችና 151 ልዩ መግለጫዎችን በተጨማሪም በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በርካታ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይፋ አድርጓል። ኢሰመጉ አሁን በሚገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ቢሆን፣ ሁኔታና ዐቅም በፈቀደለት መጠን የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕግ የበላይነት እና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የጸና ዓላማ አኳያ በመሥራት ላይ ይገኛል።

### 1.2. የልዩ ዘገባው ወሰን

ይህ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ዘገባ ቀዳሚ ትኩረቱ ከጥቅምት 23 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በትግራይ ሀይሎች እና በመንግስት ጸጥታ ሀይሎች መካከል የጀመረውን የትጥቅ ግጭት ተከትሎ ጦርነቱ ባዳረሳቸው የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ የተፈጸሙ በርካታ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን መለየት ነው::

በዚህ የትጥቅ ግጭት መጠነ ሰፊ የሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የተፈጸሙ ሲሆን ግጭቱ የሰሜኑን የኢትዮጵያ ክፍል ያካለለ በመሆኑ እና በርካታ ቦታዎች በዚህ ግጭት የተሸፈኑ በመሆናቸው ይህ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ዘገባ በዋናነት የኢሰመጉ የመስክ

ምርመራ አቅም እና የጸጥታ ሁኔታ በፈቀደ መጠን ቡድኑ ባካለላቸው አካባቢዎች ብቻ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ብቻ ያካትታል፡፡

## 1.3. የልዩ ዘገባው ዓላማ

የዚህ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ዘገባ ዐብይ ዓላማ **ከጥቅምት 23 ቀን 2013** ዓ.ም በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የጀመረውን የትጥቅ ግጭት ተከትሎ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በበቂ ማስረጃ አስደግፎ ማቅረብ ነው፡፡ ይህ ልዩ ዘገባ የትጥቅ ግጭቱን ተከትሎ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን አይነትና ምንነት፣ እነዚህ ጥሰቶች በማን፣ መቼ፣ እንዴት፣ የት እና በእነማን ላይ ተፈጸሙ የሚለውን በማስረጃ በማስደገፍ ከበቂ የህግ ትንታኔ ጋር የሚያቀርብ ይሆናል፡፡

ከዚህም በመነሳት የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ይፋ በማውጣት ተጎጂዎች ፍትሕ እንዲያገኙ፣ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ተገቢውን የሞራል እና የገንዘብ ካሳ እንዲያገኙ፣ በግጭቱ ምክንያት በደረሰባቸው ጉዳት ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ውስጥ የገቡ ዜጎች ድጋፍ እንዲያገኙ፣ በግጭቱ ምክንያት በተለያዩ  የሀገሪቱ ክፍል ውስጥ ተፈናቅለው የሚገኙ ሰዎች ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሊደረግ የሚገባውን ሁለገብ ድጋፍ እንዲያገኙ፣ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች (ሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አዛውንቶች እና ሌሎችም) ተገቢው ትኩረት እንዲሰጣቸው፣ በግጭቱ ተሳታፊ የሆኑ አካላት የዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግን (International humanitarian law ወይንም በተለምዶ የጦርነት ህግ በመባል የሚታወቀውን ህግ) እንዲያከብሩ እና በምንም አይነት ሁኔታ ከዚህ ህግ ውጪ በመሆን በዚህ ህግ ጥበቃ የሚደረግላቸውን አካላት ከማጥቃት እንዲቆጠቡ እና በሁለቱም የግጭቱ ተሳታፊዎች ጥፋት የፈጸሙ አካላት ተገቢ የሆነ ህጋዊ ቅጣት እንዲቀጡ መጠየቅ እና መወትወትን አላማው አድርጎ የተዘጋጀ ልዩ ዘገባ ነው፡፡

በመሆኑም፤ ኢሰመጉ የዚህን ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ዘገባ ይዘትና ዓላማ በተፃረረ መልኩ፣ ከሕግና ከመልካም አስተሳሰብ ውጪ በሆነ መንገድ ማንም እንዲጠቀምበት አይፈቅድም። ይህንንም ዘገባ የሐገር ሰላምን ለማደፍረስ፣ ግለሰቦችንም ሆነ ቡድኖችን ለማጥቃት፣ ከሕግ አግባብ ውጪ ሌሎች ሲጠቀሙበት ቢገኝ ኢሰመጉ ከወዲሁ አጥብቆ ያወግዛል፣ ኃላፊነቱንም እንደማይወስድ ያሳስባል።

## 1.4. የምርመራ ሥራው ስነ-ዘዴ

ይህ ልዩ ዘገባ የተዘጋጀው ኢሰመጉ የሰብዓዊ መብት የምርመራ ባለሙያዎች ባደረጉት ቃለመጠይቆች (ከተጎጂዎች፣ ምስክሮች፣ የመንግስት እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አመራሮች፣ እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ያካትታል)፣ የቡድን ውይይቶች፣ የመስክ ምልከታ ስራዎች፣ የመንግስት እንዲሁም መንግስታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ውይይቶች እና ከእነዚህ አካላት የተገኙ አስረጂ ሰነዶችን በመጠቀም መረጃዎችን ኢሰመጉ አሰባስቧል፡፡

የምርመራ ቡድኑ በተጠቀሱት አካባቢዎች ተዘዋውሮ የሟች ቤተሰቦችን፣ በጥቃቱ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን፣ የዓይን ምስክሮችን፣ የቀብር ስርዓቶችን ያከናወኑ ሰዎችንና የቤተ-ክርስትያን አባቶችን፣ በጊዜያዊነት የተቋቋሙ የመንግሥት ተቋማት የሥራ ኃላፊዎችንና ሌሎችም የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሞ ልዩ ልዩ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን አሰባስቧል፡፡

ከእነዚህ በተጨማሪ የምርመራ ቡድኑ በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ እና ከቤተ-ክርስቲያን ቅጥር ውጪ የሚገኙ የጅምላ እንዲሁም የግለሰብ መቃብሮችን፣ በግጭቱ ምክንያት የወደሙ የመንግስት ቢሮዎችን፣ የግለሰቦች የንግድ ቦታዎች፣ በዚህ ግጭት ምክንያት የወደሙ እና የተዘረፉ ሆስፒታሎችን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ ባንኮችን፣ የቴሌኮም እና የትራንስፖርት መሰረተ ልማቶችን፣ የጤና ጣቢያዎችን፣ የሀይማኖት ተቋማትን፣ የፖሊስ ጣቢያዎችን፣ የተፈናቃይ መጠለያ ጣቢዎችን እና ሌሎች ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ቦታዎች ተዘዋውሮ በመጎብኘት መረጃዎችን ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡

## 1.5. *የምርመራ ሥራው ውስንነቶች እና ያጋጠሙ ችግሮች*

የዚህ ዘገባ የምርመራ ሥራ በሚከናወንበት ወቅት ኢሰመጉ የሚከተሉት ዋና ዋና ውስንነቶች እና ተግዳሮቶች አጋጥመውታል፡-

- የትጥቅ ግጭቱ በሸፈናቸው የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ በዚህ ልዩ ዘገባ ውስጥ ያልተካተቱ ነገር ግን ለማካተት በእቅድ ውስጥ የነበሩ ቦታዎች ከነበረው የጸጥታ እና የደህንነት ችግር አንጻር (ቦታዎቹ በሰአቱ የጦር ቀጠና የነበሩ በመሆናቸው) በነጻነት ተዘዋውሮ ምርመራዎችን ለመስራት አልተቻለም፡፡
- የትጥቅ ግጭቱን ተከትሎ የደረሱ ወሲባዊ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በርካታ ቢሆኑም ምርመራ ስራው በሸፈናቸው የተወሰኑ ቦታዎች ጥቃቱ የደረሰባቸው ሰዎች መረጃውን ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው (የጥቃቱ ሰለባዎች መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆናቸው ምክንያት በሰጡት መረጃ መነሻነት ሊደርስባቸው የሚችለውን ማህበራዊ ጫና ማለትም መገለልን በመፍራት ነበር) ከደረሰው ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አንጻር በዚህ ልዩ ዘገባ ላይ የተካተተው አነስተኛ ቁጥር መሆኑን እና ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ቁጥር እዚህ ልዩ ዘገባ ላይ ከተካተተው ቁጥር ሊያልፍ እንደሚችል ኢሰመጉ ያምናል፡፡
- ኢሰመጉ ያለበት የገንዘብ፣ የሰው ኃይል፣ ለምርመራ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች እጥረት፤
- በወቅቱ የምርመራ ስራ በተሰራባቸው አካባቢዎች በነበረው የጸጥታ ስጋት የተነሳ ከፍተኛ የሆነ የትራንስፖርት እጥረት በመኖሩ የኢሰመጉ መርማሪዎች እንደልብ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ እና ተጎጂዎችን እና የተጎጂ ቤተሰቦችን ለማናገር መቸገር፤
- በምርመራ ሥራው በተሸፈኑት አካባቢዎች የተፈጸመው የሰብዓዊ መብት ጥሰትና የደረሰው ሰብዓዊ ቀውስ ከኢሰመጉ የማጣራት አቅም በላይ መሆኑ፤
- በወቅቱ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን አስመልክቶ ያላቸውን መረጃ እንዲሰጡ የተጠየቁ በየደረጃው ያሉ የህክምና፣ የኃይማኖት እና በየደረጃው ያሉ የመንግስት ተቋማት ንብረታቸው ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የወደመ በመሆኑ መረጃና ማስረጃዎችን ለማግኘት መቸገር፣
- በመጨረሻም አንዳንድ የመንግስት አመራሮች፣ እና የመንግስት ቢሮዎች ያሏቸውን መረጃዎች ለማጋራት ፈቃደኛ አለመሆን ይገኙበታል፡፡
- ኢሰመጉ የትጥቅ ግጭቱን ተከትሎ በትግራይ ክልል በሚገኙ አካባቢዎች በሁሉም የትጥቅ ግጭቱ ተሳታፊ አካላት የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመመርመር እንዳይችል ከኢሰመጉ አቅም በላይ የሆኑ ተግዳሮቶች አጋጥመውታል ከእነረሱም መካከል የትጥቅ ግጭቱ ከጀመረበት ወቅት አንስቶ ክልሉ የጦር ቀጠና መሆኑ፣ ወደ ትግራይ ክልል ለመግባትም ሆነ ለመውጣት የትራንስፖርት አገልግሎቶች መቋረጥ፣ የስልክ፣ የኢንተርኔት እና የመገናኛ አውታሮች መቋረጥ እና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡

- ኢሰመጉ ከላይ ከተጠቀሱት በትግራይ ክልል የምርመራ ስራ እንዳይከናወን ካደረጉ ተግዳሮቶች በተጨማሪ በመንግስት በኩል የነበረው ለመተባበር ፈቃደኛ አለመሆን የኢሰመጉን የምርመራ ስራ ገድቦታል፡፡ ለዚህም ማሳያነት ኢሰመጉ ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ መከላከያ ሚኒስቴር እና ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሰላም ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር ER3-M41/07/21 በቀን 12/07/2013 ዓ.ም የትጥቅ ግጭቱን ተከትሎ በትግራይ ክልል የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመመርመር የትብብር ደብዳቤን እንዲሁም ወደ አካባቢው ለመግባት እና ምርመራ ስራን ለማከናወን ፈቃድ የጠየቀ ቢሆንም ሁለቱም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ምንም አይነት ምላሽ አልሰጡም፡፡ በተጨማሪም ኢሰመጉ በድጋሚ ለሰላም ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር ER3-230/16/21 በቀን 14/8/2013 ዓ.ም የድጋፍ ደብደቤ እንዲሰጠው እና በትግራይ ክልል የትጥቅ ግጭቱን ተከትሎ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን እንዲመረምር የጠየቀ ቢሆንም በድጋሚ የሰላም ሚኒስቴር ለኢሰመጉ ምንም አይነት ምላሽ አልሰጠም፡፡
- በትግራይ ክልል  ጊዜያዊ አስተዳደር በተቋቋመበት ወቅት ኢሰመጉ ወደ ክልሉ በመግባት የትጥቅ ግጭቱን ተከትሎ የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለመመርመር ጥረት ያደረገ ቢሆንም የጊዜያዊ አስተዳደሩ ተባባሪ ባለመሆኑ ምክንያት ኢሰመጉ ወደ ክልሉ በመግባት የምርመራ ስራን ለማከናወን አልቻለም፡፡
- ይህ ልዩ መግለጫ ለህዝብ ይፋ የሆነበት ቀን የተራዘመው በዋናነት ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት መረጃን የማሰባሰቡ ሂደት ሰፊ ጊዜን መውሰዱ፣ ከተጎጂዎች የተገኙ መረጃዎችን ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጋር ከተሰበሰቡ መረጃዎች ጋር ለማመዛዘን ሰፋ ያለ ጊዜን መውሰዱ እና በዘርፉ እውቀት ካላቸው ግለሰቦች እና አካላት በመግለጫው ዙሪያ የሙያ አስተያየታቸውን ለመቀበል ሰፋ ያለ ጊዜ መውሰዱ በዋናነት የጠቀሳሉ፡፡

በመሆኑም በዚህ ልዩ ዘገባ ውስጥ የተሸፈኑት የአማራ እና የአፋር ክልሎች እንዲሁም በሸኔ ታጣቂ ቡድን በአንዳንድ የኦሮሚያ ክልሎች የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ሲሆኑ በምንም አይነት ሁኔታ ኢሰመጉ በትግራይ ክልል የደረሱትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ቸል በማለት ሳያካትት እንዳልቀረ እና በኢሰመጉ አቅም ልክ በክልሉ (በትግራይ) የደረሱትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ለመመርመር ከፍተኛ ጥረት ቢየደርግም በጊዜው የነበረው የአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ይህንን ሊያደርግ አላስቻለውም፡፡

## 2. መነሻ ታሪክ

### 2.1. ሐገራዊ እና ክልላዊ አውድ[1]

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ወደ ስልጣን ከመጡ ከመጋቢት 2010 ዓ.ም አንስቶ መንግስት በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ለማሻሻል ጥሩ የሚባሉ ለውጦችን ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ነገር ግን በሀገሪቱ በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ በርካታ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተፈጽመዋል፡፡ ለዚህም በዋናነት እንደ ምክንያት ተደርጎ ሊነሳ የሚችለው በሀገሪቷ ውስጥ የነበረው የፖለቲካ አለመረጋጋት እና ቀውስ ነው፡፡ በፖለቲካ ልዩነቶች መካረር እና የብሔር ጽንፈኝነት የእርስ በእርስ ግጭቶች፣ ማንነትን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች እና እጅግ የከፉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንዲፈጸሙ ምክንያት ሆኗል፡፡

[1] በዚህ ርዕስ ስር የተካተቱት አብዛኛዎቹ ጉዳዮች ኢሰመጉ ቀደም ሲል ጥቅምት 27 ቀን 2013 ዓ.ም ይፋ ባደረገው 147ኛው ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ዘገባ እና ታህሳስ 2014 ዓ.ም ይፋ ባደረገው ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ዘገባ ላይ ያካተተ በመሆኑ እንዲመለከቱት ይጋብዛል፡፡

በዚህም ምክንያት የሰዎች ሕይወት ጠፍቷል፣ የአካል ጉዳትና የንብረት ውድመት ደርሷል፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ደግሞ ከመኖሪያ ቤታቸው ተፈናቅለው ለብዙ መከራና ስቃይ ተዳርገዋል፡፡

በእነዚህ አመታት ውስጥ ከተፈጠሩ የፖለቲካ መካረሮች መካከል በፌደራል መንግስት እና በትግራይ ክልላዊ መንግስት አስተዳደር መካከል የነበረው በዋናነት የሚጠቀስ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ከሁለቱም አቅጣጫ በተደጋጋሚ ጊዜ ሀይለ ቃልን የያዙ የቃላት ልውውጦች ተደርገዋል፡፡ ይህ በነበረበት ሁኔታ ሀገሪቷን ሲመራ የነበረውን የኢሕአዴግ አደረጃጀትን በማፍረስ በብልጽግና ፓርቲ መተካት በሁለቱ አካላት መካከል ያለውን መቃቃር አባበብሶታል፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነሀሴ 2012 ዓ.ም ሊደረግ የነበረው ሀገራዊ ምርጫ በጊዜው ተከስቶ በነበረው የኮሮና ቫይረስ ወረርሺኝ ምክንያት በኢፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት እና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ መሰረት ተራዘመ፡፡ የምርጫውን መራዘም ተከትሎ፤ የትግራይ ክልል አስተዳደር ምርጫ ለማድረግ በማሰብ የሕግ ማሻሻያን ጨምሮ የምርጫ አስፈጻሚ ተቋም ማቋቋምን የመሳሰሉ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡ በፌዴሬሽንና ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ መሰረት የተላለፈውን ምርጫ በመቃወም ጳጉሜ 4 ቀን 2012 ዓ.ም የትግራይ ክልል ምክር ቤት በትግራይ ክልል ምርጫን አከናውኗል፡፡ በዚህም ምርጫ መሰረት ህወኃት በሙሉ ድምጽ አሸናፊ መሆኑን ገልጿል፡፡

የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በበኩሉ ነሃሴ 30 ቀን 2012 ዓ.ም *‹‹…የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት፣ አስፈጻሚ አካላት እና ምርጫ ኮሚሽን ምርጫን በሚመለከት ያወጣው አዋጅ፣ ያሳለፏቸው ውሳኔዎች እና የፈጸሟቸው ተግባራት ከሕገ-መንግሥቱ ጋር የሚቃረኑ በመሆናቸው እንዳልተደረጉ የሚቆጠሩ፣ የማይጸኑ እና ተፈጻሚነት የሌላቸው ናቸው…››*[2] የሚል ውሳኔ አሳልፏል፡፡

መስከረም 26 ቀን 2013 ዓ.ም ህወኃት የፌደራል መንግስቱን ህጋዊነት እንደማይቀበለው አሳውቋል፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የቀረበው የፌደራል መንግስቱ የአስተዳደር ዘመኑን ማጠናቀቁ እንደሆነ ለዚህም ምክንያት የፌዴራል መንግስት ምርጫ ከተራዘመበት ጊዜ አንስቶ ምንም ህጋዊ የሆነ ስልጣን እንደሌለው ህወኃት በመግለጫው አሳውቋል፡፡

## 2.2. የግጭቱ አጀማመር እና ምንነት[3]

ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች በፌደራል መንግስት እና በትግራይ ክልል መንግስት መካከል ያለውን ግንኙነት ቢያሻክሩትም ለትጥቅ ግጭቱ ዋነኛ መነሻ ምክንያት የነበረው **በጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም** በትግራይ ልዩ ሀይል እና ሚሊሻ በሰሜን ዕዝ ላይ የተፈጸመው ጥቃት ነበር፡፡ ይህንን ጥቃት ተከትሎ የትግራይ ልዩ ሀይል እና ሚሊሻ የሰሜን ዕዝ ማዘዣን እና በውስጡ የነበሩትን አጠቃላይ ንብረቶች ተቆጣጥሮ እንደነበር በፌደራል መንግስት ተገልጿል፡፡

በትግራይ ልዩ ሀይል እና ሚሊሻ በሰሜን ዕዝ ላይ የደረሰውን ጥቃት ተከትሎ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ/ር አብይ አህመድ “ህግ የማስከበር እርምጃ” በሚል **በጥቅምት 25 ቀን 2013** ዓ.ም በትግራይ ልዩ ሀይል፣ ሚሊሻ እና በአጠቃላይ በህወሀት ላይ

---

[2] https://www.facebook.com/295306200661064/posts/1558552834336388/

[3] በዚህ ርዕስ ስር የተካተቱት አብዛኛዎቹ ጉዳዮች ኢሰመጉ ቀደም ሲል ታህሳስ 2014 ዓ.ም ይፋ ባደረገው 149ኛ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ዘገባ ላይ ያካተተ በመሆኑ እንዲመለከቱት ይጋብዛል፡፡

ወታደራዊ የማጥቃት እንቅስቃሴ እንዲጀመር ትእዛዝ አስተላልፏዋል፡፡ ይህንን ጥሪ እና ትእዛዝ ተከትሎ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት፣ የአማራ ልዩ ሀይል እና ሚሊሻ (በመቀጠልም የተለያዩ ክልሎች ሚሊሻ እና ልዩ ሀይሎች) በአንድነት በመሆን በትግራይ ልዩ ሀይል እና ሚሊሻ ላይ የማጥቃት እንቅስቃሴ አድርገዋል፡፡

የሰሜን ኢትዮጵያ የትጥግ ግጭት አጀማመሩ ከላይ በተገለጸው መልኩ በፌደራል መንግስት እና በትግራይ ክልል አስተዳደር መካከል ቢሆንም ግጭቱ አድማሱን እያሰፋ የአማራ ክልልን እና የአፋር ክልልን አዳርሷል፡፡ በዚህ ትጥቅ ግጭት ውስጥ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት፣ የአማራ ልዩ ሀይል እና ሚሊሻ (ፋኖ እየተባለ የሚጠራውንም አደረጃጀት ጨምሮ)፣ የአፋር ልዩ ሀይል፣ የክልሎች ልዩ ሀይሎች፣ የትግራይ ልዩ ሀይል እና ሚሊሻ፣ እና የኦነግ ሸኔ ታጣቂ ቡድን በየጊዜው ተሳትፈውበታል፡፡

**<u>የግጭቱ ምንነት</u>** [4]

የግጭቱን ምንነት ለመወሰን በትጥቅ ግጭት ወቅት ተግባራዊ የሚሆነውን የዓለም አቀፉ የሰብዓዊነት ሕግን (International Humanitarian law) መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህ ህግ በትጥቅ ግጭቶች ውስጥ የተሳተፉ ሰዎችን እና የሲቪል ሰዎችን ዕጣ ፈንታ የሚቆጣጠሩ ዓለም አቀፍ ሕጎችን ይይዛል፡፡ ይህ ህግ በሰብዓዊነት ምክንያቶች የትጥቅ ግጭት ውጤቶችን ለመገደብ የሚሹ ህጎች ስብስብ ነው። በጦርነቱ ውስጥ የማይሳተፉ ወይም መሳተፍ ያቆሙ ሰዎችን ለመከላከል እና የጦርነት ዘዴዎችን እና መንገዶችን ለመገደብ ተግባራዊ ይደረጋል። ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ የጦርነት ህግ ወይም የትጥቅ ግጭት ህግ በመባልም ይታወቃል።

በቀድሞ ዩጎዝላቪያ የተፈጸሙ የጦር ወንጀለኞችን ለመዳኘት የተቋቋመው ጊዜያዊ ችሎት (ICTY) "የትጥቅ ግጭት ሁለት ሀገራት የታጠቁ ሃይሎቻቸውን በግጭት ወቅት ሲጠቀሙ ወይንም በአንድ ሀገር ውስጥ የተራዘመ የትጥቅ ግጭት በመንግስት ታጣቂ ሀይሎች እና በተደራጁ የታጠቁ ቡድኖች መካከል ሲኖር ወይም በአንድ ሀገር ውስጥ በተደራጁ የታጠቁ ቡድኖች መካከል የትጥቅ ግጭት ሲኖር የትጥቅ ግጭት አለ" ሲል የተጥቅ ግጭትን አብራርቷል፡፡

በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ (IHL) እና ከላይ በICTY በተሰጠው ትርጉም መሰረት ጦርነት ወይም የትጥቅ ግጭት አለ የሚባለው በሁለት ሉዓላዊ ግዛቶች መካከል የትጥቅ ግጭት ሲፈጠር (አለም አቀፍ የትጥቅ ግጭት ተብሎ የሚጠራው) ወይም በአንድ ሉዓላዊ መንግስት እና በተደራጁ ታጣቂ ቡድኖች መካከል ወይም በሁለት የተደራጁ ታጣቂ ቡድኖች መካከል የተራዘመ የትጥቅ ግጭት ሲኖር (አለም አቀፍ ያልሆነ የትጥቅ ግጭት ተብሎ የሚጠራው) ነው። በዚህም መሰረት የአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ለሁለት አይነት የትጥቅ ግጭቶች እውቅና ሰጥቷል እነሱም አለምአቀፍ የትጥቅ ግጭት እና አለም አቀፍ ያልሆነ የትጥቅ ግጭት ናቸው።

አለም አቀፍ ያልሆኑ የትጥቅ ግጭቶች በተሳታፊዎች ለውጥ እና በተሳትፏቸው መጠን ምክንያት ወደ አለም አቀፍ የትጥቅ ግጭቶች ሊለወጡ ይችላሉ (Internationalization of armed conflict)፡፡ ነገር ግን ዓለም አቀፍ ባልሆነ የትጥቅ ግጭት

---

[4] በዚህ ርዕስ ስር የተካተቱት አብዛኛዎቹ ጉዳዮች ኢሰመጉ ቀደም ሲል ታህሳስ 2014 ዓ.ም ይፋ ባደረገው 149ኛ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ዘገባ ላይ ያካተተ በመሆኑ እንዲመለከቱት ይጋብዛል፡፡

ወቅት የተሳታፊዎች መጨመር ሁል ጊዜ በግጭቱ አይነት ላይ ለውጥ ያመጣል ማለት አይደለም፡፡ አንዳንድ ዓለም አቀፍ ያልሆኑ የትጥቅ ግጭቶች ላይ ምንም እንኳን ሌላ ተሳታፊ ሀገሮች ቢጨመሩበትም እነዚህ አዲስ ግጭቱ ላይ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሀገሮች የሚሳተፉበት መንገድ እና የተሳትፏቸውን መጠን መረዳት የትጥቅ ግጭቱን አይነት ለማወቅ ወሳኝነት አለው፡፡[5]

እ.ኤ.አ. በነሐሴ 12 ቀን 1949 የተፈፀመው የጄኔቫ ስምምነቶች የጋራ አንቀፅ 2 ዓለም አቀፍ የትጥቅ ግጭት ማለት በታወጀ ጦርነት ወይም በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የበላይ ተዋዋይ ወገኖች መካከል ሊቀሰቀሱ በሚችሉ ሌሎች የትጥቅ ግጭት ሁኔታዎች ሙሉ፤ ከሁለቱ በአንዱ እውቅና ባይሰጥም እንኳ፤ የሚደረግ ግጭት እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በዚህ ምክንያት ግጭት እንደ ዓለም አቀፍ የትጥቅ ትግል ተደርጎ እንዲወሰድ የሚጋጩ ወገኖች ቢያንስ ሁለት ሉዓላዊ አገራት እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል። እንዲሁም በተጨማሪ ፕሮቶኮል 1 አንቀጽ 1 (4) ሰዎች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብታቸውን ለማስከበር እንደ የቅኝ አገዛዝ የበላይነትን ፣ የባዕዳንን የጦር ወረራ እና ዘረኛ አገዛዞችን (apartheid) የሚታገሉባቸውን ግጭቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ የታጠቁ ግጭቶች አካል እንደሆኑ ይደነግጋል። እንደነዚህ ያሉት ግጭቶች እንደ ብሔራዊ ነፃ የመውጣት እንቅስቃሴ ጦርነቶች ተደርገው የሚወሰዱ ሲሆን በዓለም አቀፍ የትጥቅ ግጭት ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው ሁሉም የሕግ ጥበቃዎች በአንድ ግዛት ክልል ውስጥ ተወስነው ቢከሰቱም እንኳን ለእነሱም ተፈጻሚ ይሆናሉ። እንዲሁም ዓለም አቀፍ ያልሆኑ የትጥቅ ግጭቶችን አስቀድሞ የጦርነቱ አካል ያልነበረ ሉዐላዊ ሀገር የታጠቁ ተቃዋሚ ቡድኖችን ደግፎ ወደ ግጭቱ ከተቀላቀለ ዓለም አቀፍ ያልሆኑ የትጥቅ ግጭቶች ወደ ዓለም አቀፍ የትጥቅ ግጭትነት እንደሚቀየሩ የዓለም አቀፍ ፍ/ቤቶች ውሳኔ ያሳያል።

በሌላ በኩል ዓለም አቀፍ ያልሆነ የትጥቅ ግጭት የምንለው በጄኔቫ ስምምነቶች የጋራ አንቀጽ 3 መሠረት በአንድ በተወሰነ ክልል ውስጥ በመንግሥት እና በታጠቁ ተቃዋሚ ቡድኖች ወይም በሁለት ተቃዋሚ ኃይሎች መካከል የሚደረግ ግጭት ነው። በተጨማሪም ዓለም አቀፍ ያልሆኑ የትጥቅ ግጭት ተጎጂዎች ደህንነትን ለመጠበቅ የተደነገገው የጄኔቫ ስምምነት ተጨማሪ ፕሮቶኮል II በአንቀጽ 1 ላይ ጄኔቫ ስምምነቶች የጋራ አንቀጽ 3 ላይ ከተቀመጠው በተጨማሪ ዓለማ አቀፋዊ ያልሆነ የትጥቅ ግጭት በአንድ ሀገር መንግስት እና በተቃዋሚ የታጠቁ ቡደኖች ወይም ሌሎች የተደራጁ የታጠቁ ቡድኖች መካከል የሚደረግ የትጥቅ ግጭት ሲሆን በዚህ አንቀጽ ላይ እነዚህ የተደራጁ ታጣቂ ቡድኖች በጥበቃው ስር ብቁ ለመሆን ተጨማሪ መስፈርቶችን ያስቀምጣል፡፡ እነዚህም መስፈርቶች

- የግጭቱ ስፋት ወይም መጠን (Intensity)
- የታጠቁ ቡድኖች አደረጀጀት (Organization) እና
- የክልሉን የተወሰነ ክፍል መቆጣጠር (Territorial control)

የግጭቱ ስፋት ወይም መጠን (Intensity)፡ ይህንን መመዘኛ በምንመለከትበት ወቅት የግጭቱን አጠቃላይ ይዘት መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡ ማለትም ሀገራቶች ያጋጠማቸውን ችግር በመደበኛ የፖሊስ አደረጃጀት መፍታት ተስኗቸው መከላከያ

[5] ታዋቂ የሆኑትን የኒካራጋዋን እና የታዲች ውሳኔዎችን ለመወሰን ጥቅም ላይ የዋሉት መመዘኛዎች ይህንን ሃሳብ በደንን ያብራሩታል፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳን ዓለም አቀፋዊ ባልሆነ የትጥቅ ግጭት ወቅት ሌሎች ሀገሮች ተሳትፎ ቢያደርጉም ማለትም ተስትፏቸው የሀገሪቱን መንግስት ደግፈው የታጠቀ ቡድኖችን ለማጥቃት ከሆነ ወይም ተሳትፏቸው ከላይ የተጠቀሱት ውሳኔዎች ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉትን መመዘኛዎች ካላሟሉ ዓለም አቀፋዊ ያልሆነ የትጥቅ ግጭት ሆነው ይቀጥላሉ፡፡

ሰራዊታቸውን ጥቅም ላይ ማዋል ይጀምራሉ፡፡ በተጨማሪም የግጭቱ የጊዜ ስፋት፣ የጥቃት ድርጊቱ ወይም የወታደራዊ ኦፐሬሽኑ ተደጋጋሚነት፣ ጥቅም ላይ የዋሉ የጦር መሳሪያዎች አይነት፣ የሲቪል ሰዎች መፈናቀል፣ የታጠቁ ቡድኖች አንዳንድ ግዛቶችን መቆጣጠር፣ የተጎጂዎች መጠን እና የመሳሰሉት ነጥቦች የግጭቱን ስፋት (Intensity) ለመረዳት ይረዱናል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች ሁሉም በአንድነት መሟላት ላይኖርባቸው ይችላል፡፡

የታጠቁ ቡድኖች አደረጃጀት (Organization)፡ በትጥቅ ግጭቱ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ አካላት የሆነ ያህል አደረጃጃት ሊኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ በመንግስት ታጣቂ ሀይሎች በኩል ይህ መመዘኛ እንደተሟላ የሚቆጠር (presumed facte) ሲሆን በታጣቂ ቡድኖች በኩል ግን ይህ መመዘኛ ተሟልቷል ለማለት ለምሳሌ አደረጃጀቱ የትእዛዝ ተዋረዱን ማሳየት የሚችል መሆኑ፣ የተለያዩ ክፍሎቹን አቀናጅቶ የተደራጀ ኦፐሬሽኖችን መፈጸም መቻሉ፣ አዳዲስ አባላቶችን ማሰልጠን የሚችል መሆኑ እና የሰብአዊነት ህጎችን ማክበር የሚችል መሆኑ የቡድኑን የተደራጀ መሆን ያሳያል፡፡

የክልሉን የተወሰነ ክፍል መቆጣጠር (Territorial control)፡ ይህ መመዘኛ በጄኔቫ ስምምነት ተጨማሪ ፕሮቶኮል II በአንቀጽ 1 ላይ የተቀመጠ ቢሆንም በጊዜ ሂደት ብዙ ትችቶችን ያስተናገደ እና አሁን ላይ መመዘኛነቱ እየቀረ የመጣ ነው፡፡

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት በዋናነት የመጀመሪያዎቹ ሁለት መመዘኛዎች ከተሟሉ የትጥቅ ግጭቱ አለማቀፋዊ ያልሆነ የትጥቅ ግጭት ይሆናል፡፡ ነገር ግን ከሁለቱ መመዘኛዎች አንዱ ካልተሟላ ግጭቱ የሀገር ውስጥ ውጥረት ወይም ብጥብጥ (Internal disturbance) ይሆናል ማለት ነው፡፡

ከላይ ያሉትን መመዘኛዎች እና ህጎች መሰረት አድርገን በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ላይ እየተካሄደ ያለውን የትጥቅ ግጭት ዓለም አቀፍ ያልሆነ የትጥቅ ግጭት ብለን ልንፈርጀው እንችላለን፡፡ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ላይ እየተካሄደ ያለው ግጭት ከላይ የተቀመጡትን ሁለቱን መመዘኛዎች በሚገባ የሚያሟላ ሆኖ ስላገኘነው ግጭቱ ዓለም አቀፍ ያልሆነ የትጥቅ ግጭት ነው ለማለት እንችላለን፡፡

## 2. የምርመራ ሥራው ዋና ዋና ግኝቶች[6]

እ.ኤ.አ ነሐሴ 12 ቀን 1949 የወጡት የጄኔቫ ስምምነቶች፣ ሁለቱ ተጨማሪ ፕሮቶኮሎች እና በልማድ እና በትግበራ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያገኙ እና በሁሉም ሀገራት እንዲሁም የትጥቅ ግጭት ተሳታፊ ቡድኖች ላይ ገዢ የሚሆኑት የልማድ ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ህጎች (customary IHL rules) በሁለቱም አይነት የትጥቅ ግጭቶች ወቅት  ማለትም ዓለም አቀፋዊ በሆኑ እና ዓለም አቀፋዊ ባልሆኑ የትጥቅ ግጭቶች ወቅት ሊደርሱ የሚችሉ ሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ለመቆጣጠር ጥቅም ላይ የሚውሉ ህጎች ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሰብዓዊ መብቶች ህግጋቶች (ማለትም ዓለም አቀፍ፣ አህጉር አቀፍ እና ሀገር አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህግጋቶች) እና ሌሎች ህጎችም እንደ አግባብነታቸው ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ በዚህም መሰረት ሰብዓዊ መብቶች በሰላም ወቅት ብቻ ሳይሆን  በትጥቅ ግጭትም ወቅት ጥበቃ የሚደረግላቸው መብቶች ናቸው፡፡

[6] በዚህ ልዩ ዘገባ ላይ በማይካድራ የደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች አልተከተቱም፡፡ ምንም እንኳን የማይካድራው ክስተት በትጥቅ ግጭቱ ወቅት የተፈጸመ ቢሆንም ኢሰመጉ ከጉዳዩ ግዝፈት እና ከደረሰው ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብት ጥሰት በመነሳት ለብቻው በ149ኛ ልዩ መግለጫው ላይ በስፋት የዳሰሰው በመሆኑ አንባቢው ይህንን መግለጫ እንዲያነብ ይጋብዛል፡፡

ጥቅምት 24/2013 ዓ/ም የተጀመረውን የትጥቅ ግጭት ተከትሎ በርካታ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ያስከተሉ ድርጊቶች ሲፈጸሙ ቆይተዋል። ኢሰመጉ ይህንን የትጥቅ ግጭት በቅርበት ሲከታተል የቆየ ሲሆን የግጭት ቀጠና በነበሩ አካባቢዎች ከግጭት ነጻ በሚሆኑበት ሰዓት በሁለት ዙር የሰብዓዊ መብቶች የምርመራ ቡድኖቹን በማሰማራት የምርመራ ስራዎችን አከናውኗል፡፡

ኢሰመጉ የምርመራ ስራ ባካሄደባቸው ጦርነቱ ሸፍኗቸው በነበሩ የሰሜን ኢትዮጵያ ክፍሎች ውስጥ በርካታ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መፈጸማቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከነዚህም ጥሰቶች መካከል ግድያ(ሞት)፣ የአካል ጉዳት፣ ጾታዊ ጥቃት(አስገድዶ መድፈር)፣ ንብረት ማውደምና መዝረፍ፣ ኢሰብዓዊ አያያዝ፣ እና እገታ ይገኙበታል፡፡

## ግድያ እና የአካል ጉዳት

ኢሰመጉ የምርመራ ስራዎችን ባከናወነባቸው እና የትጥቅ ግጭቱ ሸፍኗቸው በነበሩ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ውስጥ በሚገኙ በርካታ ስፍራዎች ከፍርድ ውጪ የተፈጸሙ ግድያዎች (Extrajudicial killings) እና በሰቪል ሰዎች ህይወት እና አካል ላይ የተፈጸሙ የመብት ጥሰቶችን በምርመራው አግኝቷል፡፡

ሁሉም ሰው በሕይወት የመኖር ሰብዓዊ መብት አለው፡፡ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3 "እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት" እንዳለው ያረጋግጣል። ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል-ኪዳንም በአንቀጽ 6 (1) እና 9 (1) ላይ ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት በቃል-ኪዳኑ የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም በአንቀጽ 2 (1) እና 2 (2) ይደነግጋል።[7]

የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 4 ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህንነት ሊከበርለትና ሊጠበቅለት እንደሚገባና እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፈግ እንደማይችል ተመላክቷል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 14 "ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው" ሲል ይደነግጋል። በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 15 ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለውና በሕግ ከተደነገገው ውጪ ሕይወቱን ሊያጣ እንደማይችል በግልፅ ደንግጓል፡፡ ኢትዮጵያም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት እነዚህን ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች አጽድቃ እና የሐገሪቱ ሕግ አካል እንዲሆኑ አድርጋለች፡፡ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ደግሞ በሕገ መንግስቱ ምዕራፍ ሦስት ስር የተዘረዘሩት መብቶችና ነጻነቶች ከዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት፣ ስምምነቶች እና ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ሊተረጎሙ እንደሚገባ እውቅና የሰጠች ሐገር እንደመሆኗ፤ ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር፣ የማስከበር እና የማሟላት ግዴታ ተጥሎባታል።[8]

---

[7] የኢሰመጉ 149ኛ ልዩ መግለጫ ገጽ 12

[8] Ibid ገጽ 13

ይህ ልዩ ዘገባ በትጥቅ ግጭት ወቅት የተፈጸሙ ግድያዎችን እና የደረሱ የአካል ጉዳቶችን የሚሸፍን በመሆኑ ከሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች በተጨማሪ (human rights laws) የሰብዓዊነት ህጎችን (humanitarian laws) የሚጠቀም ይሆናል፡፡ ስለሆነም በሰሜን ኢትዮጵያ እይተካሄደ የሚገኘው የትጥቅ ግጭት አለም ዓቀፋዊ ያልሆነ የትጥቅ ግጭት በመሆኑ ለዚህ የትጥቅ ግጭት አይነት ጥቅም ላይ የሚውሉ ህጎች በዚህ የትጥቅ ግጭት ወቅት ይተገበራሉ፡፡

ዓለም አቀፋዊ ይዘት የሌለውን የትጥቅ ግጭት የሚገዛው የአራቱ የጀነቫ ስምምነቶ የጋራ የሆነው አንቀጽ 3 በተዋዋይ ወገኖች (በተዋጊ ወገኖች) ላይ አስገዳጅ የሆነ ድንጋጌን አስቀምጧል፡፡ ይህ አንቀጽ የጦር መሳሪያቸውን ያስቀመጡ የጦር ሀይል አባላትንና በህመም ፣ በመቁሰል፣ በመታሰር ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንያት ከውጊያ ውጪ የሆኑትን ሰዎች ጨምሮ በግጭቱ ተግባር ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ የሌላቸው ሰዎች ህይወትና አካል ላይ የሀይል እርምጃ መፈጸም፣ በተለይም በማንኛውም መልኩ የሚፈጸም ግድያ፣ አካልን መቆራረጥ፣ ጭካኔ የተሞላበት ተግባር መፈጸምና ማሰቃየት በማንኛውም ጊዜና ቦታ የተከለከሉ ናቸው ሲል ይደነግጋል፡፡

ሁለተኛው የጄኔቫ ስምምነቶች ተጨማሪ ፕሮቶኮል በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) ላይ በሰዎች የህይወት፣ የጤንነትና የአካል ወይም የአእምሮ ደሕንነት ላይ የሀይል ድርጊት፣ በተለይም ግድያ እንዲሁም እንደማሰቃየት አካልን ማጉደል ወይም እንደማናቸውም የአካል ቅጣት ያለ የጭካኔ አያያዝ በማናቸውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ የተከለከለና ተከልክሎም የሚቆይ ነው ሲል ይደነግጋል፡፡

አለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤትን ለማቋቋም የወጣው ሰነድ (rome statute) በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (ሐ) ላይ አለማቀፋዊ ይዘት በሌለው የትጥቅ ግጭት ወቅት በትጥቅ ግጭቱ ላይ ተሳትፎ በሌላቸው ሰዎች ላይ የሚፈጸም ግድያ ወይም አካል ጉዳት የጦር ወንጀል መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም የልማድ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ በደንብ ቁጥር 89 ላይ በትጥቅ ግጭት ላይ ተሳትፎ በሌላቸው ሰዎች ላይ ግድያ መፈጸም የተከለከለ ተግባር መሆኑን ይደነግጋል፡፡

ከዓለም አቀፍ ልማዳዊ የትጥቅ ግጭት ህጎች (customary IHL)፣ ከ አራቱ የጀነቫ ስምምነቶች እና ከሁለቱ ተጨማሪ የጄኔቫ ስምምነት ፕሮቶኮሎች በመነሳት በትጥቅ ግጭት ወቅት ተፈጻሚ የሚሆኑ አምስት መርሆችን ማግኘት እንችላለን፡፡ እነዚህ አምስት መርሆች የመለየት መርህ (principle of distiniction)፣ በትጥቅ ግጭት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማድረግ ያቆሙ ሰዎችን ያለማጥቃት መርህ (The principle on the prohibition to attack those *hors de combat)* ፣ ተገቢ ያልሆነ ስቃይን ከማድረስ የመቆጠብ መርህ (The principle on the prohibition to inflict unnecessary suffering)፣ የተመጣጣኝነት መርህ (The principle of proportionality) እና የአስፈላጊነት መርህ (The principle of necessity) ናቸው፡፡ እነዚህ መርሆች ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያገኙ እና ጥቅም ላይ የሚውሉ መርሆች በመሆናቸው ከነዚህ መርሆች በተቃርኖ በሲቪል ሰዎች እና ጥበቃ በሚደረግላቸው ሰዎች ላይ የሚፈጸሙ ግድያዎች የአካል ጉዳቶች ልማዳዊ በሆኑ ዓለም አቀፋዊ የሰብዓዊነት ህጎች (customary IHL) መሰረት የጦር ወንጀለኝነትን ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡[9]

[9] Rule 156 of customary IHL compiled by the ICRC

**<u>የምርመራው ግኝቶች፡</u>**

## አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

### 1. <u>ሰሜን ወሎ እና ደቡብ ጎንደር</u>

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ ከታህሳስ 08/2014 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 15/2014 ዓ.ም ድረስ በሰሜን ወሎ እና ደቡብ ጎንደር አንዳንድ ቦታዎች ላይ የምርመራ ስራዎችን አከናውኗል፡፡ በዚህም መሰረት በደቡብ ጎንደር ከሚገኙ ቦታዎች ጉና በጌምድር እና ላይ ጋይንት ወረዳዎች እንዲሁም በሰሜን ወሎ ዞን መቄት ወረዳ በሚገኙ በደብረዘቢጥ፣ ገረገራ፣ ፍላቂት እና አርቢት በተባሉ ቀበሌዎች በመዘዋወር የምርመራ ስራዎችን አከናውኗል፡፡

በደቡብ ጎንደር ዞን በላይ ጋይንት ወረዳ 36 ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሰላማዊ (civilian) በህወኃት ታጣቂዎች የተገደሉ ሲሆን (ከነዚህም መካከል 3 ሴቶች ይገኙበታል) በተጨማሪም 37 ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች ከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡

> ***"በላይ ጋይንት ወረዳ ነፋስ መውጫ ከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሙላት መንገሻ የግል ድርጅት ሰራተኛ የነበሩ እና በሰራቸው 6 ቤተሰብ አባላትን የሚያስተዳድሩ የነበሩ ሲሆን ነሀሴ 7 ቀን 2013 ዓ.ም ላይ ጋይንት ወረዳ ጎብጎብ በምትባል ቦታ ላይ በህወሀት ታጣቂዎች አንገታቸው ላይ በጥይት ተመተው ህይወታቸው በማለፉ ቤተሰቦቻቸው ሌላ የገቢ ምንጭ ስለሌላቸው ከፍተኛ ችግር ውስጥ ይገኛሉ፡፡"***

በደቡብ ጎንደር ዞን ኢሰመጉ የምርመራ ስራ ባከናወነባቸው በጉና በጌ ምድር ወረዳ ውስጥ 15 ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሰላማዊ (civilian) ሰዎች በህወኃት ታጣቂዎች የተገደሉ ሲሆን (ከነዚህም መካከል 4 ሴቶች ይገኙበታል) በተጨማሪም 19 ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች ከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡

ሰሜን ወሎ ዞን መቄት ወረዳ በህወኃት ታጣቂ ቡድን ቁጥጥር ስር በነበረበት ወቅት ማለትም ከሀምሌ 29/2013 ዓ.ም እስከ ጳጉሜ 05/2013 ዓ.ም ድረስ 105 ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሰላማዊ ሰዎች (civilian) የተገደሉ ሲሆን 141 ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች ከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ በሰሜን ወሎ ዞን መቄት ወረዳ ፍላቂት ከተማ ኢሰመጉ ያናገራቸው የሟች ቤተሰብ አባል ስለ ጉዳዩ ሲያስረዱ

> ***"እናቴ ጳጉሜ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ፍላቂት ከተማ ውስጥ ቤቷ ተቀምጣ በነበረበት እናቴ በጦርነቱ ባልተሳተፈችበት ቤቷ ውስጥ በመድፍ ተመታ ሞታብኛለች፡፡"*** ሲሉ አስረድተዋል፡፡

አብዛኞቹ ከላይ በተጠቀሱት ቦታዎች ውስጥ የደረሱ ጉዳቶች በአካባቢዎቹ በነበረው ውጊያ ምክንያት ከሁለቱም ተዋጊ ወገን ሲተኮሱ በነበሩ ከባድ መሳሪያዎች መሆኑን ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል፡፡ ኢሰመጉ ያነጋገራቸው የሟች ቤተሰብ ስለሞተባቸው ልጅ ለኢሰመጉ ሲያስረዱ

> ***"የ16 አመት ልጄ ጥቅምት 4 ቀን 2014 ዓ.ም መቄት ወረዳ ፍላቂት ከተማ ቤት ውስጥ ተቀምጠን በነበርንበት ከባድ መሳሪያ ቤቴ ላይ አርፎ ልጄ ሆዱ ላይ ተመትቶ ሞቶብኛል::"*** ሲሉ አስረድተዋል

ከሟቾች መካከል አብዛኞቹ የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች በመሆናቸው እና ብዙዎቹ ቤተሰቦች ሌላ የገቢ ምንጭ አልባ በመሆናቸው ችግሩን የከፋ እንዳደረገው ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል፡፡

**ደቡብ ጎንደር ዞን ላይ ጋይንት ወረዳ ነፋስ መውጫ ከተማ በህወኃት ታጣቂ ቡድን የተገደሉ ሰዎች ስም ዝርዝር**

ደቡብ ጎንደር ዞን ላይ ጋይንት ወረዳ የሟቾች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | የሞተው ሰው ስም | ጾታ | እድሜ | የሚኖርበት ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አስርአለቃ ሀብቴ መኩሪያ | ወ | 45 | 02 |
| 2 | አስር አለቃ ደመቀ ቀለሙ | ወ | 47 | 02 |
| 3 | ዘውዱ ንጋቴ | ወ | 56 | 01 |
| 4 | አስር አለቃ ተመስገን ነጋሽ | ወ | 48 | 01 |
| 5 | ሸዋ ጥሩዬ | ወ | 30 | 03 |
| 6 | ሀምሳአለቃ ክንድዬተሰማ | ወ | 49 | 01 |
| 7 | ደሴ ክብረት | ወ | 49 | 03 |
| 8 | አበባው ጀምበሬ | ወ | 56 | 04 |
| 9 | ይታያል ጫኔ | ወ | 48 | 03 |
| 10 | እባቡ አታሌ | ወ | 31 | 03 |
| 11 | ደሴ ጌታሁን | ወ | 27 | 04 |
| 12 | ወራሽ አራጋው | ወ | 32 | 03 |
| 13 | መቶ አለቃ ሞገስ ተፈራ | ወ | 45 | 02 |
| 14 | በለጠ ይማም | ወ | 40 | 04 |
| 15 | ይበልጣል ጋሻው | ወ | 30 | 04 |
| 16 | እሱባለው ዋቢ | ወ | 29 | 01 |
| 17 | ገብሬ ተስፋ | ወ | 32 | 01 |
| 18 | ደምሌ ዘገየ | ወ | 56 | 01 |
| 19 | ሙላት መንገሻ | ወ | 49 | 01 |
| 20 | ይበልጣል ባየ | ወ | 33 | 01 |
| 21 | መምህር መራዊ ጋሻው | ወ | 40 | 02 |
| 22 | ያየሁሰው ጌታሁን | ወ | 34 | 01 |
| 23 | ሞላ ፍላቴ | ወ | 31 | 03 |
| 24 | ሙሉየ አለምነው | ሴ | 50 | 02 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 25 | እንዳልክ ሞላ | ወ | 27 | 02 |
| 26 | አበበች እምሩ | ሴ | 50 | 04 |
| 27 | መሀሪ ስዩም | ወ | 24 | 02 |
| 28 | አይነኩሉ መኮነን | ወ | 25 | 04 |
| 29 | ያሬድ ዘመነ | ወ | 25 | 04 |
| 30 | አዲስ ብርሀኑ | ወ | 21 | 04 |
| 31 | ለገሰ ሲሳይ | ወ | 23 | 04 |
| 32 | ማስተዋል አስፋው | ወ | 25 | 04 |
| 33 | ፀዳሉ ሲሳይ | ሴ | 30 | 02 |
| 34 | ያለለት እንየው | ወ | 20 | 04 |
| 35 | ዋን ጂቢ | ወ | 26 | 01 |
| 36 | አባ ወልዱ | ወ | 71 | 01 |

## 2. ደቡብ ወሎ ዞን

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ በጥር ወር 2014 ዓ.ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደቡብ ወሎ ዞን አምባሳል (ውጫሌ) ፣ ሐይቅ፣ ደሴና ኮምቦልቻ ከተማዎች ላይ በመዘዋወር የምርመራ ስራዎችን አከናውኗል፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች ላይ የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የተፈጸሙ ሲሆን ከእነዚህም ጥሰቶች መካከል ግድያ ይገኝበታል፡፡

ኢሰመጉ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደቡብ ወሎ ዞን አምባሰል (ውጫሌ)፣ ሐይቅ፣ ደሴና ኮምቦልቻ ከተማዎች በመዘዋወር ባሰባሰባቸው መረጃዎች መሰረት በእነዚህ አካባቢዎች ውስጥ በአጠቃላይ **206** በትጥቅ ግጭቱ ቀጥተኛ ተሳትፎ የሌላቸው ንጹሃን ሰዎች መገደላቸውን ለመረዳት ችሏል፡፡ በተጨማሪም በነዚህ አካባቢዎች ውስጥ **344** ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች ከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡

በተመሳሳይ በደቡብ ወሎ ዞን ውስጥ በነበረው የትጥቅ ግጭትም እንዲሁ በከባድ መሳሪያ ጉዳት የደረሰባቸው በርካታ ሰዎች መኖራቸውን ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል፡፡ ለዚህም ማሳያነት ከአንድ ቤተሰብ አራት ሰዎች የሞቱባቸው ግለሰብ ለኢሰመጉ ሲያስረዱ

***"ጥቅምት 7 ቀን 2014 ዓ.ም በደቡብ ወሎ ዞን አምባሰል ወረዳ ጦርነቱን ሲጋት ቤት ውስጥ እንደነበርን ከባድ መሳሪያ ቤቱ ላይ ወድቆ ባለቤቴን ጨምሮ አራት ሰዎች ሞተዋል፡፡"*** ሲሉ አስረድተዋል

በተጨማሪም ኢሰመጉ በአካባቢው ተሰማርቶ ከነበረው የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ባገኘው መረጃ መሰረት ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች በአጠቃላይ **103** በትጥቅ ግጭቱ ተሳትፎ የሌላቸው ንጹሃን ሰዎች መገደላቸውን ለመረዳት ችሏል፡፡

## 3. ሰሜን ሸዋ ዞን

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ በየካቲት ወር 2014 ዓ.ም በአማራ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን በኤፍራታና ግድም ወረዳ፣በአንፆኪያ ገምዛ ወረዳ፣ በሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር እና በአጣዬ ከተማ አስተዳደር በመዘዋወር የምርመራ ስራዎችን አከናውኗል፡፡ የምርመራ ስራው በሸፈናቸው ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች ውስጥ በርካታ ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች ላይ በህወሀት ታጣቂ ቡድን እና በሸኔ ታጣቂ ቡድን ግድያ የተፈጸመ ሲሆን እነዚህንም ጥሰቶች በዝርዝር ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

### 3.1.1. ኤፍራታና ግድም ወረዳ

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር የኤፍራታና ግድም ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት በደብዳቤ ቁጥር ኤ/ግ/ወ/አ/ም/08/2014 በቀን 13/4/2014 ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ መሰረት በወረዳው በነበረው የትጥቅ ግጭት ምክንያት በህወኃት ታጣቂ ቡድን ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ወንድ 156፣ሴት 3 በድምር፡ 159 ሰዎች መገደላቸውን እንዲሁም ወንድ 125፣ሴት 23 በድምር፡ 148 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት መድረሱን ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል፡፡

በአማራ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን በኤፍራታና ግድም ወረዳ በትጥቅ ግጭቱ ወቅት በርካታ ሰዎች **የተገደሉ** ሲሆን ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ሰዎች ስም ዝርዝር ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ. | የተገደለው ሰው ስም | ዕድሜ | ፆታ | የተገደለበት ቀን | የተገደለበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግርማ ታደሰ | 45 | ወ | 29/2/2014 | ማጀቴ |
| 2 | ማንያዘዋል አባተ | 52 | ›› | | ማጀቴ |
| 3 | አስፋ ገበየው | 49 | ›› | 11/03/2014 | ማጀቴ |
| 4 | ሻረው በላየነህ | 65 | ›› | 29/02/2014 | ማጀቴ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ዘውዱ መኮታ | 25 | ›› | 01/03/2014 | ማጀቴ |
| 6 | ጌታሁን ሹሜ | 50 | ›› | 01/03/2014 | ማጀቴ |
| 7 | ደምሰው ጥላዬ | 63 | ›› | 29/02/2014 | ማጀቴ |
| 8 | ደርበው ሙሀመድ | 50 | ›› | 01/03/2014 | ማጀቴ |
| 9 | መርሻ ደሳለኝ | 50 | ›› | 29/02/2014 | ማጀቴ |
| 10 | ዘውዱ ይፍሩ | 20 | ›› | 1/03/2014 | ማጀቴ |
| 11 | ተፈሪ ስመኝ | 50 | ›› | 28/02/2014 | ማጀቴ |
| 12 | ማሚ ይምሩ | 60 | ›› | 5/02/2014 | ማጀቴ |
| 13 | ፀጋዬ ተምትሜ | 45 | ›› | 29/02/2014 | ማጀቴ |
| 14 | ዳምጠው ከበደ | 40 | ›› | 29/02/2014 | ማጀቴ |
| 15 | ማሞ መኩሪያ | 42 | ›› | 30/02/2014 | ማጀቴ |
| 16 | ፉአድ አስማረው | 35 | ›› | 24/03/2014 | ማጀቴ |
| 17 | አበበ ነበር | 55 | ›› | 23/03/2014 | ማጀቴ |
| 18 | አማከለወ ጌትነት | 34 | ›› | 24/03/2014 | ማጀቴ |
| 19 | ግርማ ፀጋው | 23 | ›› | 23/03/2014 | ካራቆሬ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 20 | አያልቅበት ረዳ | 40 | ›› | 07/03/2014 | ካራቆሬ |
| 21 | ኪዳኑ ታደሠ | 35 | ›› | 21/03/2014 | ካራቆሬ |
| 22 | አብርሀም ተስፋዬ | 20 | ጠ | 03/4/2014 | ሠርቆ |
| 23 | ዘውዱ ተስፋዬ | 22 | ›› | 30/02/2014 | ቁልፊ |
| 24 | ፍስሀ ማርዬ | 45 | ›› | - | ካራቆሬ |
| 25 | ሉሌ ስመኝ | 76 | ›› | 17/03/2014 | ቆሮ ወንዝ |
| 26 | ባዱ ሉቤ | 46 | ›› | 17/03/2014 | ቆሮ ወንዝ |
| 27 | በሀይሉ ንጉሴ | 27 | ›› | 23/03/2014 | በርጊቢ |
| 28 | ብርቄ አባቴ | | ›› | 06/03/2014 | ካራቆሬ |
| 29 | ዲያቆን ኤልያስ አለማሁ | 23 | ›› | - | ካራቆሬ |
| 30 | ሻለው ንጉሴ | 25 | ›› | 28/03/2014 | ------ |
| 31 | ብርሃን ንጉሴ | | ›› | 07/03/1014 | ካራቆሬ |

በሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳድር የኤፍራታና ግድም ወረዳ ሴቶች:ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ኤ/ግ/ወ/ሴ/ህ/ወ/ጉ/25/2014 በቀን 13/4/2014ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ መሰረት በወረዳው በነበረው የትጥቅ

ግጭት ምክንያት ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሴት ህጻናት 2፣ወንድ ህጻናት 8 በጠቅላላው 10 ህጻናት ላይ (ሁለት የ2 አመት ሕጻናትን ጨምሮ) እንዲሁም በ 9ሴቶች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡

**የቆሠሉ ህፃናት**

| ተ.ቁ | ስም | ፆታ | እድሜ |
|---|---|---|---|
| 1 | ባርኮት ወንደሰን | ወ | 2 |
| 2 | ናሆም ከበደ ተክሌ | ወ | 10 |
| 3 | ዮሃንስ አለኔ | ወ | 6 |
| 4 | ያብስራ አረጌ | ሴ | 16 |
| 5 | በረከት ሲመኝ | ወ | 10 |
| 6 | ኤርሚያስ አደለ | ወ | 2 |

**የቆሰሉ ሴቶች**

| ተ.ቁ | ስም | እድሜ |
|---|---|---|
| 1 | ጌጤ አረጋ | 65 |
| 2 | የተመኝ አሰን | 60 |
| 3 | ትርንጎ ደምጤ | 30 |
| 4 | እናኒ ደምጤ | 45 |
| 5 | ደስታ አምደማሪያም | 45 |
| 6 | ቃልኪዳን ከፈለኝ | 26 |
| 7 | የሺአረግ ታከለ | 22 |
| 8 | ብርቱካን አስግደው | 15 |
| 9 | መቅደስ ምናሉ | 14 |

### 3.1.2. **የአንፆኪያ ገምዛ ወረዳ**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር ም/ቤት በሰሜን ሸዋ ዞን የአንፆኪያ ገምዛ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር አገወ/አስ/084/014 በቀን 12/04/2014ዓ.ም ለኢሰመጉ በተላከ መረጃ መሰረት ከዚህ በታች ስማቸው የተዘረዘሩ ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ወንድ፡ 121፣ሴት፡ 4 በድምር፡ 125 ንጹሃን ሰዎች በህወኃት ታጣቂ ቡድኖች መገደላቸውን ለመረዳት ችሏል፡፡

**ህገ-ወጥ ግድያ**

| ተ.ቁ. | የተገደለው ሰው ስም | ዕድሜ | ፆታ | ቀበሌ (ቦታ) | የስራ ሁኔታ | የማች ቤተሰብ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ወ | ሴ | ድ |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ታደሰበከጠአትፍቺ ው | ወ | 60 | መኮይ | አ/አደር | 3 | 2 | 5 |
| 2. | አያሌው ማህመድ እድሪስ | ወ | 53 | መኮይ | ጥ/ሰርተኛ | 2 | 3 | 5 |
| 3. | አበበ ነበርሞልቶት | ወ | 56 | መኮይ | ነጋዴ | 3 | 3 | 6 |
| 4. | ንጉስአሰፋ ወ/አገኘ | ወ | 47 | መኮይ | አ/አደር | 3 | 6 | 9 |
| 5. | ፉአድ አስማረው | ወ | 32 | መኮይ | ነጋዴ | 2 | 2 | 4 |
| 6. | አማከለው ጌትነት ቸሩ | ወ | 30 | መኮይ | አ/አደር | 1 | 4 | 5 |
| 7. | ዋናሳጅን ውብሸት ምንይሉ | ወ | 44 | መኮይ | ፖሊስ | 2 | 3 | 5 |
| 8. | ቢኒያም አባተ ዳምጠው | ወ | 27 | መኮይ | ተማሪ | 4 | 2 | 6 |
| 9. | እድሪስ አህመድ ሃሰን | ወ | 36 | መኮይ | አ/አደር | 2 | 2 | 4 |
| 10. | አህመድ አብዱ | ወ | 30 | መኮይ | ከተማ ነዋሪ | 5 | 1 | 6 |
| 11. | መካሻው ደሳለኝ | ወ | 32 | መኮይ | ከተማ ነዋሪ | 2 | 2 | 4 |
| 12. | ግርማ አሰፋ አበበ | ወ | 50 | መኮይ | ከተማ ነዋሪ3 | 3 | 3 | 6 |
| 13. | ሰዩም ይፍሩ | ወ | 55 | መኮይ | ከተማ ነዋሪ | - | - | - |
| 14. | መሃመድ ሃሰን አህመድ | ወ | 68 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 3 | 2 | 5 |
| 15. | መሃመድ ሃሰን | ወ | 70 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 3 | 5 |
| 16. | ዘይኑ ዳውድ ሁሳን | ወ | 26 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 2 | 4 |
| 17. | ሃሰን ዳውድ ሁሳን | ወ | 35 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | | | |
| 18. | እንድሪስ ሁሴን | ወ | 30 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | | | |
| 19. | መሃመድ አህመድ ኢብራሂም | ወ | 30 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | | | |
| 20. | ሀሴን መሃመድ | ወ | 44 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | - | -. | - |
| 21. | ዳውድ ሁሴን | ወ | 32 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | - | - | -- |
| 22. | መሃመድ መንግስቴ | ወ | 58 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 0 | 7 | 7 |
| 23. | አበበ ዳምጠው | ወ | 61 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 4 | 3 | 7 |
| 24. | አለሙ ገዝሙህዩ | ወ | 61 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 4 | 6 |
| 25. | ሙሄ መሃመድ | ወ | 52 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 4 | 2 | 6 |
| 26. | ግዛው ሰይድ | ወ | 26 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 3 | 4 | 7 |
| 27. | ሰይድ ሁሰን | ወ | 45 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 2 | 4 |
| 28. | እመር ሰይድ | ወ | 60 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 3 | 3 | 6 |
| 29. | ሁሴን ይመር | ወ | 14 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 5 | 4 | 9 |
| 30. | ግርማ ሞገስ | ወ | 23 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 5 | 4 | 9 |
| 31. | ጁሃር ግርማ | ወ | 55 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 3 | 5 |
| 32. | ከሪም ማሙዩ | ወ | 64 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 4 | 6 |
| 33. | መሃመድ ሳሊህ | ወ | 62 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 4 | 3 | 7 |
| 34. | እመርመሃመድ ግዛቸው | ወ | 63 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 4 | 6 |
| 35. | ሃሰን ግዛው | ወ | 60 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 4 | 6 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 36. | እምርመሃመድ ግዛቸው | ወ | 27 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 4 | 6 |
| 37. | ሰይድ መሃመድ | ወ | 24 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 1 | 1 | 2 |
| 38. | ከድር መሃመድ | ወ | 68 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 2 | 4 |
| 39. | ጁሃር መሃመድ | ወ | 67 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 1 | 1 | 2 |
| 40. | መሃመድ የሱፍ | ወ | | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 2 | 4 |
| 41. | መሃመድ የሱፍ | ወ | | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | - | - | - |
| 42. | ሁሴን መሃመድ | ወ | 27 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 2 | 4 |
| 43. | በቀለ በለጠ | ወ | 39 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 2 | 4 |
| 44. | መሃመድ ዘኪይ | ወ | 34 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 1 | 1 | 2 |
| 45. | ይመር መሃመድ | ወ | 37 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 5 | 3 | 8 |
| 46. | ሳኒ ሁሴን ቸርነት | ወ | 67 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 5 | 4 | 9 |
| 47. | አህወመድ መሃመድ | ወ | 45 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 1 | 3 |
| 48. | ሰይድ የሱፍ | ወ | 42 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 4 | 2 | 6 |
| 49. | ይመር የሱፍ | ወ | 29 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 1 | 3 | 4 |
| 50. | እብራሄምሙሉህ | ወ | 72 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 1 | 1 | 2 |
| 51. | ሁሴን መሃመድ | ወ | 56 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 3 | 4 | 7 |
| 52. | ሰይድ አህመድ | ወ | 22 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 3 | 5 |
| 53. | ሰይድ ሁሴን | ወ | 75 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 4 | 4 | 8 |
| 54. | እመር አልይ | ወ | 29 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 3 | 5 | 8 |
| 55. | ማሞ ሽዋአረጋው | ወ | 47 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 4 | 4 | 8 |
| 56. | ሸህ ኡመር ወርቅነህ | ወ | 50 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 3 | 2 | 5 |
| 57. | አህመድ አብዱ | ወ | 34 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 2 | 4 |
| 58. | ሰይድ ሁሴን | ወ | 59 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 1 | 2 | 3 |
| 59. | ተስፋው የማም | ወ | 35 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 1 | 1 | 2 |
| 60. | ሙሃ የመር | ወ | 50 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር98 | 1 | 5 | 6 |
| 61. | ይመር መሃመድ | ወ | 65 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 1 | 3 |
| 62. | አህመድ ይመርዪ | ወ | 40 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 1 | 4 | 5 |
| 63. | ሁሴን ኢብራሂም | ወ | 70 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 4 | 2 | 6 |
| 64. | መሃመድ አሚን | ወ | 21 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 5 | 7 |
| 65. | ተፈሪ ግዛው | ወ | 65 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 3 | 1 | 4 |
| 66. | ተስፋዬ ተፈራ | ወ | 45 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 1 | 1 | 2 |
| 67. | አበራ ግዛው | ወ | 65 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 0 | 4 | 4 |
| 68. | ገሰሰ ታዬ | ወ | 41 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 4 | 9 | 13 |
| 69. | ዝንበለው ሻወል | ወ | 62 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 4 | 2 | 6 |
| 70. | ሻንበል ሻረው አበበ | ወ | 56 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 5 | 7 |
| 71. | ሲራጅ ኑርዪ | ወ | 32 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 3 | 1 | 4 |
| 72. | እንዳል ተፈሪ | ወ | 26 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 1 | 1 | 2 |
| 73. | በለጠ ታደሰ | ወ | 25 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 2 | 4 |
| 74. | አሳምር ድንበሩ | ወ | 23 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 4 | 3 | 7 |
| 75. | ግርማ ፀጋዬ | ወ | 70 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 4 | 4 | 8 |
| 76. | አሚና አመዘነው | ወ | 43 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 5 | 1 | 6 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 77. | ግርማ ፀጋዬ | ወ | 59 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 2 | 2 | 4 |
| 78. | ከውንያን ይመር | ወ | 25 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 1 | 1 | 2 |
| 79. | ከውንያ ሙሄ | ወ | 48 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 0 | 3 | 3 |
| 80. | መሪማ አሰፋ | ወ | 35 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 3 | 3 | 6 |
| 81. | ሰፉ ገበሬው በሻ | ወ | 48 | ኩሬ | አ/አደር | 1 | 2 | 3 |
| 82. | ድጋፍ ከፋለኝ | ወ | 35 | ኩሬ | አ/አደር | 3 | 3 | 6 |
| 83. | ደስታው አሰፋ | ወ | 55 | ዋሻንገት | አ/አደር | 1 | 2 | 3 |
| 84. | አያሌው አብዱ | ወ | 35 | ዋሻንገት | አ/አደር | 4 | 2 | 6 |
| 85. | ጌታቸው አብዱ | ወ | 50 | አዋሻንገት | አ/አደር | 4 | 4 | 8 |
| 86. | መስፍን አስምረው | ወ | 45 | ዋሻንገት | አ/አደር | 3 | 2 | 5 |
| 87. | እንዳለ አሰፋ | ወ | 30 | ዋሻንገት | አ/አደር | 0 | 2 | 2 |
| 88. | እንዳለ አረጋኘኝ | ወ | 25 | ዋሻንገት | አ/አደር | 2 | 2 | 4 |
| 89. | ንጉሴ | ወ | 35 | ዋሻንገት | አ/አደር | 2 | 2 | 4 |
| 90. | አሳምን ድምሩ | ወ | 30 | ዋሻንገት | አ/አደር | 2 | 2 | 4 |
| 91. | ተሰማ ማሞ | ወ | 35 | ዋሻንገት | አ/አደር | 6 | 4 | 10 |
| 92. | ሱልታን ተገኘ | ወ | 40 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 4 | 2 | 6 |
| 93. | እንድሪስ ማሞ | ወ | 45 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 3 | 6 | 9 |
| 94. | ሰይድ ሃሰን | ወ | 40 | አሰ/ቀ/ወ | አ/አደር | 3 | 2 | 5 |
| 95. | ቢያሲቢያው ደስታ | ወ | 32 | ሃ/ማ/ማ | አ/አደር | 2 | 3 | 5 |
| 96. | በለጠው መከተው | ወ | 42 | ጨቀጨቅ | አ/አደር | 5 | 4 | 9 |
| 97. | ጌታ ባልው ተሰፋዬ | ወ | 55 | ጨቀጨቅ | አ/አደር | 3 | 3 | 6 |
| 98. | ሰውነት ተስፋዬ | ወ | 50 | ጨቀጨቅ | አ/አደር | 4 | 2 | 6 |
| 99. | ኢብራሂም ወርቁ | ወ | 47 | ጨቀጨቅ | አ/አደር | 4 | 3 | 7 |
| 100. | አረጋ መሃመድ | ወ | 43 | ጨቀጨቅ | አ/አደር | 3 | 3 | 6 |
| 101. | የመር አምዴ | ወ | 55 | ጨቀጨቅ | አ/አደር | 2 | 1 | 3 |
| 102. | ሰይድ ዳውድ | ወ | 33 | አፍሶ | አ/አደር | 4 | 3 | 7 |
| 103. | ድምሩ ተሰፋዬ | ወ | 35 | አፍሶ | አ/አደር | 3 | 3 | 6 |
| 104. | እድሪስ አህመድ | ወ | 38 | አፍሶ | አ/አደር | 1 | 1 | 2 |
| 105. | አስፋው መሃመድ | ወ | 50 | አፍሶ | አ/አደር | 1 | 1 | 2 |
| 106. | መሃመድ አሊ | ወ | 55 | መቅደሳ | አ/አደር | 2 | 2 | 4 |
| 107. | እንድሪስ ይማም | ወ | 57 | መቅደሳ | አ/አደር | 3 | 2 | 5 |
| 108. | ሰይድ ይመም | ወ | 27 | መቅደሳ | አ/አደር | 5 | 3 | 8 |
| 109. | አህመድ ሰይድ | ወ | 55 | መቅደሳ | አ/አደር | 1 | 1 | 2 |
| 110. | መሃመድ መኮንን | ወ | 55 | መቅደሳ | አ/አደር | 3 | 2 | 5 |
| 111. | አልይጌመታፈሪያ | ወ | 32 | መቅደሳ | አ/አደር | 3 | 2 | 5 |
| 112. | አሴ አህመድ | ወ | 60 | መቅደሳ | አ/አደር | 3 | 2 | 5 |
| 113. | አሲፋ የማም | ወ | 47 | መቅደሳ | አ/አደር | 4 | 3 | 7 |
| 114. | አል መሁመድ | ወ | 39 | መቅደሳ | አ/አደር | 4 | 3 | 7 |
| 115. | ፈቲማ እንድሪስ | ወ | 35 | መቅደሳ | አ/አደር | 1 | 1 | 2 |
| 116. | አሰን ሽህ ሙሄ | ወ | 30 | መቅደሳ | አ/አደር | 1 | 1 | 2 |
| 117. | መሀመድ አወል | ወ | 35 | መቅደሳ | አ/አደር | 1 | 2 | 3 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 118. | ግርማ ደምላው | ወ | 38 | መኮይ | ነጋዴ | 3 | 3 | 6 |
| 119. | ምትኬ ደምላው | ወ | 34 | መኮይ | ነጋዴ | 1 | 1 | 2 |
| 120. | አለሙ ዳኛቸው | ወ | 45 | መኮይ | ነጋዴ | 1 | 5 | 6 |
| 121. | ገለታ ውባሬ | ወ | 18 | መኮይ | የመኪና ረዳት | 1 | 2 | 3 |
| 122. | አሳምን ድምሩ | ወ | 32 | አስ/ቀ/ወ | ግብርና | 3 | 4 | 7 |
| 123. | ሙባረክ ንጉሴ | ወ | 30 | ጨቀጨቅ | ግብርና | 3 | 4 | 7 |
| 124. | ጀማል ተፈሪ | ወ | 32 | ጨቀጨቅ | ግብርና | 2 | 3 | 5 |
| 125. | ገለታው አባተ | ወ | 32 | መኮይ | ነጋዴ | 4 | 2 | 6 |

በተጨማሪም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን የአንፆኪያ ገምዛ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር አገወ/አስ/084/014 በቀን 12/04/2014ዓ.ም ለኢሰመጉ በተላከ መረጃ መሰረት ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ወንድ፡ 84፣ ሴት፡ 5፣ ድምር፡ 89 ሰዎች ላይ ከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡

በአጠቃላይ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ስም ዝርዝር ከዚህ በታች በሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**የአካል ጉዳት/የቆሰሉ**

| ተ.ቁ | የቆሰሉ ግለሰቦችሰው ስም | ፆድሜ | እድሜ | ቀበሌ | የስራ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ሙሄ መሃመድ | ወ | | ሃ/ማ/ማ | ግብርና |
| 2. | አበራ ሽፈራ | ወ | | ሃ/ማ/ማ | ግብርና |
| 3. | ብርሃን በቀለ | ወ | | ሃ/ማ/ማ | ግብርና |
| 4. | አቡሽ ጣሌ | ወ | | ሃ/ማ/ማ | ግብርና |
| 5. | ባየው ሰማኝ | ወ | | ጨቀጨቅ | ግብርና |
| 6. | ሙሄው አልይ | ወ | | ጨቀጨቅ | ግብርና |
| 7. | ጣሰው አፈሳ | ወ | | ጨቀጨቅ | ግብርና |
| 8. | ተመስጋን ይርጋ | ወ | 15 | ዋሻ ንገት | ግብርና |
| 9. | አደፈርስ ማሞ | ወ | 50 | ዋሻ ንገት | ግብርና |
| 10 | አዲስ ጌታቸው | ወ | 12 | ዋሻ ንገት | ግብርና |
| 11 | ማሞ አደፈርስ | ወ | 40 | አስ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 12 | ግርማ ዳምጠው | ወ | 40 | አስ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 13 | አደፍርስ ማሞ | ወ | 30 | አስ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 14 | ግርማ ዳምጠው | ወ | 31 | አስ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 15 | መሃመድ አህመድ | ወ | 55 | አስ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 16 | የሲን ጥላሁን | ወ | 50 | አስ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 17 | መንግስቴ ከበደ | ወ | 27 | አስ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 18 | መሃመዴ አልይ | ወ | 30 | አስ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 19 | ኤርሚስ ነጋ | ወ | 27 | አስ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 20 | ኤፍሬም አሰፋ | ወ | 27 | አስ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 21 | መሃመድ አማን | ወ | 33 | አስ/ቀ/ወ | ግብርና |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 22 | ጣይቱ መሃመድ | ሴ | 37 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 23 | ከሚሳ ሁሲን | ሴ | 30 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 24 | ሻምበል አበራ | ወ | 40 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 25 | የሱፍ አልይ | ወ | 49 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 26 | ብዚ ነጋ | ወ | 15 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 27 | ኡመር ሁሴን | ወ | 62 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 28 | አህመድ መሃመድ | ወ | 45 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 29 | ፋጡማ መሃመድ | ሴ | 50 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 30 | ሙሳ ኢብራሂም | ወ | 29 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 31 | ሻምበል ጥላሁን | ወ | 70 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 32 | መሃመድ አሊ | ወ | 25 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 33 | እንዲርስ መሃመድ | ወ | 20 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 34 | ኢንድሪስ ዳውድ | ወ | 20 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 35 | ንጉሱ ሞልቶት | ወ | 45 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 36 | ሰአዳ ንጉስ | ሴ | 60 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 37 | ጸጋው ተገኝ | ወ | 13 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 38 | ሰአዳ ንጉስ | ወ | 20 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 39 | መቻል ጸጋይ | ወ | 5 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 40 | ሃሰን ኡመር | ወ | 32 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 41 | አብይ ማሞ | ወ | 40 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 42 | ካፒታል ሙሳ | ወ | 22 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 43 | አሰፋ ባየው | ወ | 26 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 44 | አህመድ ውብሬ | ወ | 45 | አሰ/ቀ/ወ | ግብርና |
| 45 | ብርሃን ማሞ | ወ | 42 | መቅደሳ | ግብርና |
| 46 | የስፍ ደምሴ | ወ | 40 | መቅደሳ | ግብርና |
| 47 | ሲሳይ ታዬ | ወ | 50 | መቅደሳ | ግብርና |
| 48 | ጀማል ሰአዳ | ሴ | 30 | መቅደሳ | ግብርና |
| 49 | ዘቢባ ሰየድ | ወ | 35 | መቅደሳ | ግብርና |
| 50 | ኢሳም አብዱ | ወ | 40 | መቅደሳ | ግብርና |
| 51 | አህመድ አሰን | ወ | 46 | መቅደሳ | ግብርና |
| 52 | አልይ የጥና | ወ | 55 | መኮይ | ግብርና |
| 53 | አበበ መኮንን | ወ | 45 | መኮይ | ግብርና |
| 54 | መኮንን ጭፍሬ | ወ | 30 | መኮይ | ነጋዴ |
| 55 | ሰይድ ይጥና | ወ | 45 | መኮይ | መ/ሰራተና |
| 56 | አበበ መኮንን | ወ | 50 | መኮይ | ነጋዴ |
| 57 | መኮንን ጭፍሬ | ወ | 47 | መኮይ | ነጋዴ |
| 58 | ስጦታው ታዬ | ወ | 55 | መኮይ | ነጋዴ |
| 59 | ደምሴ አስካደ | ወ | 60 | መኮይ | አ/አደር |
| 60 | መሃመድ ዋሽም | ወ | 60 | መኮይ | ነጋዴ |
| 61 | ይማም የብዛ | ወ | 50 | መኮይ | ነጋዴ |
| 62 | ክፍሌ ሽፋው | ወ | 40 | መኮይ | ነጋዴ |
| 63 | ባያሌው ጌታነታ | ወ | 30 | መኮይ | ነጋዴ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 64 | መሃመድ አሳለፍ | ወ | 55 | መኮይ | የቀን ሰራተኛ |
| 65 | ታሪኩ ማሞ | ወ | 34 | መኮይ | የቀን ሰራተኛ |
| 66 | ተሾመ ይድረስ | ወ | 42 | መኮይ | ነጋዴ |
| 67 | አመዘነ ተገኝ | ወ | 55 | መኮይ | የመ/ሰራተኛ |
| 68 | ማሞ በየነ | ወ | 43 | መኮይ | ነጋዴ |
| 69 | አስማረው ዳኜ | ወ | 32 | መኮይ | የቀን ሰራተኛ |
| 70 | አለሙ አረዳ | ወ | 46 | መኮይ | ነጋዴ |
| 71 | መሃመድ ውርቤ | ወ | 40 | መኮይ | ነጋዴ |
| 72 | ደምስ አስፋው | ወ | 50 | መኮይ | አ/አደር |
| 73 | እሸቴ ማሞ | ወ | 33 | መኮይ | ነጋዴ |
| 74 | አመዘነ ደምሴ | ወ | 30 | መኮይ | ነጋዴ |
| 75 | መሃመድ መኮንን | ወ | 48 | መኮይ | አ/አደር |
| 76 | ጀማል መሃመድ | ወ | 40 | መኮይ | ቀን ሰራተኝ |
| 77 | አያሌው ሽፈራ | ወ | 52 | መኮይ | ቀን ሰራተኝ |
| 78 | ከተማ ተሾመ | ወ | 35 | መቅደሳ | አ/አደር |
| 79 | ሱሊማን ኢብራሂም | ወ | 28 | መቅደሳ | አ/አደር |
| 80 | አብዱ የሱፍ | ወ | 30 | መቅደሳ | አ/አደር |
| 81 | አሚን ሱሊማን | ወ | 39 | መቅደሳ | አ/አደር |
| 82 | አብደል ጀሊል | ወ | 45 | መኮይ | ቀን ሰራተኝ |
| 83 | ተስፋዬ ተፈራ | ወ | 55 | መኮይ | አ/አደር |
| 84 | ግርማ ሃይሌ | ወ | 29 | መኮይ | አ/አደር |
| 85 | ተፈሪ በቀለ | ወ | 35 | መኮይ | ሹፌር |
| 86 | ገዛከኝ ናደው | ወ | 35 | ሃ/ማ/ማ | አ/አደር |
| 87 | መሰለ ትዛዙ | ወ | 28 | ሸበቶ | አ/አደር |
| 88 | እንዳለ አወፋ ንጉሴ | ወ | 28 | ግሶጌ | ረዳት |

### 3.1.3. **አጣዬ**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን የአጣዬ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር አጣ/ከ አከ/335/2014/ በቀን 13/04/2014 ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ መሰረት በወረዳው በሚገኙ 3ቀበሌዎች በአካባቢው በነበረው የትጥቅ ግጭት በህወሀት ታጣቂ ቡድን ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው በርካታ ዜጎች መገደላቸውን ገልጿል ከዚህም ውስጥ ወንድ 34፣ሴት 11 በድምር፡ 45 ሰዎች መገደላቸውን ከደብዳቤው ለመረዳት ተችሏል፡፡

***ህገ-ወጥ ግድያ***

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ |
|---|---|---|
| 1 | ዘውዱ ማሙዬ | ወ |
| 2 | በየነ ገብረየስ | ወ |
| 3 | ስጨናቂ በየነ | ወ |
| 4 | ብርቱካን ምናሉ | ሴ |

| | | |
|---|---|---|
| 5 | ዳዊት ምናሉ | ወ |
| 6 | ዘነቡ ታደሰ | ሴ |
| 7 | አውጋቸው ነጋሽ | ወ |
| 8 | ሰይድ መሃመድ | ወ |
| 9 | ትርንጎ ከበደ | ሴ |
| 10 | ዳንኤል ከበደ | ወ |
| 11 | ተመስገን በየነ | ወ |
| 12 | ሽጋው በየነ | ወ |
| 13 | እግስት ሙላቱ | ሴ |
| 14 | መቅደስ ሙላቱ | ሴ |
| 15 | ሜሮን ሙላቱ | ሴ |
| 16 | ሉባባ ማሽሌ | ሴ |
| 17 | ሰይድ መኮን | ወ |
| 18 | ከድር ጀማል | ወ |
| 19 | መስፍን ዳኜ | ወ |
| 20 | ሲሳይ አንባው | ወ |
| 21 | ቃልኪዳን ከፈለኝ | ሴ |
| 22 | ሙሉ አበበ | ወ |
| 23 | ማናገረው ገ/ሃና | ወ |
| 24 | አህመድ አባተ | ወ |
| 25 | ባዬ ሉሌ | ወ |
| 26 | ሉሌ ስሙኝ | ወ |
| 27 | መቅደስ ምናሉ | ሴ |
| 28 | ጸጉ ማህሌ | ሴ |
| 29 | ወንድሜ ነህ ካሳዬ | ወ |
| 30 | አስማረ ባሶሚሌ | ወ |
| 31 | አራጋው | ወ |
| 32 | ወላስማ ሲራጅ | ወ |
| 33 | ደኒ ዘውዱ | ወ |
| 34 | ዘውዴ ምትኬ | ወ |
| 35 | አሊ ሁሴን አህመድ | ወ |
| 36 | አህመድ መሀመድ | ወ |
| 37 | መንገሻ ነጋ ገብሬ | ወ |
| 38 | መለሰ ድረሴ | ወ |
| 39 | ከተማ ሰጤ | ወ |
| 40 | በሀይሉ ንጉሴ | ወ |
| 41 | ይርጋ የሺ ጥላ | ወ |
| 42 | ዘሙ አሊ | ሴ |

| | | |
|---|---|---|
| 43 | መስፍን ግርማ | ወ |
| 44 | ሙላቱ አልማው | ወ |
| 45 | ግርማ ዘለለው | ወ |

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን የአጣዬ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር አጣ/ከ አከ/335/2014/ በቀን 13/04/2014 ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ መሰረት በአካባቢው በነበረው የትጥቅ ግጭት በወረዳው በሚገኙ 3ቀበሌዎች ወንድ፡ 30፣ ሴት፡ 7፣ ድምር 37 ሰዎች ላይ ከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡

**የአካል ጉዳት**

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ |
|---|---|---|
| 1 | አረጋ አግዘው | ወ |
| 2 | ብርቱካን ምናሉ | ሴ |
| 3 | ምናሉ በየነ | ወ |
| 4 | ህይወት ምናሉ | ሴ |
| 5 | ዳናዊት ምናሉ | ወ |
| 6 | አስጨናቂ በየነ | ወ |
| 7 | ታምሩ ልብሰ ወርቅ | ወ |
| 8 | ሙሉ አብዱ | ሴ |
| 9 | መህመድ አብራር | ወ |
| 10 | ሰይድ አህመድ | ወ |
| 11 | እብርዬ ሁሴን | ወ |
| 12 | ጌታብሎ ከፈለኝ | ወ |
| 13 | ተስፋዬ ዳኘ | ወ |
| 14 | ሙሉቀን መለሰ | ወ |
| 15 | ሀሊማ መሀመድ | ሴ |
| 16 | ተምር አብዱ | ሴ |
| 17 | ሀድራ ሰይድ | ሴ |
| 18 | ይትባረክ ሉሌ | ወ |
| 19 | ተስፋዬ ሽቶ | ወ |
| 20 | ነጋ ብርቁ | ወ |
| 21 | ታጠረ አታለል | ወ |
| 22 | ደስታ ድረሴ | ወ |
| 23 | ተከተል መታፈሪያ | ወ |
| 24 | አልታሰብ ገላው | ወ |
| 25 | ጌጡ የጸዳው | ወ |
| 26 | እሸቱ ወልደሃና | ወ |
| 27 | ሙሉጌታ አስፋው | ወ |
| 28 | ሀይለኛው ንጉሴ | ወ |
| 29 | ላንዱበር ወንድሜነህ | ወ |

| | | |
|---|---|---|
| 30 | አበበ ከፈለኝ | ወ |
| 31 | አራራው ደባይ | ወ |
| 32 | ዮናስ ዝምበሌ | ወ |
| 33 | ነጋሽ ምትክ | ወ |
| 34 | እሸቴ ወርቅነህ | ወ |
| 35 | እንዳለ መርድ | ወ |
| 36 | ዮናስ ተካ | ወ |

### 3.1.4. **ሸዋሮቢት**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን ሸዋሮቢት ከተማ በነበረው የትጥቅ ግጭት በርካታ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመዋል፡፡ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን የሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ህጻናት፣ ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሸ/ከ/አስ/ሴ/ህ/ወ/ሰ/ማ/ጉ/102/35 በቀን 14/04/2014 ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ መሰረት በአካባቢው በነበረው የትጥቅ ግጭት በህወኃት ታጣቂ ቡድን በደረሰ ጥቃት ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ወንድ 62፣ ሴት 7 በድምሩ 69 ሰዎች መገደላቸውን እንዲሁም ወንድ፡ 15፣ ሴት፡ 2፣ ድምር፡ 17 ሰዎች ላይ ከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳት መድረሱን ከደብዳቤው ለመረዳት ተችሏል፡፡

## 4. ሰሜን ወሎ

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜኑ የአትዮጵያ ክፍል በነበረው ጦርነት የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ከተፈጸሙበት አካባቢ አንዱ የሆነው እና የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ በዚህ ልዩ መግለጫ ካካተታቸው ስፍራዎች አንዱ ሰሜን ወሎ ሲሆን ኢሰመጉ በዚህ አካባቢ ከጥር 23 ቀን 2014 ዓ.ም እስከ የካቲት 01 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የቆየ የምርመራ ስራን ያከናወነ ሲሆን በዚህም ሶስት ወረዳዎች ማለትም ላስታ-ላሊይበላ ወረዳ፣ ጋዞ-እስታይሽ ወረዳ እና ዋድላ-ሐሙሲት ወረዳ ተሸፍነዋል፡፡

### 4.1. **ላስታ-ላሊይበላ ወረዳ**

ይህንን ወረዳ የህወሀት ታጣቂ ቡድን ተቆጣጥሮ የቆየው ከሀምሌ 27 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 05 ቀን 2014 ዓ.ም ሲሆን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር የላስታ ወረዳ ሴቶች ህጻናት ጉዳይ ዋና ጽ/ቤት የሴቶች ማደራጃ ተሳትፎና ተጠቃሚነት የስራ ሂደት በደብዳቤ ቁጥር የሌ/ንቅ/ተሣ/ማ/128/14 በቀን 25/05/2014 ዓ.ም በሰጡት መረጃ መሰረት የህ.ወ.ሀ.ት ቡድን በላስታ ወረዳ በሚገኙ ገጠራማ ሰፈሮችና መንደሮች በመግባት የ28 ህጻናት ወላጆችን መግደሉን ለኢሰመጉ ገልጸዋል፡፡

### 4.2. **ጋዞ-እስታይሽ ወረዳ**

ይህንን ወረዳ የህወሀት ታጣቂ ቡድኑ ተቆጣጥሮ የቆየው ከሀምሌ 27 ቀን 2013ዓ.ም እስከ ታህሳስ 03/2013ዓ.ም ሲሆን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን የጋዞ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት በቀን 26/5/2014 ዓ.ም በሰጠው መረጃ

መሰረት  በጋዞ ወረዳ ባሉት 17 ቀበሌዎች ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ወንድ፡ 13፣ ሴት፡ 4፣ በድምሩ፡ 17 ሰዎች ተገድለዋል፡፡ በተጨማሪም በዚህ የትጥቅ ግጭት ምክንያት ከግጭቱ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸው ወንድ፡ 16፣ ሴት፡ 7፣ በድምሩ፡ 23 ሰዎች ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡

### 4.3. **ዋድላ-ሐሙሲት ወረዳ**

ይህንን ወረዳ የህወሀት ታጣቂ ቡድን ከሀምሌ 27 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 3 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ተቆጣጥሮ የነበረ ሲሆን  በአካባቢው በሁለቱ ተዋጊ ሀይሎች መካከል በነበረው ውጊያ በውል ከየትኛው ወገን እንደተተኮሱ ባልታወቁ ከባድ መሳሪያዎች በርካታ ሰዎች ህይወታቸውን አጥተዋል ከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳትም ደርሶባቸዋል፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሠ/ወሎ/ዞን አስ/ር በዋድላ ወረዳ የሀሙሲት (020) ቀበሌ አስ/ር ጽ/ቤት ቁ2 በደብዳቤ ቁጥር ሀሙ/አስ/24/014 በቀን 27/05/2014 በሰጠው መረጃ መሰረት በአጠቃላይ ወንድ፡ 33፣ ሴት፡ 9፣ በድምሩ፡ 42 ንጹሃን ዜጎች በጦርነቱ ምክንያት ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡

በዚህ አካባቢ በነበረው ከባድ ውጊያ አባቷን እና ወንድሟን ያጣች አንድ ወጣት ስለነበረው ውጊያ ለኢሰመጉ ስታስረዳ

> ***"ከነሀሴ 27 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስትና በትግራይ ሀይሎች መካከል በነበረው ጦርነት ምክንያት ከህዳር 28 እስከ ታህሳስ 2 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ በሁለቱም ወገን በኩል ከፍተኛ ውጊያ ይደረግ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ከየትኛው ወገን እንንተተኮሰ ባልታወቀበት እኛ ቤታችንን ዘግተን ከተቀመጥንበት በከባድ መሳሪያ በመመታቱ አባቴና ወንደሜ ወዲያውኑ ሊሞቱ ችለዋል፡፡ በጦርነቱ ምክንያት ወዲያውኑ መቅበር ባለመቻላችን ታህሳስ 02 ቀን 2014 ዓ.ም በጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ቀብራቸው ሊፈጸም ችሏል፡፡"*** ስትል አስረድታለች፡፡

## 5. **ሰሜን ወሎ**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙ የተለያዩ ከተሞችና የገጠር ቀበሌዎች (ወልዲያ፣መርሳ፣ውርጌሳ፣ስሪንቃ፣ሳንቃ በር፣ጌሾ በር፣ሊብሶ) የህውሃት ታጣቂ ቡድን በርካታ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የፈጸመ ሲሆን ኢሰመጉ የመስክ የምርመራ ስራ በማድረግ ያገኛቸውን የግድያና የአካል ማጉደል እንደሚከተለው አቀርቧል፡፡ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ መሰረት በአጠቃላይ በዞኑ **2384** ሰላማዊ ሰዎች መገደላቸውን ገልጿል፡፡

***ህገ-ወጥ ግድያ***

| ተ.ቁ. | የተገደለው ሰው ስም | የተገደለበት ቦታ |
|---|---|---|
| 1 | ወሌ ሲራጅ | መርሳ ከተማ 04 ቀበሌ |
| 2 | ሳሊም መሀመድ አሊ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 3 | ጀማል አህመድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |

| | | |
|---|---|---|
| 4 | ሰይድ አሊ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 5 | ሰይድ ኑርየ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 6 | ይማም አሊ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 7 | አብዱ መሐመድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 8 | አራጋው አህመድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 9 | ፋንታው መሀመድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 10 | ሼህ መሐመድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 11 | ሰይድ አሊ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 12 | ቢረዳ አባተ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 13 | ጉመታው አሊ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 14 | ሙሄ ሁሴን | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 15 | ወንድም አገኝ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 16 | ሞላ አበበ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 17 | ወንደሰን ተገኝ አበበ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 18 | አለምነው መከተ ሲሳይ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 19 | አብዱ ይማም ሁሴን | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 20 | አብዱ ሰይድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 21 | ሁሴን ሰይድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 22 | ጥላሁን ዘውዱ ደረሰ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 23 | አሰፋ መርጊያው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 24 | ካሚሉ ፋንታው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 25 | አህመድ አሰፋ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 26 | ጀማል ጌታሁን | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 27 | ፈንታው አድሴ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 28 | ኑርአዲስ ፈንታው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 29 | ፈንታቢል ብሩ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 30 | ሙሄ አሊ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 31 | አብዱ ኑርዬ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 32 | ሙሄው ሰይድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 33 | ሰይድ ኑርዬ ይማም | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 34 | አብዱ ኑርዬ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 35 | ወንደሰን እሸቱ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 36 | ጣይቱ ይመር ከበደ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 37 | ኑርአዲስ ታዬ ሀይሉ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 38 | አስናቁ ሲሳይ አራጋው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 39 | ደስታ ገብሬ ምረቱ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |

| | | |
|---|---|---|
| 40 | ራህማ ጓንጉል | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 41 | ይማም ሰይድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 42 | ዋሲሁን በሪሁን | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 43 | ቦጋለ አበበ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 44 | ደስታ ( የአእምሮ በሽተኛ) | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 45 | ኀይረዲን አህመድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 46 | ሀረጓ አብርሃ ሀይሉ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 47 | ሲራጅ አሊ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 48 | አንዋር ሰይድ ትኩ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 49 | መሀመድ ፈንታው ሀሰን | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 50 | ዳዊት ተክለማርያም | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 51 | ሰይድ ኑርዬ ይማም | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 52 | አብዱ ሁሴን መሐመድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 53 | ይማም አህመድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 54 | ቢረዳ አባተ ግዛው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 55 | ጀማል አህመድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 56 | ተፈራ ቢመኝ ምረቱ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 57 | ኑርዬ ሞላ መሐመድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 58 | ሁሴን አሊ አጀው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 59 | ኢማን መሐመድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 60 | ደምሴ መኮንን | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 61 | ረመዳን ኢጋሩ ሳንቃ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 62 | ይማም ሰይድ ሙስጠፌ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 63 | ፈንታው መሐመድ አሊ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 64 | አወል ይማም ሸበሽ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 65 | እርጎ መንገሻ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 66 | ይማም እንድሪስ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 67 | ሀድያ ኮርሜ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 68 | ሞላ ቀናው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 69 | ኑርዬ ሞላ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 70 | ጉማታው አሊ ተገኝ | መርሳ ከተማ ቀነሌ 03 |
| 71 | አሊ ተፈራ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 72 | መሐመድ አባተ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 73 | ይማም ሰይድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 74 | ሻንበል ደጉ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 75 | ጌታሰው ሙጨ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |

| | | |
|---|---|---|
| 76 | አብርሃ ብርሃኑ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 77 | ደስታ ሽፈራው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 78 | ኤፍሬም ሽፈረዋ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 79 | መሐመድ ሞላ አሰፋ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 80 | አቶ አልዩ ይማም | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 81 | አቶ ሻምበል ተፈራ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 82 | ሀቢብ ወርቁ አቦይ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 83 | ሰይድ ይመር መኮንን | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 84 | ሀቢብ ሰይድ ፈረጃ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 85 | ሀይሌ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 86 | መለሰ ካሳው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 87 | ሞገስ አበበ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 88 | እንድሪስ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 89 | እንድሪስ ደመቀ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 90 | ቢረዳ አባተ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 91 | ይማም አህመድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 92 | ይመር አያሌው ንጉስ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 93 | ጓዲሁን አስረሴ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 94 | ሀዋ አሊ ኑር | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 95 | መዲና ተሰማ ሞላ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 96 | ሰላም ፈንታው ስጦታው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 97 | ሀይለጊዮርጊስ ግርማ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 98 | አበጋዝ ብሩ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 99 | እሸቱ ሰጠ ምላሹ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 100 | ሲሳይ ፈንታው በየነ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 101 | ሰብለወንጌል ገበያው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 102 | ምስጋን ጌትነት | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 103 | ደስታ አለሙ ተፈራ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 104 | ፋሲካ ቢሆነኝ ጋረድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 105 | ገነት ስንታየሁ ሞላ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 106 | ሰብለ ገበያው በየነ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 107 | ሀብተጊዮርጊስ ግርማ አያሌው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 108 | ራሄል ለማ ገ/መስቀል | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 109 | አስራት ከበደ ካሳ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 110 | አራጋው ተካ ቦጋለ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 111 | ብርሃን ፈቃድ ተድላ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |

| | | |
|---|---|---|
| 112 | መሐመድ ሁሴን ምስጌ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 113 | አርጃ አመሌ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 114 | ተክቶ ቢረሳው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 115 | ምስጌ ጌታነህ ሀብቱ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 116 | እዮብ አለባቸው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 117 | ጌቱ ካሴ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 02 |
| 118 | የሺወርቅ ካሴ መኮንን | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 119 | ጸሐይ መኩሪያው አማረ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 120 | ሀብታሙ ገብሬ አበጋዝ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 121 | ወረታው ይታየው ውብነህ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 122 | ሽመልስ ሞላ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 123 | አማረ በላይ ለማ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 124 | አለም በላይ ለማ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 125 | መሰረት ተሻገር | መርሳ ከተማ ቀበሌ 03 |
| 126 | አክሊል ጸርጌ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 127 | ሄኖክ ፋንታው ከበደ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 128 | እየሩስ እሸቱ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 129 | ብሩክ ወንድምአገኝ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 130 | ሰጤት አያሌው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 131 | ሰዒድ ሱሊማን | መርሳ ከተማ ቀበሌ 05 |
| 132 | ዝናቡ ያረጋል አስፋው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 05 |
| 133 | ሙሉጌታ በላይ ሲሳይ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 05 |
| 134 | ጀሚላ ካሳው አበበ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 05 |
| 135 | ቶፊቅ አህመድ እንድሪስ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 06 |
| 136 | ያሬድ ወንዴ ምስጋን | መርሳ ከተማ ቀበሌ 06 |
| 137 | ጋሻው ምትኩ አበበ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 06 |
| 138 | እንዳባት ደስታው ሞገስ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 06 |
| 139 | እየሩስ በላይ አዲሱ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 06 |
| 140 | አብዱርሃማን ሱሊማን | መርሳ ከተማ ቀበሌ 06 |
| 141 | ዘነበ አዳነ ቢምረው | መርሳ ከተማ ቀበሌ 06 |
| 142 | ትዕግስት ስጦት | መርሳ ከተማ ቀበሌ 05 |
| 143 | ሙሉጌታ ሲሳይ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 07 |
| 144 | ገነት ለምለሙ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 08 |
| 145 | ሽመለስ ሞላ እጅጉ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 09 |
| 146 | ተስፋዬ ፈንታው ብርሃኑ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 09 |
| 147 | ሳሙኤል ተስፋዬ ደጉ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 10 |

| | | |
|---|---|---|
| 148 | ደስዬ መሠለ ፈንታ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 10 |
| 149 | አቶ ጎበዜ ሲሳይ | ወልዲያ ከተማ ቀበሌ 06 |
| 150 | አቶ አስማማው መለሰ ፈንቴ | ጉባላፍቶ ወረዳ ቀ.018 |
| 151 | አቶ ሰይድ አደም ሁሴን | ሊብሶ ቀበሌ ገ/ማ |
| 152 | አቶ ፈቃደ ደረሰ ወርቅነህ | ጉባላፍቶ ቀበሌ 12 |
| 153 | አቶ ይማም አደም ያሲን | ሀብሩ ወረዳ |
| 154 | አቶ መሃመድ እድሪስ ሂራጅ | ሊብሶ ቀ/ማ |
| 155 | ወጣት መሃመድ ሁሴን | ወልዲያ ከተማ ቀ.02 |
| 156 | አቶ ዝናቡ ያረጋል | ወልዲያ ከተማ ቀ.05 |
| 157 | አቶ ሙሉጌታ በላይ | ወልዲያ ከተማ ቀ.05 |
| 158 | ወጣት ሄኖክ ፋንታው | ወልዲያ ከተማ ቀ.04 |
| 159 | አቶ ሀይለማርያም ትኩዬ | ሳንቃበር ቀ/ገ/ማ |
| 160 | ወ/ሮ ሀዲያ ፎርሜ | መርሳ ከተማ ቀ.01 |
| 161 | አቶ ይማም ሰይድ ኢብራሒም | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 162 | አቶ ሰይድ ኑርዬ ይማም | መርሳ ከተማ |
| 163 | አቶ መሀሙድ መኮንን ያዘው | መርሳ ከተማ ወረላሉ ቀበሌ |
| 164 | አቶ ይማም ሰይድ ሙስጠፋ | መርሳ ቀበሌ 01 |
| 165 | ወ/ሮ ትእግስት አሰፋ ሀይሉ | መርሳ ቀበሌ 02 |
| 166 | አቶ ይማም እንድሪስ አህመድ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 01 |
| 167 | አቶ በላይ ወርቁ ከበደ | መርሳ ከተማ ቀበሌ 04 |
| 168 | አቶ አስራት ከበደ | ወልዲያ ቀበሌ 02 |

**የቆሰሉ**

| ተ.ቁ. | የቆሰለው ሰው ስም | እድሜ | የቆሰለበት ቀን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አስር አለቃ ገበያው አራጋው አከለ | 52 | ነሃሴ 21 ቀን 2013 | ወልዲያ ከተማ ነዋሪ ሲሆኑ፣ከላሽንኮቭ ጥይት ሰደፍ መላ አካላቸውን የተደበደቡ፣በወልዲያ ዩንቨርስቲ ቅጥር ግቢ ለአንድ ሳምንት የታሰሩ |
| 2 | ተማሪ እርጎ ዘውዱ ደመቀ | 18 | ህዳር/2014 | መርሳ ከተማ ነዋሪ ስትሆን በክላሽንኮቭ በጥይት ተመታ የቆሰለች |
| 3 | ተማሪ አብዱ መሀመድ ሁሴን | 13 | ህዳር/2014 | መርሳ ከተማ ነዋሪ የነበረ ሲሆን በተባራሪ ጥይት ጭንቅላቱን ጎኑ ላይ ተመቶ አነስተኛ ጉዳት የደረሰበት |
| 4 | አቶ ይማም አደም | 25 | ታህሳስ 6 ቀን/2014 ዓ.ም. | መርሳ ከተማ ነዋሪ ሲሆን፣ከድሮን የተተኮሰ ፈንጂ ፍንጣሪ ጉንጩና ደረቱ ላይ ጉዳት አድርሶበታል |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 5 | አቶ ገዱ ብርሃኔ ገ/ማ | 59 | ነሃሴ 14 ቀን/2014 ዓ.ም. | መርሳ ከተማ ነዋሪ ሲሆኑ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እንዳሉ በከባድ መሳሪያ የጥይት ፍንጣሪ ተመተው ቀኝ ታፋቸው ላይ ጉዳት ደርሶባቸዋል |
| 6 | በላይነሽ ተፈራ ሁሴን | 38 | ታህሳስ 6 ቀን 2014 ዓ.ም. | መርሳ ከተማ ነወሪ ስትሆን በጥይት ተመታ ቀኝ እግሯ ታፋዋ ላይ ጉዳት የደረሰባት |
| 7 | ጀሚላ አብዱ | 29 | ህዳር 10 ቀን/2014 ዓ.ም. | መርሳ ከተማ ነዋሪ ስትሆን በጥይት ግራ ጎኗ ላይ ተመታ ጉዳት የደረሰባት |
| **8** | ኑርአዲስ ያሲን | 20 | ታህሳስ 7 ቀን/2014 ዓ.ም. | መርሳ ከተማ ነዋሪ ሲሆን በጥይት ቀኝ ጉልበቱ ላይ የተመታ |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

| ተ.ቁ | የቆሰለው ሰው ስም | የጉዳት አይነት | የሚገኙበት ቀበሌ |
|---|---|---|---|
| 1 | አብዱ ሀሰን | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 04 ቀበሌ |
| 2 | ያሲን ደመቀ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 04 ቀበሌ |
| 3 | ጀማል ወርቁ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 04 ቀበሌ |
| 4 | ፈንታው አበጋዝ አሊ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 04 ቀበሌ |
| 5 | ዘሃራ ሰይድ የሱፍ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 04 ቀበሌ |
| 6 | ከድጃ ተበጀ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 04 ቀበሌ |
| 7 | ይመር ቢሆነኝ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 04 ቀበሌ |
| 8 | ይማም መሀመድ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 9 | መሀመድ ሞላ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 10 | አራጌ በላይ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 11 | ሰይድ ቃሴ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 12 | ይመር አበጋዝ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 13 | ሞላ መሀመድ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 14 | በላይነሽ ተፈራ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 15 | መሀመድ ደርሴ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 16 | ሞላ አሊ አገኘሁ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 17 | አራጌ በላይ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 18 | ጀማል አደም | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 19 | አብዱ አሸብር | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 20 | አሊ ሞላ አስፋው | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 21 | ካሳው አህመድ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 22 | በላይነሽ ተፈራ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 23 | ሀሰን ሞላ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 24 | አዲሱ አበራ ሙላት | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 25 | አሊ ሲሳይ መለሰ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 26 | ምናለ በየነ ቸኮል | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 27 | ሁሴን ኑርየ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 28 | ይማም አደም ደግየ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 29 | አደም ዱባለ ውነቱ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 30 | ሰይድ ዱባለ ውነቱ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 31 | መሀመድ ሀሰን ኑር | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 32 | ሀና አባተ ክብረት | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 33 | ከድጃ በርሄ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 34 | አሊ ደጉ ተፈራ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 35 | ኡስታዝ አብደላ ሲራጅ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 36 | ሀያት ሁሴን | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 37 | አዲሱ አሳየ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 38 | በላይነሽ ተፈራ ሁሴን | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 39 | ሰናይ ጌትየ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 40 | በለጠ አበራ ይመር | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 41 | አድስ ሰጠ ወርቁ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 42 | ጦይባ ፈንታው | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 43 | መሀመድ ፈንታው | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 01 ቀበሌ |
| 44 | ዘኪያ አህመድ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 03 ቀበሌ |
| 45 | ግርማ ታደሰ | ቁስለኛ | መርሳ ከተማ 03 ቀበሌ |
| 46 | ፈንታው እንድሪስ | የቆሰሉ | መርሳ ከተማ 03 ቀበሌ |
| 47 | ጎዳዳ ሞላ | የቆሰሉ | መርሳ ከተማ 03 ቀበሌ |
| 48 | ሀድያ ፈንታው | የቆሰሉ | መርሳ ከተማ 03 ቀበሌ |
| 49 | ሀድራ ፈንታው | የቆሰሉ | መርሳ ከተማ 03 ቀበሌ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 50 | ታደሰ ይመር | የቆሰሉ | መርሳ ከተማ 03 ቀበሌ |
| 51 | መስፍን ሉልሰገድ | የቆሰሉ | መርሳ ከተማ 03 ቀበሌ |
| 52 | ሰለሞን ውለታው | የቆሰሉ | መርሳ ከተማ 03 ቀበሌ |
| 53 | ጀማል ወርቁ | የቆሰሉ | መርሳ ከተማ 03 ቀበሌ |
| 54 | በድሩ መሀመድ | የቆሰሉ | መርሳ ከተማ 03 ቀበሌ |
| | | | |
| | | | |

## አፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ተከስቶ የነበረውን ግጭት አስመልክቶ በምርመራ ስራው ከሸፈናቸው በጦርነቱ ከተጎዱ እና በርካታ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ከተፈጸመባቸው ክልሎች መካከል አንዱ የአፋር ክልል ሲሆን ኢሰመጉ የምርመራ ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት አንዳንድ የክልሉ አካባቢዎች በጸጥታ ስጋት ውስጥ የነበሩ በመሆናቸው በዚህ ክልል ውስጥ ኢሰመጉ በዚህ ልዩ መገለጫ ለመሸፈን የቻለው ጥቅምት 05 ቀን 2014 ዓ.ም በህወኃት ታጣቂ ሀይሎች በተፈጸመ የከባድ መሳሪያ ጥቃት በአፋር ክልል ጭፍራ ወረዳ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ሲሆን በዋናነት በሚሌ ወረዳ ተጠልለው የነበሩ ተፈናቃዮችን እንደ መረጃ ምንጭ በመጠቀም ተጠናቅሯል፡፡

አንዲት የ12 ዓመት ታዳጊ ጥቅምት 05 ቀን 2014 ዓ.ም አፋር ክልል ጭፍራ ወረዳ የደረሰውን ከቤተሰቦቿ ጋር በመሆን ለኢሰመጉ ስታስረዳ

> ***"ከባድ መሳሪያ ከሩቅ ቦታ እየተተኮሰ ቤቶች ላይ እያረፈ ሲያፈርስ አይቼ ደነገጥኩ፣ ሰው ሁሉ እየተጯጯኸ መሸሽ ጀመረ እኔም ከእናቴ ጋር ሸሸሁ፡፡ ከከተማው ወጥተን ሲመሽ ደከመኝ ውሀ ጠማኝ ሌሊት ነው በጫካው ውስጥ እሾክ እየወጋን እንሄዳለን ሲደክመኝ አለቀስኩ እየተቆጡኝ ሁለት ቀን ተጉዘን እዚህ(ሚሌ) ደረሰን፡፡ አሁንም ሳስታውሰው እደነግጣለሁ አሁንም ያለሁበት ቤት ተመቶ የምሞት እናቴም አባቴም ወንድሞቼም የሚሞቱብኝ ይመስለኛል፡፡ አሁን ትምህርት የለም ወላጆቼ ለእኛ ምግብ ሲጨነቁ እሰማለሁ ሰዎች ምግብ ሲያመጡልን እንበላለን ካላመጡልን ግን ጾማችንን እንውላለን ጓደኞቼ ይማራሉ እኔ ግን አልማርም፡፡"*** ስትል አስረድታለች

በተጨማሪም ኢሰመጉ ባሰባሰበባቸው መረጃዎች አፋር ክልል ጋሊኮማ ከ200 በላይ የሚሆኑ ከጦርነቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች መሞታቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

***በሰሜኑ ጦርነት ከተገደሉ ሰዎች መካከል የጥቂቶቹ ፎቶግራፎች እንደሚከተለው ቀርቧል***



ሟች በዕውቀቱ ዘመነ

በዕውቀቱ ዘመነ በገረገራ ፍላቂት የሚኖር የ16 አመት የ7ኛ ክፍል ተማሪ የነበረ ሲሆን ጥቅምት 4 ቀን 2014 ዓ.ም በመኖሪያ ቤቱ እያለ በከባድ መሳሪያ ተመቶ ህይወቱ አልፏል፡፡



ሟች ፍቅር ብርሃን

ወ/ሮ ፍቅር በገረገራ ፍላቂት የምትኖር ባለትዳር እና የሁለት ልጆች እናት ነበረች ጳግሜ 5/2013ዓ.ም ከምሽቱ 2 ሰአት ላይ ወደ መኖሪያ ቤቷ በተተኮሰ ከባድ መሳሪያ ምክንያት ህይወቷ አልፋል፡፡



ሟች ፺/አ ደመቀ ቀላሙ

፺/አ ደመቀ ቀላሙ በላ/ጋይንት ይኖር የነበረ ሲሆን ነሐሴ 06/2013 ከቀኑ 5፡00 ሰአት በተለምዶ መንትዮች በሚባለው ቦታ በጥይት ተመቶ ህይወቱ አልፏል፡፡



ሟች ሙላት መንገሻ

ሙላት መንገሻ በላ/ጋይንት ይኖር የነበረ ሲሆን በነሐሴ 7 ቀን 2013ዓ.ም ከምሽቱ 2፡30 በጎብጎብ በሚባል ቦታ በጥይት አንገቱን ተመቶ ህይወቱ አልፏል ፡፡



ሟች ታደሰ ሙሉአለም አሰፋ

አቶ ታደሰ የ50 አመት ጎልማሳ ሲሆኑ በግብርና ሲተዳደሩ ቆየተዋል በ5/12/13 ከምሽቱ 12፡30 በተተኮሰ ጥይት ተመቶ ህይወቱ አልፏል፡፡ስርዓተ ቀብሩ በደ/ገነት ኪዳነ ምህረት ቤተ-ክርስቲያን ተፈጽሟል፡፡



ሟች ገነት አለባቸው

ወ/ሮ ገነት በጋይንት የምትኖር ባለትዳር እና የሦስት ልጆች እናት ነበረች በ7/12/2013ዓ.ም ከቀኑ 9፡00 ሰአት ላይ መኖሪያ ቤቷ በር ላይ በተተኮሰ ጥይት ራሷን ተመታ ህይወቷ አልፋል፡፡



ሟች ገብሬ ተስፋ

አቶ ገብሬ ተስፋ የ31 አመት ጎልማሳ ሲሆን በባጃጅ ስራ የሚተዳደር ሲሆን በ7/12/2013 ከምሽቱ 2፡00 ሰአት ላይ በተተኮሰ ጥይት ሆዱን ተመቶ ህይወቱ አልፏል፡፡



ሟች ይበልጣል ባዬ

አቶ ይበልጣል ባዬ የ31 አመት ጎልማሳ የሆነ የመንገድ ትራንስፖርት ሰራተኛ ሲሆን በ7/12/2013ዓ.ም ከምሽቱ 2፡00 ሰአት ላይ በተለምዶ ጎብጎ ጋይንት ተብሎ በሚጠራው ቦታ በተተኮሰ ጥይት አናቱን ተመቶ ህይወቱ አልፏል፡፡



ሟች ማንያዘዋል አባተ

አቶ ማንያዘዋል አባተ በግብርና ስራ የሚተዳደሩ የ50 አመት የነበረ ሲሆን በቀን 27/2/2014ዓ.ም በጥይት ጭንቅላታቸውን ተመተው ህይወታቸው አልፏል፡፡



ሟች አስፋ ገበየሁ

አቶ አስፋ ገበየሁ በኤፍራታና ግድም ወረዳ የሚኖሩ የ 49አመት ጎልማሳ ሲሆኑ ያገቡና የአራት ልጆች አባት ነበሩ በቀን 27/2/2014ዓ.ም በተተኮሰ ጥይት ጭንቅላታቸው ላይ ተመተው ህይወታቸው አልፏል፡፡



ሟች ጌታሁን ሹሜ

አቶ ጌታሁን ሹሜ በግብርና ስራ የሚተዳደሩ የ 50 አመት ጎልማሳ የነበረ ሲሆን በቀን 27/2/2014ዓ.ም በ 11 ሰዓት ማጅራታቸውን በጥይት ተመተው ህይወታች አልፏል፡፡



ሟች ግርማ ታደሰ

አቶ ግርማ ታደሰ በግብርና ስራ የሚተዳደር የ45 አመት ጎልማሳ የነበረ ሲሆን በቀን 27/2/2014ዓ.ም በ11 ሰዓት ጭንቅላቱን በ ጥይት ተመቶ ህይወቱ አልፏል፡፡



ሟች አበበ በነበር

አቶ አበበ በነበር ያገቡና የአምት ልጆች አባት የነበሩ ሲሆነ በቀን 23/3/2014ዓ.ም አንገታቸውን በጥይት ተመተው ህይወታቸው አልፏል፡፡



ሟች ዘውዱ መከታ

ዘውዱ መከታ የ 25 አመት ወጣት የነበረ ሲሆን በቀን 27/2/2014ዓ.ም በ11ሰዓት ሆዱን በጥይት ተመቶ ህይወቱ አልፏል፡፡



ሟች ዘውዱ ይፍሩ

ዘውዱ ይፍሩ በአጣዬ ከተማ የሚኖር የ20 አመት ወጣት የነበረ ሲሆን በቀን 27/2/2014ዓ.ም በ11 ሰት ጭንቅላቱን በጥይት ተመቶ ህይወቱ አልፏል፡፡



ሟች ደምሰው ጥላዬ

አቶ ደምሰው ጥላዬ የ63 አመት አርሶአደር እና የስድስት ልጆች አባት የነበሩ ሲሆን በቀን 27/2/2014ዓ.ም በ11 ሰዓት ደረታቸው አካባቢ በጥይት ተመተው ህይወታቸው አልፏል፡፡



ሟች ሺጋው በላይነህ

አቶ ሺጋው በላይነህ በኤፍራታና ግድም ወረዳ የሚኖር የ65 አመት አዛውንት ሲሆኑ በቀን 28/2/2014ዓ.ም በጥይት ተመተው ህይወታቸው አልፏል፡፡



ሟች ጸጋዬ ተምትሜ

አቶ ጸጋዬ ተምትሜ የ 45 አመት ጎልማሳ ሲሆን በአጣዬ ወረዳ የሚኖር ባለትዳርና የ አምስት ልጆች አባት የነበረ ሲሆን በ ማጀቴ ከተማ በቀን 27/2/2014ዓ.ም በ11 ሰዓት ጭንቅላቱን በጥይት ተመቶ ህይወቱ አልፏል፡፡



ሟች ተፈራ ስመኝ

አቶ ተፈራ ስመኝ የ55አመት አዛውንት ሲሆኑ በኤፍራታና ግድም ወረዳ የ ሚኖሩ ባለትዳርና የ ስምንት ልጆች አባት የነበሩ የ55አመት አዛውንት ሲሆኑ በቀን 27/2/2014ዓ.ም በ11 ሰዓት ልባቸው ላይ በጥይት ተመተው ህይወታቸው አልፏል፡፡



ሟች ማሞ መኩሪያ

አቶ ማሞ መኩሪያ የ42አመት ጎልማሳ ሲሆን በኤፍራታና ግድም ወረዳ የሚኖር ባለትዳርና የአራት ልጆች አባት የነበረ ሲሆን በማጀቴ ከተማ በቀን 27/2/2014ዓ.ም በ10፡30 ትከሻው ላይ በጥይት ተመቶ ህይወቱ አልፏል፡፡



ሟች ደርበው ሙህመድ

አቶ ደርበው ሙህመድ የ50 አመት አዛውንት ሲሆኑ በኤፍራታና ግድም ወረዳ የሚኖሩ ባለትዳርና የስምንት ልጆች አባት የነበሩ ሲሆኑ በቀን 27/2/2014ዓ.ም በ11 ሰዓት ጭንቅላታቸውን በጥይት ተመተው ህይወታቸው አልፏል፡፡



ሟች ማሜ የምሩ

ሜ የምሩ የ 60 አመት አዛውንት ሲሆኑ በአጣዬ ወረዳ
የአራት ልጆች አባት የነበሩ ሲሆን በማጀቴ ከተማ
)14ዓ.ም በ11 ሰዓት ጭንቅላታቸው እና ደረታቸው
ሙተው ህይወታቸው አልፏል፡፡



ሟች አብርሀም ተስፋዬ

አብርሀም ተስፋዬ የ 20 አመት ወጣት ሲሆን በካራቆሬ የሚኖር የ12ኛ ክፍል ተማሪ የነበረ ሲሆን በቀን 28/2/2014ዓ.ም ሠደቆ የሚባል ቦታ በከባድ መሳሪያ ተመቶ ህይወቱ አልፏል፡፡



ሟች ዳምጠው ከበደ

አቶ ዳምጠው ከበደ የ40 አመት ጎልማሳ ሲሆን በኤፍራታና ግድም ወረዳ የሚኖር ያገባና የ አምስት ልጆች አባት የነበረ ሲሆን በማጀቴ ከተማ በቀን 27/2/2014ዓ.ም በ 11ሰዓት በጥይት ተመቶ ህይወቱ አልፏል፡፡



ሟች ታመነ አስማማው አባተ

አቶ ታመነ አስማማው በ መቄት ወረዳ የሚኖሩ የ80አመት አዛውንት ሲሆኑ በግብርና ስራ የሚተዳደሩ የአምስት ልጆች አባት ነበሩ በ5/12/2013ዓ.ም ከቀኑ 12፡00 ሰአት መኖሪያ ቤታቸው በር ላይ በተተኮሰ ጥይት ደረታቸው እና ግንባራቸው ላይ ተመተው ህይወታቸው አልፏል፡፡



ሟች ንጉስ አሰፋ

አቶ ንጉስ አሰፋ የ 50 አመት ጎልማሳ ሲሆኑ በአንጾኪያ ወረዳ መኮይ ቀበሌ የሚኖሩ ያገቡና የ ስድስት ልጆች አባት የነበሩ ሲሆን በመኮይ ቀበሌ በጥይት ጀርባቸው፤ሸንጣቸው ላይ እና እጃቸው ላይ በጥይት ተመተው ህይወታቸው አልፏል፡፡



ሟች ፉአድ አስማረው

አቶ ፉአድ አስማረው የ35 አመት ወጣት ሲሆን በኤፍራታና ግድም ወረዳ የሚኖር ያገባና የ አንድ ልጅ አባት ሲሆን በመኮይ ከተማ በቀን 23/3/2014ዓ.ም ከምሽቱ 4ሰዓት ደረቱ ላይ በጥይት ተመቶ ህይወቱ አልፏል፡፡



ሟች ግርማ ፀጋው

ግርማ ፀጋው በካራቆሬ የሚኖር የ23አመት ወጣት ነበር በቀን 28/2/2014ዓ.ም በከባድ መሳሪያ ተመቶ ህይወቱ ያለፈ ሲሆን በቀን 23/03/2014ዓ.ም ሚካኤል ቤተክርስትያን ስርዓተ ቀብሩ ተፈጽሟል



ሟች አማከለው ጌትነት

አቶ አማከለው ጌትነት የ34ዓመት ወጣት ሲሆን በኤፍራና ግድም ወረዳ የሚኖር ያገባና የአንድ ልጅ አባት የነበረ ሲሆን በመኮይ ከተማ ልቡ ላይ በጥይት ተመቶ ህይወቱ አለፏል፡፡



ሟች በሀይሉ ንጉሴ

በሀይሉ ንጉሴ የ27 አመት ወጣት ሲሆን በአጣዬ ከተማ የሚኖር ያገባና የ ሁለት ልጆች አባት የነበረ ሲሆን በቀን 23/3/2014ዓ.ም በ5 ሰዓት በጥይት ተመቶ ህይወቱ አልፏል፡፡



ሟች አያልቅበት ረዳ

አቶ አያልቅበት ረዳ የ 40 አመት ጎልማሳ ሲሆን በካራቆር የሚኖር ያገባና የ ስድስት ልጆች አባት የነበረ ሲሆን በቀን 3/3/2014ዓ.ም ህይወቱ አልፏል፡፡

## ጾታዊ ጥቃት

በዓለም አቀፍ እንዲሁም በአህጉር አቀፍ ደረጃ ጾታዊ ጥቃት አስመልክቶ በርካታ ህጎች አሉ፡፡ እነዚህ ህጎች በምንም ሁኔታ ውስጥ ማለትም በሰላምም ወቅት ሆነ በትጥቅ ግጭት ወቅት የሚፈጸሙ ጾታዊ ጥቃቶች ከህግ ውጪ መሆናቸውን ይደነግጋሉ፡፡

የአፍሪካ ቻርተር በሰዎች እና ህዝቦች መብቶች የሴቶች መብቶች በአፍሪካ ፕሮቶኮል (ማፑቶ ፕሮቶኮል) በአንቀጽ 1(j) ላይ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ምንነት ትርጉም ሲሰጥ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ማንኛውም አይነት ድርጊት አካላዊ፣ ጾታዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሊያደርስ የሚችል እንዲሁም እነዚህን ድርጊቶች ለመፈጸም የሚደረግ ዛቻ ወይም መሰረታዊ ነጻነቶችን በግል ወይም በአደባባይ፣ በሰላም ጊዜ ወይም በትጥቅ ግጭት ወቅት በዘፈቀደ መገደብ ወይም ማሳጣት ማለት ነው ሲል ትርጉም ይሰጠዋል፡፡

የጀኔቫ ስምምነት ሁለተኛ ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 ሰብዓዊ ክብር ላይ የሚፈጸም ሕገ-ወጥ ድርጊት፣ በተለይም አዋራጅና ዝቅ የሚያደርግ አያያዝ፣ አስገድዶ መድፈር፣ የግዳጅ ዝሙት አዳሪነትና ማናቸውንም ዓይነት የብልግና ጥቃት መፈጸም በየትኛውም ቦታ የተከለከለና ተከልክሎ የሚቀይ ነው ሲል ይደነግጋል፡፡

የልማድ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ በደንብ ቁጥር 93 ላይ አስገድዶ መድፈር እና ሌላ አይነት ጾታዊ ጥቃቶች የተከለከሉ መሆናቸውን እና የጦር ወንጀልን የሚያስከትሉ ናቸው ሲል ይደነግጋል፡፡ ይህ ክልከላ ዓለም አቀፍ የልማድ ህግ በመሆኑ በሁለቱም አይነት የትጥቅ ግጭቶች እና በየትኛውም የዓለም ክፍል ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ አባል ባትሆንም አለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤትን ለማቋቋም የወጣው ሰነድ (rome statute) በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2(b)xxii ላይ አስገድዶ መድፈር እንዲሁም ማንኛውም አይነት ጾታዊ ጥቃት የጦር ወንጀል እንደሆነ ይገልጻል፡፡

የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ አንቀጽ 270(f) በሲቪል ሰዎች ላይ የሚፈጸም የጦር ወንጀልን ሲዘረዝር አስገድዶ መድፈር አንድ የጦር ወንጀል መሆኑን ይደነግጋል፡፡

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የነበረው የትጥቅ ግጭት በርካታ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የተፈጸሙበት ሲሆን ከነዚህም መካከል በተለያዩ በትጥቅ ግጭቱ በተካሄደባቸው አካባቢዎች የተፈጸሙ ጾታዊ ጥቃቶች በዚህ ልዩ ዘገባ ላይ ተካተው ይገኛሉ፡፡

ይህ የኢሰመጉ ልዩ ዘገባ የሸፈነው የአማራ እና የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታትን ሲሆን በነዚህ ክልሎች ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች በርካታ ሰዎች ላይ ጾታዊ ጥቃቶች ተፈጽመዋል፡፡ ይህ ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በቦታ ቅደም ተከተል ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

1. **<u>ሰሜን ወሎ እና ደቡብ ጎንደር</u>**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ እና ደቡብ ጎንደር በነበረው የትጥቅ ግጭት ከፍተኛ የሆነ ሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የተፈጸሙባቸው የአገሪቱ ክፍሎች ሲሆኑ በእነዚህ አካባቢዎች በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች ኢሰመጉ በመዘዋወር የመስክ ምርመራን አከናውኗል፡፡ በምርመራ ስራውም ከተገኙት መጠነ ሰፊ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መካከል ጾታዊ ጥቃት አንዱ ነው፡፡ ጥቃት የደረሰባት ሴት ስለጉዳዩ ለኢሰመጉ ስታስረዳ

> ***"ነሀሴ 6 ቀን 2013 ዓ.ም ወደ ከተማችን ገቡ፡፡ አብዛኛው ሰው ከተማውን ለቆ ወጥቶ ነበር፡፡ እኔም በሬን ዘግቼ እንደተቀመጥኩኝ በሩን እየደበደቡ ከፈቸ አሉኝ፡፡ ከገቡ በኋላ ከቤቴ ያለውን መጠጥ ሙሉውን ከጠጡና ሌላውን ደግሞ ከሰበሩት በኋላ ሶስት ሆነው እየተፈራረቁ ደፈሩኝ "ሴት እናት እና እህት የላችሁም ተውኝ ስላቸው" ብሔር ተኮር የሆነ ጸያፍ ስድብ እየሰደቡኝ ደፈሩኝ በመጨረሻም ሸሮና በርበሬውን ይዘው ሄዱ፡፡ ባደረሱብኝ ጥቃት ከፍተኛ ደም ይፈሰኝ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ባለቤቴ ሊፈታኝ ችሏል፡፡"*** ስትል ገልጻለች፡፡

የህወሀት ታጣቂ ቡድን እነዚህን አካባቢዎች ተቆጣጥሮ በነበረበት ወቅት በርካታ ሴቶች (ህጻናት፣ ወጣትና አዛውንት) ላይ በቡድን እና በግል በመሆን ጾታዊ ጥቃቶችን ፈጽሟል፡፡ በዚህም በርካታ ሴቶች ላይ አካላዊ እና ስነልቦናዊ ጉዳቶች የደረሱ ሲሆን ችግሩን ይበልጥ አስከፊ ያደረገው በአካባቢው የህክምና ተቋማት ላይ ደርሶ በነበረው ውድመት ምክንያት ይህ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች የህክምና ድጋፍ ለማግኘት ባለመቻላቸው ለበለጠ ጉዳት መዳረጋቸውን ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል፡፡ ጥቃት የደረሰባት ሴት ስለጉዳዩ ለኢሰመጉ ስታስረዳ

*ነሀሴ 06 ቀን 2013 ዓ.ም የህወሀት ታጣቂዎች ወደ ከተማችን ገቡ አብዛኛው ሰው እና አቅም ያለው ከተማውን ለቆ ሄደ እኔ ሶስት ህጻናት ልጆችን ስለያዝኩኝ መሄጃም ስለሌለኝ ከቤቴ ቀረሁኝ ከተማ ውስጥ መብራት የለም ነበር ከፍተኛ ጦርነት ነበር የነበረው ነሀሴ 06 ቀን 2013 ዓ.ም አምስት ሆነው ወደ ቤቴ መጥተው የታጣቂ ቤት አሳይን አሉኝ ቤቴን ሙሉ በሙሉ ፈተሹት ሽሮና በርበሬውን ይዘውት ሄዱ የጦር መሳሪያ ደግነው አስፈራሩኝ ከዚያ በኋላ ሶስቱ እየተፈራረቁ ደፈሩኝ ሶስቱ ህጻናት ልጆቼ አይናቸው እያየ ይህንን ድርጊት ፈጸሙብኝ፡፡* ስትል ገልጻለች

የደቡብ ጎንደር መስተዳደር ዞን ነፋስ መውጫ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ነመቀ04/1842/13 በቀን 24/12/2013 ዓ.ም ለኢሰመጉ በላከው ደብዳቤ መሰረት የህወሀት ታጣቂ ቡድን አካባቢውን ተቆጣጥሮ በነበረበት ወቅት 72 ሴቶችን በቡድን እና በግል በመሆን አስገድዶ መድፈር መፈጸሙን ገልጿል፡፡

በተመሳሳይ በሰሜን ወሎ ዞን መቄት ወረዳ የህወሀት ታጣቂ ቡድን አካባቢውን ተቆጣጥሮ በነበረበት ወቅት የደረሱ ጾታዊ ጥቃቶችን መረጃ ለማሰባሰብ ኢሰመጉ በተለያየ መልኩ የሞከረ ቢሆንም በአካባቢው የነበረው የመንግስት መዋቅር ፈርሶ የነበረ በመሆኑ እንዲሁም ጾታዊ ጥቃት ደርሶባቸው የነበሩ ሴቶች ከማህበረሰቡ ሊደርስባቸው የሚችለውን ጫና በመፍራት መረጃ ለማጋራት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በቂ መረጃዎችን ለማግኘት አልተቻለም ስለሆነም በእዚህ ልዩ ዘገባ ላይ የተካተቱት መረጃ ለማጋራት ፈቃደኛ የሆኑት ብቻ ናቸው፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ በመቄት ጤና ጣቢያ አገልግሎት ሲሰጥ ከነበረ የጤና መኮንን በተገኘ መረጃ መሰረት የህወሀት ታጣቂ ቡድን በአካባቢው በነበረ ሰአት 3 ሴቶች ተደፍረው በማርገዛቸው ምክንያት የህክምና አገልግሎት እንደሰጣቸው ገልጿል፡፡

በእነዚህ አካባቢዎች ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎች ክብርን የሚያዋርዱ ስድቦች እየተሰደቡ እንደተደፈሩ ለኢሰመጉ ያስረዱ ሲሆን የዚህ ጥቃት ሰለባ የሆኑ በርካታ ሴቶች የተደበደቡ ሲሆን ብዙዎች ጥቃቱ ከደረሰባቸው በኋላ ምንም አይነት የህክምና እና ስነልቦና ድጋፍ እና አገልግሎት ያገኙ ባለመሆኑ ለከፋ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጉዳት ተዳርገዋል፡፡

## 2. <u>ደቡብ ወሎ ዞን</u>

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ ከጥር 23 እስከ የካቲት 01 ቀን 2014 ዓ.ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደቡብ ወሎ ዞን አምባሰል (ውጫሌ)፣ ሐይቅ፣ ደሴና ኮምቦልቻ ከተማዎች ላይ በመዘዋወር የምርመራ ስራዎችን አከናውኗል፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች ላይ የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የተፈጸሙ ሲሆን ከእነዚህም ጥሰቶች መካከል ጾታዊ ጥቃት ይገኝበታል፡፡

ኢሰመጉ በእነዚህ አካባቢዎች በመዘዋወር ጥቃት የደረሰባቸውን ሰዎች (ሴት ህጻናት፣ ወጣት፣ አዛውንት እና ወንዶችን ጨምሮ)፣ ቤተሰቦቻቸውን፣ የሚመለከተውን የመንግስት አካላት እና ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን የመረጃ ምንጮች በመጠቀም መረጃዎችን አሰባስቧል፡፡

በዚህም መሰረት ኢሰመጉ ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች በአጠቃላይ 122 ሰዎች (ሴት ህጻናት፣ ወጣት፣ አዛውንት እና ወንዶችን ጨምሮ) ላይ አስገድዶ መድፈር መፈጸሙን ለመረዳት የቻለ ሲሆን በተጨማሪም ኢሰመጉ በአካባቢው ተሰማርቶ ከነበረ

የጠቅላይ አቃቤ ህግ ቡድን ባገኘው መረጃ መሰረት 183 ሰዎች (ሴት ህጻናት፣ ወጣት፣ አዛውንት እና ወንዶችን ጨምሮ) ላይ አስገድዶ መድፈር መፈጸሙን ለመረዳት ችሏል፡፡

### 3. ሰሜን ሸዋ ዞን

ኢሰመጉ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የነበረውን የትጥቅ ግጭት አስመልክቶ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን በኤፍራታና ግድም ወረዳ፣ በአንፆኪያ ገምዛ ወረዳ፣ በሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር እና በአጣዬ ከተማ አስተዳደር የተለያዩ የምርመራ ስራዎችን አከናውኗል፡፡ ይህንንም ተከትሎ በርካታ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በአካባቢዎቹ መፈጸማቸውን ለመረዳት የተቻለ ሲሆን ከእነዚህም ጥሰቶች መካከል ጾታዊ ጥቃት ይገኝበታል፡፡ ጥቃት የደረሰባት ሴት ስለጉዳዩ ለኢሰመጉ ስታስረዳ

> ***"ከእህቴ ጋር ሸሽተን ሰው ቤት ተደብቀን ነበር በ16/03/2014 ዓ.ም ማታ 4 ሰዓት አካባቢ መጥተው ሊወስዱኝ ሲሉ አልሄድም ስል በጥይት አስፈራርተው ተኮሱብኝ ከዛ እህቴ ከምትሞቺ ሂጂ ስትለኝ የሌላ ሰው ቤት ይዘውን ሄዱ አንድ ሰው ነው የደፈረኝ ጠዋት ወደ ቤት ሂጂ አለኝ በትግረኛ ነበር ሲያወራ የነበረው በተደጋጋሚ ነበር ጥቃቱን ያደረሰብኝ፡፡"*** ስትል አስረድታለች

ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች ኢሰመጉ ባከናወነው የምርመራ ስራ በአጠቃላይ 33 ሴቶች (ህጻናት፣ ወጣት፣ አዛውንት) ላይ ጾታዊ ጥቃት መፈጸሙን ለመረዳት ችሏል፡፡ ኢሰመጉ ጥቃት የደረሰባቸው አንዳንድ ሴቶች በደብረ ብርሀን ዩኒቨርሲቲ ህክምና ማግኘታቸውን ለመረዳት ችሏል፡፡

### 4. ሰሜን ወሎ

ኢሰመጉ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን ላስታ-ላሊይበላ፣ ጋዞ እስታይሽ እና ዋድላ ሀሙሲት በመዘዋወር በትጥቅ ግጭቱ የደረሱ የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን መርምሯል፡፡ በዚህም የምርመራ ስራ ከተገኙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መካከል ጾታዊ ጥቃት አንዱ ነው፡፡ የህወሀት ቡድን ይህንን አካባቢ ተቆጣጥሮ በነበረበት ወቅት በርካታ ሴቶች (ህጻናት፣ ወጣት፣ አዛውንት) ጾታዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል፡፡

ኢሰመጉ ባሰባሰበው መረጃ መሰረት በእነዚህ አካባቢዎች 75 ሴቶች ላይ በቡድን እና በግል ጾታዊ ጥቃት የደረሰ ሲሆን ይህም ጥቃት በተፈጸመበት ወቅት ሴቶቹ ጸያፍ እና የሚያዋርድ ስድብ ይሰደቡ እንደነበር ለኢሰመጉ ገልጸዋል፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች የደረሰው ጾታዊ ጥቃት ከአካባቢው ከነበሩ ሰዎች ለመረዳት እንደተቻለው መጠነ ሰፊ ቢሆንም ጥቃቱ የደረሰባቸው ሴቶች ሊደርስባቸው የሚችለውን ተጽእኖ በመስጋት መረጃ ለማጋራት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በእዚህ ልዩ ዘገባ ላይ የተካተተው ቁጥሩ ሊያንስ እንደሚችል ይገመታል፡፡ አንዲት ጥቃት የደረሰባት ሴት ስለጉዳዩ ለኢሰመጉ ስታስረዳ

> ***"ከሀምሌ 27 ጀምሮ ነበር ወደ ከተማችን የገቡት መስከረም 10 ቀን 2014 ዓ.ም ምሽት አካባቢ 4 ሆነው መጥተው ጠላ እንድሰጣቸው አዘዙኝ ከዚያ ሰጠኋቸው ባለቤቴን ቀድመው ይዘውት ወጥተው ነበር አራቱ ሁሉም እየተጋገዙ እና እየተጠባበቁ ደፈሩኝ እንዲተዉኝ ስጠይቃቸው ጸያፍ ስድብ እየሰደቡ***

*ደፈሩኝ፡፡ በደረሰብኝ ጉዳት ከፍተኛ የሆነ ድብርት፣ ጭንቀት እና የስኑልቦና ጫና ውስጥ ነው ያለሁት፡፡”* ብላለች

## 5. ሰሜን ወሎ

ኢሰመጉ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙ በሀብሩ፣ ራያ ቆቦ፣ ዋድላ፣ ወልድያ፣ አንጎን፣ ግዳን፣ መቄት፣ ላሊበላ፣ ላስታ፣ ጎባ ላፍቶ፣ ቡግና፣ መርሳ፣ ጋዞ፣ ቆቦ፣ ዳውንት፣ ፍላቂት፣ ጋሽና፣ ሀራ ከተማ በመዘዋወር በትጥቅ ግጭቱ የደረሱ የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን መርምሯል፡፡ በዚህም የምርመራ ስራ ከተገኙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መካከል ጾታዊ ጥቃት አንዱ ነው፡፡ የህወሀት ቡድን እነዚህን አካባቢዎች ተቆጣጥሮ በነበረበት ወቅት በርካታ ሴቶች (ህጻናት፣ ወጣት፣ አዛውንት) ጾታዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል፡፡ ኢሰመጉ ከሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሰወአሰ/228/2014 በቀን 25/6/2014ዓ.ም ባገኘው መረጃ መሰረት ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች በድምሩ **421** ሴቶች ላይ ጾታዊ ጥቃት ደርሷል፡፡ ከእነዚህ ጥቃት ከደረሰባቸው ሴቶች መካከል **ሶስት** ሴቶች ሲሞቱ ለ**290** ሴቶች ደግሞ የሁለት ቀን የስነ-ልቦና ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

**ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች በየወረዳው እንደሚከተለው ቀርቧል**

| ተ.ቁ. | የወረዳው ስም | የተደፈሩ ሴቶች ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ሃብሩ ወረዳ | 47 |
| 2 | ራያ ቆቦ ወረዳ | 42 |
| 3 | ዋድላ ወረዳ | 29 |
| 4 | ወልድያ ከተማ | 25 |
| 5 | አንጎት ወረዳ | 15 |
| 6 | ግዳን ወረዳ | 5 |
| 7 | መቄት | 8 |
| 8 | ላሊበላ ከተማ | 3 |
| 9 | ላስታ ወረዳ | 33 |
| 10 | ጉባላፍቶ ወረዳ | 13 |
| 11 | ቡግና | 3 |
| 12 | መርሳ | 95 |
| 13 | ጋዞ | 58 |
| 14 | ቆቦ ከተማ | 9 |
| 15 | ዳውንት | 5 |
| 16 | ፍላቂት ከተማ | - |
| 17 | ጋሽና ከተማ | - |
| 18 | ሃራ ከተማ | - |
| | የተደፈሩ ሴቶች ጠቅላላ ድምር | 421 |

## ንብረት ውድመት

ንብረት የማፍራት መብት እና ላፈሩት ንብረት ጥበቃ የማግኘት መብት በተለያዩ ዓለም አቀፍ፣ አህጉር አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ህጎች ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በትጥቅ ግጭት ወቅት (ዓለም አቀፋዊ እና ዓለም አቀፋዊ ባልሆነ) ጥበቃ የሚደረግላቸው ንብረቶች እንዳሉ የሰብዓዊነት ህግ ይደነግጋል፡፡

የልማድ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ በደንብ ቁጥር 7 ላይ የትጥቅ ግጭቱ ተሳታፊ የሆኑ አካላት በማንኛውም ጊዜ በሲቪል ንብረቶች እና በወታደራዊ ንብረቶች መካከል ልዩነት የማድረግ ሀላፊነት አለባቸው፡፡ ጥቃት በወታደራዊ ንብረቶች ላይ ብቻ ነው መፈጸም ያለበት በሲቪል ንብረት ላይ ጥቃት ማድረስ የተከለከለ ነው ሲል ይደነግጋል፡፡ ይህ የልማድ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ አለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤትን ለማቋቋም የወጣው ሰነድ (rome statute) በሲቪል ንብረት ላይ የሚደርስ ጥቃት በትጥቅ ግጭቱ አስገዳጅ ካልሆነ በቀር የጦር ወንጀል እንደሚሆን ያብራራል፡፡

የጄኔቫ ስምምነት ሁለተኛ ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 16 በትጥቅ ግጭት ወቅት በታሪካዊ ሀውልቶች፣ በጥበብ ስራዎች ወይም የህዝብ ባህላዊና መንፈሳዊ ቅርስ እንደሆኑ በሚቆጠሩ የአምልኮ ቦታዎች ላይ ያነጣጠረ ማናቸውንም የጠላትነት ድርጊት መፈጸም፣ እንዲሁም ለወታደራዊ ድርጊት ድጋፍ እንዲሰጡ በአገልግሎት ላይ መዋል የተከለከለ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም ይኸው ፕሮቶኮል አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2(ሰ) ላይ ዝርፊያ ማናቸውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ የተከለከለና ተከልክሎም የሚቆይ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ አንቀጽ 270(ሸ) ንብረት የወረሰ፣ ያወደመ ወይም ለራሱ ያደረገ እንደሆነ የጦር ወንጀል እንደተፈጸመ ይደነግጋል በተጨማሪም ይኸው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ቀ) ምግብን፣ ለምግብ ማምረቻ የሚውሉ የእርሻ ቦታዎችን፣ ሰብልን፣ የቤት እንስሳትን፣ የመጠጥ ውሀ አገልግሎቶችን፣ የመስኖ ስራዎችን፣ የጤና ተቋማትን ወይም ትምህርት ቤቶችን የወረሰ፣ ያፈረሰ፣ ያጠፋ፣ ከጥቅም ውጨ እንዲሆን ያደረገ ወይም ለራሱ እንዲሆን ያደረገ እንደሆነ የጦር ወንጀልን እንደሚፈጽም ይደነግጋል፡፡

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ተካሂዶ የነበረውን የትጥቅ ግጭት ተከትሎ በርካታ ንብረት ላይ ውድመት ተከስቷል፡፡ ኢሰመጉ በምርመራ ስራ በሸፈናቸው በአማራ እና በአፋር ክልል በሚገኙ አካባቢዎች በነበሩ ከባድ ውጊያዎች ከፍተኛ መጠን ያለው ንብረት ወድሟል፡፡

ይህ የትጥቅ ግጭት በነበረባቸው አንዳንድ አካባቢዎች ውስጥ ከፍተኛ ውጊያ የነበረ በመሆኑ ከሁለቱም ወገኖች ሲወረወሩ በነበሩ ከባድ መሳሪያዎች የበርካታ ሲቪል ሰዎች መኖሪያ ቤቶች፣ የንግድ ቤቶች፣ ህንጻዎች፣ የመንግስት እና የግል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሆስፒታሎች፣ ትምህት ቤቶች፣ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ባንኮች እና የመሳሰሉት፣ የሀይማኖት ተቋማት እዲሁም ሌሎች በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ ስር ጥበቃ የተደረገላቸው የሲቪል ንብረቶች ላይ ከፍተኛ ውድመት ደርሷል፡፡

በተጨማሪም በህወሐት ታጣቂ ቡድን በተፈጸሙ ጥቃቶች ከላይ የተዘረዘሩት የሲቪል ንብረቶች ላይ ተመሳሳይ የሆነ ከፍተኛ ውድመት ደርሷል፡፡

1. <u>ሰሜን ወሎ እና ደቡብ ጎንደር</u>

ኢሰመጉ በሰሜን ወሎ እና ደቡብ ጎንደር አካባቢዎች በመዘዋወር ባከናወነው የምርመራ ስራ መሰረት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን መቄት ወረዳ በነበረው ከባድ ውጊያ ምክንያት በሁለቱም ተዋጊ ወገኖች ሲወረወሩ በነበሩ ከባድ መሳሪያዎች የ336 የንጹሃን ሰዎች መኖሪያ ቤቶች በከባድ መሳሪያዎች መውደማቸውን ለመረዳት ችሏል፡፡ የመቄት ነዋሪ የሆነ ጉዳት የደረሰበት ግለሰብ ስለጉዳዩ ለኢሰመጉ ሲያስረዳ

> ***ጳጉሜ 5 ቀን 2013 ዓ.ም 2፡00 ሰዓት አካባቢ ከመኖሪያ ቤቴ ላይ የተወረወረ ከባድ መሳሪያ 3 ሰዎችን ሲገድል ቤቴን ሙሉ ለሙሉ አፈራርሶብኛል፡፡*** ሲል አስረድቷል

በተጨማሪም የህወሀት ታጣቂ ቡድን ደቡብ ጎንደርን ተቆጣጥሮ በነበረበት ወቅት በመኖሪያ ቤቶች ላይ ከባድ ጉዳት አድርሷል፡፡ የጉና በጌምድር ወረዳ ነዋሪ የሆነ ጉዳት የደረሰበት ግለሰብ ስለጉዳዩ ለኢሰመጉ ሲያስረዳ

> ***የመኖሪያ ቤቴን ያቃጠሉና ያወደሙብኝ ሲሆን በመኖሪያ ቤቴ ከነበሩ ንብረቶች ፍሪጅ፣ ቴሌቪዥን፣ እንዲሁም በርካታ ንብረቶች ከነቤቱ ሙሉ በሙሉ በእሳት እንዲወድም ሆኗል፡፡ በአጠቃላይ ግምቱ ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን መኖሪያ ቤቴ በእሳት እንዲወድም ሆኗል፡፡*** ሲል አስረድቷል

በተመሳሳይ የጉና በጌምድር ወረዳ ነዋሪ የሆኑ ነጋዴ ስለደረሰባቸው የንብረት ውድመት ሲያስረዱ

> ***የህወሀት ሀይሎች ወደ ንግድ ቤቴ በመምጣት የሚፈልጉትን ምግብ ከሰጠኋቸው በኋላ ሊገለኝ ስለነበር በመካከላችን የተኩስ ልውውጥ ተደረገ፡፡ የንግድ ቤቱን ለሶስት ቀን በቦንብና በቤንዚን እያርከፈከፉ ሲያቃጥሉት ዋሉ፡፡ በአጠቃላይ የወደመው የንግድ ድርጅት ግምት ከአምስት ሚሊዮን በላይ የሚሆን ንብረቴ ወድሟል፡፡*** ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም የህወሀት ታጣቂ ቡድን በደቡብ ጎንደር ላይጋይንት ወረዳ ላይ ባደረሰው ጥቃት በርካታ ንብረት የወደመ ሲሆን ከዚህም መካከል በመንግስት ተቋማት 2,850,100 ብር የሚገመት ንብረት የወደመ ሲሆን በጤና ተቋማት ደግሞ 772,257 ብር የሚገመት ንብረት ወድሟል፡፡ አንድ የላይጋይንት ወረዳ ነዋሪ የሆኑ ግለሰብ ንብንብ ጤና ጣቢያ ላይ የደረሰውን ጉዳት ሲያስረዱ

> ***ድርጊቱ ሲፈጸም ከቦታው እራቅ ብዬ ስመለከት ነበር ነሀሴ 7 ቀን 2013 ዓ.ም የህወሀት ቡድን ወደ ከተማችን ገቡ እስከዚያ ድረስ በጤና ጣቢያው የቆሰሉ የመከላከያ ሰራዊት አባላት እርዳታ እየተሰጣቸው ነበር መድሀኒቶችን ሙሉ በሙሉ ወሰደዋል የወጣቶች ስኑ-ተዋልዶ መሳሪያዎች ተወስደዋል የእናቶች ማዋለጃ ሙሉ በሙሉ ተወስደዋል የሚችሉትን ይወስዳሉ የማይችሉትን ይሰባብራሉ ያወድማሉ በአጠቃላይ ጤና ተቋማቱን ከጥቅም ውጪ አድርገውታል 80% የሚሆነው የተቋሙ እቃ ወድሟል፡፡*** ሲሉ አስረድተዋል

2. <u>ደቡብ ወሎ ዞን</u>

ኢሰመጉ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደቡብ ወሎ ዞን በሚገኙ ወረዳዎች እና ከተማዎች በመዘዋወር የምርመራ ስራን ያከናወነ ሲሆን በዚህም መሰረት በርካታ የንጹሃን ዜጎች ንብረቶች ላይ (የመንግስት እና የግል) ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን ለመረዳት ችሏል፡፡ በዚህም መሰረት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የደሴ ከተማ አስተ ዳደር ትምህርት መምሪያ በደብዳቤ ቁጥር ደከት/403/2014 በቀን 25/05/2014 ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ መሰረት በመንግስት ትምህርት ተቋማት **222,071,799** ብር እና በግል ትምህርት ተቋማት **2,163,046** ብር በድምሩ **224,234,825** ብር የከተማው ትምህርት ተቋማት መውደሙን ገልጿል፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደቡብ ወሎ አስተዳደር ዞን አምባሰል ወረደ አስተዳደር ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር አስ-1/104/2014 በቀን 25/05/2014 ዓ.ም ለኢሰመጉ በላከው ደብዳቤ መሰረት በአምባሰል ወረዳ በህወኃት ታጣቂ ቡድን በመንግስት ሴክተር መስሪያ ቤቶች ላይ 61 741 964 ብር፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚ ተቋማት ላይ 403 835 068.75 ብር፣ በቀበሌ ማህበረሰብ ንብረት ላይ 211 024 742 ብር፣ በመንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ላይ 3 934 726.90 ብር በአጠቃላይ ድምር በአምባሰል ወረዳ 680 536 501 ብር የሚጠጋ ንብረት በህወሀት ታጣቂ ቡድን መውደሙን ገልጿል፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደሴ ከተማ አስተዳደር ሴቶችና ህጻናት ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ በደብዳቤ ቁጥር ሴ/ህ/መ/ጉ/መ-03/187/2014 ቀን 26/05/2014 ዓ.ም ለኢሰመጉ በላከው ደብዳቤ መሰረት የ285 ሴቶች መኖሪያ ቤት መውደሙን ገልጿል፡፡

በተጨማሪም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደቡብ ወሎ ዞን የሐይቅ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሐ/ከን/137/14 በቀን 25/05/2014 ዓ.ም በላከው ደብዳቤ መሰረት የወደመ የመንግስት ንብረት 319125670 ብር፣ የወደመ የንግድ ተቋማት ብዛት 805፣ በከፊልና ሙሉ በሙሉ በመሳሪያ የወደሙ ቤቶች ብዛት 454፣ በከፊል የወደሙ የእምነት ተቋማት ብዛት 2 መሆኑን ገልጿል፡፡

### 3. ሰሜን ሸዋ ዞን

ኢሰመጉ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የነበረውን ጦርነት ተከትሎ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን በሚገኙ በኤፍራታና ግድም ወረዳ፣ በአንጾኪያ ገምዛ ወረዳ፣ በአጣዬ ከተማ እና በሸዋሮቢት ከፍተኛ የሆነ ንብረት የወደመ ሲሆን በእነዚህም አካባቢዎች ኢሰመጉ በመዘዋወር የምርመራ ስራን አከናውኗል፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር ኤፍራታና ግድም ወረዳ የካራ ቆሬ ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ካቆ/ቀ/001/14 በቀን 13/04/2014 ዓ.ም በላከው ደብዳቤ መሰረት የ**36** ሰዎች ቤት በህወሀት ታጣቂ ቡድን መውደሙን ገልጿል፡፡ በተጨማሪም በወረዳው አንድ ቤተ ክርስቲያን፣ አንድ መስጂድ እና የጤና ጣቢያ ወድሟል፡፡ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ የሰሜን ሸዋ ዞን ጤና መምሪያ የኤፍራታና ግደም ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ መሰረት በአጠቃላይ **28 000 000** ብር የሚገመት ንብረት መውደሙን ገልጿል፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር ኤፍራታና ግድም ወረዳ አጣዬ ከተማ የአጣዬ ከተማ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም እንዲሁ ከፍተኛ የሆነ የንብረት ውድመት በነበረው የትጥቅ ግጭት በህወሀት ታጣቂ ቡድን እና በሸኔ ታጣቂ ቡድን የደረሰበት ሲሆን የኤፍራታና ግድም ወረዳ ትምህርት ዋና ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ኤግ/ትም/146/365/61 በቀን 11/04/2014 ዓ.ም ለኢሰመጉ በላከው ደብዳቤ መሰረት **11 029 500** ብር የሚገመት ንብረት መውደሙን ገልጿል፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን አንጾኪያ ገምዛ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር አገወ/አሰ/084/014 በቀን 12/04/2014 ዓ.ም ለኢሰመጉ በላከው ደብዳቤ መሰረት በወረዳው 107 የሚጠጉ ሰዎች ንብረታቸው እንደወደመባቸው ገልጿል፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን የሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ህጻናት፣ ሰራተኛ እና ማህበራ ጉዳይ ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሸ/ከ/አሰ/ሴ/ህ/ወ/ሰ/ማ/ጉ/102/35 በቀን 14/04/2014 ዓ.ም ለኢሰመጉ በላከው ደብዳቤ መሰረት 9106 እንስሳት፣ 15 መኖሪያ ቤት፣ 16262 የቤት ቁሳቁስ፣ የሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒል 30 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ንብረት መውደሙን ገልጿል፡፡

4. **<u>ሰሜን ወሎ</u>**

ኢሰመጉ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን ላስታ-ላሊይበላ፣ ጋዞ እስታይሽ እና ዋድላ ሀሙሲት በመዘዋወር በትጥቅ ግጭቱ የደረሱ የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን መርምሯል፡፡ በዚህም የምርመራ ስራ ከተገኙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መካከል ንብረት ውድመት አንዱ ነው፡፡ የህወሀት ቡድን ይህንን አካባቢ ተቆጣጥሮ በነበረበት ወቅት እና በአካባቢዎቹ በነበረው ከፍተኛ ውጊያ ከሁለቱም ወገን ሲተኮሱ በነበሩ ከባድ መሳሪያዎች በርካታ የሲቪል ንብረቶች ላይ ውድመት ደርሷል፡፡ አንድ ነዋሪ ስለሁኔታው ለኢሰመጉ ስታስረዳ

> ***ከህዳር 28 እስከ ታህሳስ 2 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ በመንግስትና በህወሀት መካከል ከፍተኛ ውጊያ ነበር በዚህ ወቅት ከየትኛው ወገን እንደተተኮሰ ባልታወቀበት እኛ ቤታችንን ዘግተን ከተቀመጥንበት በከባድ መሳሪያ በመመታቱ ልጄና ባለቤቴ ወዲያውኑ ተገድለዋል፡፡ ቤቴም ከነንብረቱ ወድሟል፡፡*** ስትል አስረድታለች

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን ጋዞ እስታይሽ ወረዳ ግምቱ 273,850,160.00(ሁለት መቶ ሰባ ሶስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ ሺህ አንድ መቶ ስድሳ ብር) የሆነ የመንግስትና የግለሰብ ንብረቶች መውደማቸውን የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት ለኢሰመጉ ገልጿል፡፡

5. **<u>ሰሜን ወሎ</u>**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ተነስቶ በነበረው ጦርነት ምክንያት በርካታ የሲቪል ንብረቶች ላይ ከፍተኛ የሆነ የንብረት ውድመት ደርሷል፡፡ የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ለኢሰመጉ በደብዳቤ ቁጥር ሰወአሰ/278/2014 በቀን 25/6/2014 ዓ.ም በሰጠው መረጃ መሰረት

1. 31 የዞን መስሪያ ቤቶች
2. 527 የወረዳ መስሪያ ቤቶች
3. 313 የቀበሌ ጽ/ቤቶች
4. 77 ጤና ጣቢያዎች
5. 219 ጤና ኬላዎች
6. 1 ሪፈራል ሆስፒታል
7. 6 የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል
8. 285 የግብርና ቀበሌ ጽ/ቤት
9. 285 የግብርና ማሰልጠኛ ጣቢያ
10. 609 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች
11. 52 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች
12. 435 የከተማ ውሃ ተቋማት
13. 2 ዩንቨርስቲ
14. 1 መምህራን ኮሌጅ
15. 1 የቴ/ሙያ ኮሌጅ
16. 1 የግብርና ምርምር
17. 1 ተርኒኪ የንብርት ውድመት የደረሰባቸው መሆኑን ገልጿል፡፡

## 6. <u>አፋር</u>

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ተከስቶ የነበረውን የትጥቅ ግጭት ተከትሎ በአፋር ክልል ከፍተኛ የሆነ የንብረት ውድመት የደረሰ ሲሆን በዚህም ግጭት በበርካታ የሲቪል ንብረቶቸ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል፡፡ ኢሰመጉ ከክልሉ ባገኘው መረጃ መሰረት በንብረት ደረጃ 9.1 ቢሊዮን ብር የሚገመት ንብረት መውደሙን ለመረዳት ችሏል፡፡ በተጨማሪም ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ጣቢያዎ፣ ጤና ኬላዎች፣ አንድ ሆስፒታል፣ አምቡላንሶች፣ የምግብ መጋዘኖች፣ የመንግስትና የግል ተሽከርካሪዎች፣ የውሀ ተቋማት መውደማቸውን ገልጸዋል፡፡

በክልሉ የሚገኙ 65 ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ የወደሙ ሲሆን 138 ትምህርትቤቶች በከፊል ወድመዋል፡፡ የወደመው ንብረት በገንዘብ ሲተመን 1 102 441 060 ብር ወድሟል፡፡ ከክልሉ ጤና ቢሮ ኢሰመጉ ባገኘው መረጃ መሰረት አንድ ሆስፒታል፣ 17 ጤና ጠቢያዎች፣ 62 የጤና ኬላዎች ሙሉ በሙሉ ወድመዋል እንዲሁም ተዘርፈዋል፡፡

## የጭካኔ፣ ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ እና ቅጣት

የጭካኔ፣ ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ እና ቅጣት በየትኛውም አይነት የትጥቅ ግጭት ወቅት የተከለከለ ድርጊት ሲሆን ይህ ድርጊት የጦር ወንጀልን እንደሚመሰርትም ተደንግጎ ይገኛል፡፡

የጄኔቫ ስምምነቶች የጋራ አንቀጽ 3 በግጭቱ ተግባር ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ በሌላቸው ሰዎች ላይ በሕይወትና በአካል ላይ የሀይል እርምጃ መፈጸም፣ በተለይም በማንኛውም መልኩ የሚፈጸም ግድያ፣ አካልን መቆራረጥ፣ ጭካኔ የተሞላበት ተግባር መፈጸምና ማሰቃየት በማንኛውም ጊዜና ቦታ የተከለከሉ መሆናቸውን በግልጽ ይደነግጋል፡፡

የጄቫኔቫ ስምምነቶች ተጨማሪ ፕሮቶኮል ሁለት አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) በሰዎች የህይወት፣ የጤንነትና የአካል ወይም የአእምሮ ደህንነት ላይ የሀይል ድርጊት በተለይም ግድያ እንዲሁም እንደ ማሰቃየት፣ አካልን ማጉደል ወይም እንደማናቸውም የአካል ቅጣት ያለ የጭካኔ አያያዝ በየትኛውም ቦታ የተከለከለና ተከልክሎም የሚቆይ ነው ሲል ይደነግጋል፡፡

የልማድ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ በደንብ ቁጥር 90 ላይ ማሰቃየት፣ የጭካኔ ወይም ኢሰብዓዊ አያያዝ እና ክብርን የሚያዋርድ እና ዝቅ የሚያደርግ አያያዝ የተከለከለ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

አለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤትን ለማቋቋም የወጣው ሰነድ (Rome statute) በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 (a)ii ላይ ማሰቃየት ወይም ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ የጦር ወንጀል እንደሆነ ይደነግጋል፡፡

ኢሰመጉ በአማራ እና በአፋር ክልል በሚገኙ አንዳንድ አካባቢዎች በመዘዋወር በሰራው የምርመራ ስራ መሰረት የህወሀት ታጣቂ ቡድን አንዳንድ አካባቢዎችን ተቆጣጥሮ በነበረበት ወቅት በበርካታ ንጹሃን ሰዎች ላይ የጭካኔና ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ እና ቅጣት መፈጸሙን ለመረዳት ችሏል፡፡

ይህ ውጊያ በነበረባቸው አንዳንድ አካባቢዎች የህወሓት ሀይል ተቆጣጥሮ በነበረበት ወቅት ኢ-ሰብዓዊ በሆነ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ መደብደባቸውን፣ የአካል ጉዳት ማድረሳቸውን እና ማንገላታታቸውን ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል፡፡ ኢሰመጉ ካነጋገራቸው ተጎጂዎች መካከል የደረሰባቸውን ድብደባ ሲያስረዱ

> ***ነሀሴ 21 ቀን 2013 ዓ.ም ከምሽቱ 3፡00 ሰዓት አካባቢ ወደ 20 የሚጠጉ የህወሀት ታጣቂ ቡድን አባላት መኖሪያ ቤቴን ከከበቡ በኋላ በሩን ሰብረው በመግባት ክላሽ መሳሪያ ወሰዱ እኔንም በመኪና ጭነው አይኔን አስረው እየደበደቡ ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ወሰዱኝ ሀላፊው የምትጠየቀውን መልስ አለኝ የፍጥኝ ታስሬ ከባድ ድብደባ አደርሰውብኝ አካሌ ተጎድቷል፡፡ ከነሀሴ 21 ቀን እስከ ነሀሴ 29 ቀን 2013 ዓ.ም እጅና እግሬን ታስሬ ያለምንም ውሀ እና ምግብ ቆይቼ ነበር፡፡ አለውህ***

***የሚባል አካባቢ ወስደው ሊረሽኑኝ ሲሉ ድንገት አምልጨ ህይወቴን አትርፌያለሁ፡፡*** ሲል አስረድቷል፡፡

ኢሰመጉ ባሰባሰባቸው መረጃዎች መሰረት ኢሰብዓዊ የጭካኔ አያያዝ እና ቅጣት የተፈጸመባቸው ሰዎች በአካባቢው በነበረው ከባድ ውጊያ እና በአካባቢው የነበሩ የጤና ተቋማት በአብዛኛው በመውደማቸው ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች የህክምና አገልግሎት ባለማግኘታቸው የከፋ ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ አንድ ጉዳት የደረሰባት ሴት ስለ ጉዳቷ ለኢሰመጉ ስታስረዳ

***ህዳር 2014 ዓ.ም በሰፈሬ ባለሁበት በዕለቱ የመከላከያ ሰራዊት ልብስ የለበሱ የህወሀት ሰራዊት አባላት የወገን ጦር መስለውን ሀገር ሰላም ብለን ከጓደኞቼ ጋር እያለን ያዙን ከዚህ በኋላ በእነርሱ ተማረከን ይዘውን ወደ ተራራ አወጡን ከዚያ በኋላ እየደበደቡን በሰደፍና በዱላ እየመቱን አጠገባቸው በቁም እስረኝነት አቆዩን እኔ ከጓደኞቼ ጋር ሶስት ነበርን በዛው ቀን ምሽት 9 ሰዓት አካባቢ አመለጥኩኝ፡፡ ቀጥታ ወደ ቤት መጣሁኝ እቤቴ ተደብቄ ባለሁበት በድጋሚ ወደ ቤቴ ገቡና ሙሉ ቤቴን በተቀጣጣይ ቦምብ ኢቃጠሉብኝ፡፡*** ስትል አስረድታለች፡፡

## የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች

በትጥቅ ግጭት ወቅት ሰዎች በአስገዳጅነት ማፈናቀል በጥብቅ የተከለከለ መሆኑን በርካታ ህጎች እና የህግ ድንጋጌዎች አሉ፡፡ ለዚህም ማሳያነት የልማድ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግጋቶች ላይ ከደንብ ቁጥር 129-133 ድረስ በስፋት ስለ ሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ዘርዝሮ ይዟል፡፡ በዚህ ህግ ላይ ለትጥቅ ግጭት ትርፍ ሲባል ዜጎችን ከመኖሪያቸው ማፈናቀል የተከለከለ መሆኑን በመግለጽ በትጥቅ ግጭት ወቅት የተፈናቀሉ ሰዎች ያላቸውን መብት አካትቶ ይዟል፡፡ በተመሳሳይም አለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤትን ለማቋቋም የወጣው ሰነድ (rome statute) በአንቀጽ 2(e)(viii) ላይ ሰላማዊ ሰዎች እንዲፈናቀሉ ማድረግ የጦር ወንጀል መሆኑን ይደነግጋል፡፡

የጀኔቫ ኮንቬንሽን ተጨማሪ ፕሮቶኮል ሁለት አንቀጽ 17 በግጭቱ ውስጥ የሚገኙ ሰላማዊ ሰዎች ደኅንነት፣ወይም አስገዳጅ የሆኑ ወታደራዊ ምክንያቶች እንዲፈጸም የሚጠይቁ ካልሆነ በስተቀር፣ ሰላማዊውን ህዝብ ከግጭቱ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ከአንድ ቦታ ማፈናቀል አይቻልም፡፡እንደዚህ ያለው መፈናቀል መፈጸም ያለበት ከሆነ ሰላማዊው ህዝብ አጥጋቢ የሆኑ የመጠለያ፣የጤና አጠባበቅ፣የጤንነት፣የደህንነትና የምግብ ሁኔታዎች በተሟሉበት አቀባበል ይደረግለት ዘንድ የሚቻሉት እርምጃዎች ሁሉ መወሰድ እንደሚኖርባቸው እንዲሁም ሰላማዊ ሰዎች ከግጭቱ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች የራሳቸውን ይዞታ ለቀው እንዲሄዱ እንደማይገደዱ በግልጽ አስቀምጧል፡፡

በአፍሪካ የሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ለመደገፍ እና ለመጠበቅ የወጣው የአፍሪካ ህብረት ስምምነት (የካምፓላ ስምምነት) በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 4(ለ) ላይ በትጥቅ ግጭት ወቅት ሰላማዊ የሆኑ ግለሰቦችን ወይንም በጅምላ የሚደረግ ማፈናቀል የተከለከለ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም ይኸው ስምምነት በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 5 ላይ የታጣቂ ቡድኑ አባላት ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች የሚቀርበውን ጥበቃ እና ድጋፍ ከማደናቀፍ መከልከል እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

## አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የነበረውን የትጥቅ ግጭት ተከትሎ በርካታ ዜጎች ከተለያዩ የአማራ ክልል ክፍሎች ተፈናቅለዋል፡፡ አካባቢዎቹ በህወሀት ታጣቂ ቡድን ቁጥጥር ስር በነበሩበት ወቅት እና ከባድ ውጊያ በነበረበት ወቅት በርካታ ዜጎች ቤት ንብታቸውን ትተው ተፈናቅለዋል፡፡

ኢሰመጉ ከአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ከዋግኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን ከአንዱ/ሳህል/ በስተቀር የቀሪ ወረዳ ነዋሪ ማህበረሰብ አስተዳደር ዞን ተፈናቅለዋል በደቡብ ጎንደር የተለያዩ ቦታዎች ለምሳሌ **በእብናት፣ ቢጋይንት/ነፋስ መውጫ፣ደብረታቦር**ና ሌሎችም ቦታዎች **በባህርዳርም** ዘንዘልማ በማቆያ ጣብያዎችና ቤት ለቤት ተጠልለው እና ተከራይተው ተጠልለው እንደነበር እና ተፈናቃዮች በከፍተኛ ቁጥር በደሴ ከተማ፣በኮምቦልቻ እና በሃይቅ ከተማ ይኖሩ እንደነበር ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል፡፡

### 1.እብናት

ከዋግኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን ከ8 ወረዳዎችና ሁለት ከተማ አስተዳደሮች ብዙ ተፈናቃዮች ብዙ ኪሎ ሜትሮችን በእግራቸው ቀንና ለሊት ተጉዘው በእብናት ከተማ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ ሴቶች ብቻ የተጠለሉበት እና በቂም ባይሆን የተወሰነ እርዳታ ተደርጎላቸው እንደነበር ማየት ተችሏል፡፡

> ***ተፈናቃዮች በዋናነት የህወኃት ታጣቂ ቡድን ወደ ዞኑ ከገባ ጳጉሜ 05/2013 ዓ.ም ምሽት ጀምሮ በቦታው የነበረው የአማራ ልዩ ሀይልና አዛዦቹ ወደኋላ አፈግፍጉ በተባለ ቅጽበት ነዋሪውም ለደህንነቱ በመስጋት ከልዩ ኃይሉ ጋር ለመሸሽ እና ለማፈግፈግ መገደዱን እና በቦታው የነበረው የመከላከያ ሰራዊት አባላትም እኛ አልታዘዝንም እያሉ የጠላትን ሃይል ለመመከት ፍላጎት እንዳልነበራቸው ተፈናቃዮች ገልጸዋል፡፡***

ይህ የምርመራ ስራ በተሰራበት ወቅት ማለትም ጥቅምት 6 ቀን 2014ዓ.ም ከዞኑ ምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በተገኘ መረጃ መሰረት በየጊዜው የተፈናቃይ ቁጥር የሚጨምር ወይም የሚቀንስ ቢሆንም እብናት ከተማ ላይ ከ18ሺህ በላይ ተፈናቃዮች እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ተፈናቃዮች ከነበሩበት አካባቢ በድንገት ስለወጡ የአልባሳት ዕጥረት፣ በቂ ያልሆነና ያልተመጣጠነ ምግብ፣ የመኝታ እና ሌሎችም ችግሮች እንደነበሩባቸው ኢሰመጉ ማወቅ ችሏል፡፡

የህወኃት ታጣቂ ቡድን አካባቢውን ተቆጣጥሮ በነበረበት ወቅት የነዋሪዎችን የቤት እቃ በመኪና በመጫን መዝረፉን፣ ከነዋሪው ህዝብ ላይ ምግብ በመንጠቅ ህዝቡ እንዲራብ ማድረጉን እና በተጨማሪም ተፈናቃዮች በሚፈናቀሉበት ሰዓት ነፍሰጡር እናቶች በመንገድ ላይ በመውለድ ለአደጋ ተጋላጭ እንዲሆኑ ማድረጉን እንዲሁም ተፈናቃዮች የተፈናቀሉት በለሊት ከተኙበት ስለነበር በድንጋጤ ሰው በሰው ላይ በደረሰው መረጋገጥ ህጻናት ህይወታቸው እንዲያልፍ ምክንያት እንደሆነ እና በእድሜ የገፉ ነዋሪዎች እዛው ስለነበሩ በረሃብ፣ በመድሃኒት እጥረትና በኑሮ ውድነት በከፍተኛ ችግር እንዲሰቃዩ እና የደረሱ ሰብሎችን በማጨድና ሰብስቦ በመውሰድ ከፍተኛ ውድመት አድርሰዋል፡፡

ተፈናቅለው በማቆያ ጣቢያ የነበሩ ተፈናቃዮችም ፍትሃዊ የሆነ እርዳታ ክፍፍል እንዳልተደረገላቸው እና ተፈናቅለው አብረው የመጡ የአካባቢው የዞንና የወረዳ አመራሮች ለተፈናቃዩ የሚመጣውን እርዳታ መንገድ ላይ ጠብቀው ለራሳቸው እያደረጉ እና እየሸጡ ለግል ጥቅማቸው እንዳዋሉት ኢሰመጉ ከአቤቱታ አቅራቢዎች ባሰባሰበው መረጃ መረዳት ችሏል፡፡

**2. ነፋስ መውጫ ከተማ/ጋይንት**

ነፋስ መውጫ ከተማ የህወኃት ታጣቂ ቡድን ብዙ የሃብት ውድመት ያደረሰባት ከተማ ብትሆንም ከህወኃት ሃይል ነጻ ከወጣች በኋላ የትጥቅ ግጭቱን ተከትሎ ከሰሜን ወሎና ከዋግኽምራ ዞን የተፈናቀሉ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ቤት ተከራይተው ተጠልለውባት እንደነበር ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል፡፡

**3. ባህርዳር ከተማ- ዘንዘልማ**

በባህርዳር ከተማ ከፍተኛ የሆነ የሰሜን ወሎ እና የዋግኽምራ ዞን ተፈናቃዮች በዘንዘልማ የገበያ ማዕከል እና በከተማው ቤት ተከራይተው ይገኙ የነበረ ሲሆን ከየዞኑ አስተባባሪዎች በተገኘ መረጃ መሰረት ከዋግኽምራ ዞን **ሴት** 6159፣ **ወንድ** 8363 **ድምር 14,522** ሲሆን አባወራ **3986**፣ እማወራ **2068** በቤተሰብ ብዛት ወንድ **4383**፣ ሴት **4091**፣ ድምር **8474** ሰዎች ተፈናቅለዋል፡፡ በሌላ በኩል ከሰሜን ወሎ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች ተፈናቅለው በባህርዳር ከነበሩት **28ሺህ** ተፈናቃዮች መሃል **3672** ብቻ ማቆያ/መጠለያ አግኝተው የነበረ ሲሆን **ከ10ሺህ** በላይ የሚሆኑት ደግሞ መጠለያ ያላገኙ ናቸው፡፡ ከጉባ ላፍቶ ኡራብ እና ከላሊበላ ብልባላ የተፈናቀሉ ተፈናቃዮቸወ የህ.ወ.ኃ.ት. ታጣቂዎች ያላችሁን አምጡ እያሉ አስገድደው ይቀሙ እንደነበር፣ንጹሃንን እንደገደሉና ሴቶችን እንደደፈሩ ገልጸዋል፡፡

**4. ደብረታቦር/አቦ ሰፈር**

ከወለጋ ሆሮጉድሩ ዞን ጃርቴ ወረዳ ከመጋቢት 30/2013 ዓ.ም ጀምሮ ከ**280** በላይ የሆኑ ተፈናቃዮች በደብረታቦር ከተማ በተለምዶ አቦ ሰፈር እየተባለ በሚጠራው ሰፈር ቆርቆሮ በቆርቆሮ በሆነ ማቆያ ተጠልለው የነበረ ሲሆን በቤተሰብ **15ኪሎ** ዱቄት እየተሰጣቸው በስቃይ ውስጥ የሚኖሩ ተፈናቃዮች እንደነበሩ እና መንግስትም ሆነ ሌሎች እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች በቂ በሚባል ደረጃ ድጋፍ ባለማድረጋቸው ተፈናቃዮች የነበሩበት ሁኔታ እጅግ አሰቃቂ እንደነበር ማወቅ ተችሏል፡፡

መጋቢት 2/2013 ዓ.ም ጃርቴ ወረዳ በአንድ ቀን ብቻ 28 ሰዎች ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ ተጨፍጭፈው ተገድለዋል፣ሀብት ንብረት ተዘርፏል፣ከ10ሺህ በላይ ሰዎች ከጃርቴ ወረዳ ተፈናቅለዋል፡፡

> ***በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ጀምረው የኖሩ ቢሆንም ከኃጫሉ ሁንዴሳ ግድያ በኋላ መኖር እንዳልቻሉ እና ልጆቻቸው በአማርኛ መማር እንዳይችሉ መደረጋቸውን እና የወረዳና የክልሉ አመራሮችም ምንም አይነት ጥበቃ እንዳላደረጉላቸው ይባስ ብሎም የመንግስት መዋቅር አካላት ለሸኔ ድጋፍ ያደርጉ እንደነበር በዚህም የስኑ ልቦና ጉዳት እንዳጋጠማቸው ተፈናቃዮች ገልጸዋል፡፡***

**አፋር ክልል**

የታጣቂው ህወሃት ቡድን የአፋርን ክልል በመቆጣጠር የሞት፣ የአካልጉዳት፣ የንብረት ውድመት እና መፈናቀል ያስከተለ ሲሆን ጥቅምት 5 ቀን 2014ዓ.ም የጭፍራ ከተማን በመድፍ በመደብደብ 3ሰዎች መገደላቸውን እና **367** የሚሆኑ አባወራዎች ወንድ **790**፣ ሴት **1230** በአጠቃላይ **2020** ሰዎች ቤት ንብረታቸውን ትተው ከ 50 ኪሎ ሜትር በላይ በእግር በመጓዝ ወደ ሚሌ ከተማ ልዩ ስሙ 50 ቀበሌ ወደሚባል ቦታ ተሰደዋል፡፡

በጋሊኮማ ከተማ ከ**200** በላይ ሰዎች በመድፍ ድብደባ የሞቱ ሲሆን **62,750** አባዎራዎች ተፈናቅለዋል ከዚህም ውስጥ ወንድ **184,485**፣ ሴት **192,016** ሲሆኑ በአጠቃላይ **376,502** ሰዎች በጦርነቱ ምክንያት መፈናቀላቸውን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎ ለመረዳት ችሏል፡፡

## እገታ ወይም የአፈና ተግባር

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ያለው የትጥቅ ግጭትን ተከትሎ ከደረሱ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መካከል አንዱ የእገታ ድርጊት ነው፡፡ በዚህ ድርጊት ከትጥቅ ግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች በአስገዳጅነት ተይዘው የተወሰዱ ሲሆን የብዙዎቹ ቤተሰቦች ለኢሰመጉ እንደገለጹት ታግተው የተወሰዱት የቤተሰቦቻቸው አባላት በህይወት ይኑሩ ወይም አይኑሩ ለመረዳት እንዳልቻሉ ገልጸዋል፡፡

የጄኔቫ ስምምነቶች የጋራ አንቀጽ 3 የጦር መሳሪያቸውን ያስቀመጡ የጦር ሀይል አባላትንና በህመም ፣ በመቁሰል፣ በመታሰር ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንያት ከውጊያ ውጪ የሆኑትን ሰዎች ጨምሮ በግጭቱ ተግባር ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ የሌላቸውን ሰዎች በእገታ መያዝ በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ የተከለከለ ተግባር መሆኑን ይገልጻል፡፡

ሁለተኛው የጄኔቫ ስምምነት ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2(ሰ) በጠላትነት ስራዎች ቀጥተኛ ተሳትፎ ያላደረጉ ወይም መሳተፋቸውን ያቆሙ ሰዎችን በመያዣነት ማገት በማንኛውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ የተከለከለና ተከልክሎም የሚቆይ ነው ሲል ይደነግጋል፡፡

የእገታ ድርጊት በሁሉም አይነት የትጥቅ ግጭቶች ጊዜ የተከለከለ ድርጊት መሆኑን ለመረዳት የመጀመሪያው የጄኔቫ ስምምነቶች ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 75 (2)(ሐ) ላይ የተደነገገውን መመልከት ይቻላል፡፡ ይህ ተጨማሪ ፕሮቶኮል አለማቀፋዊ ይዘት ላላቸው የትጥቅ ግጭቶች ተፈጻሚ የሚሆን ህግ ሲሆን ይህ ድርጊት በሁለቱም የትጥቅ ግጭቶች ወቅት የተከለከለ ድርጊት ስለመሆኑ ያሳያል፡፡

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ አባል ባትሆንም አለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤትን ለማቋቋም የወጣው ሰነድ (rome statute) በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2(a)(iii) እና 2(c)(iii) ላይ በሁለቱም (አለማቀፋዊ በሆነ እና አለማቀፋዊ ባልሆነ) የትጥቅ ግጭት ወቅት ሰዎችን አግቶ መውሰድ የጦር ወንጀልን እንደሚመሰርት ይገልጻል፡፡

የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ በአንቀጽ 270 ንዑስ አንቀጽ (ሰ) ላይ የማስፈራራት ወይም የማሸበር ድርጊት ያደረገ፣ በወጀ(በመያዣነት) ያገተ ወይም የጅምላ ቅጣት የጣለ ወይም የበቀል ድርጊት ያደረገ እንደሆነ ከአምስት አመት እስከ ሀያ አምስት አመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት ወይም ነገሩ በጣም ከባድ በሆነ ጊዜ በዕሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት እንደሚያስቀጣ እንዲሁም ይህ ቅጣት የጥፋት ድርጊቱን ባደራጀ፣ ትዕዛዝ በሰጠ ወይም ድርጊቱን በፈጸመ ግለሰብ ላይ እንደሚጣል ይደነግጋል፡፡

## አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

**1. ሰሜን ወሎ**

ኢሰመጉ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙ አካባቢዎች በመዘዋወር የምርራ ስራን ያከናወነ ሲሆን በዚህ የምርመራ ስራ ከተገኙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች አንዱ የእገታ ወይም የአፈና ድርጊት ነው፡፡ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን ወልዲያ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ወ/ከ/068/2014 በቀን 27/05/2014 ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ መሰረት የህወሀት ታጣቂ ቡድን አካባቢውን ተቆጣጥሮ በነበረበት ወቅት ከ145 በላይ የሚሆኑ ሰዎችን ይዞ እንደነበር እና የእነዚህ ሰዎች አድራሻ መረጃውን ኢሰመጉ እስካገኘበት ጊዜ ድረስ እንደማይታወቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

**2. ደቡብ ወሎ**

ኢሰመጉ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደቡብ ወሎ ዞን ደሴ፣ ኮምቦልቻ፣ ወረኢሉ፣ ተንታ፣ ጃማ፣ ኩታበር፣ ለጋንቦ ከተማወችና ወረዳዎች ላይ የምርመራ ስራን ያከናወነ ሲሆን ኢሰመጉ በአካባቢው ተሰማርቶ ከነበረው የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የምርመራ ቡድን ባገኘው መረጃ መሰረት በአካባቢው **8 ወንድ፣ 6 ሴት በአጠቃላይ ድምር** 14 ሰዎች መታገታቸውን ለመረዳት ችሏል፡፡

## በሸኔ ታጣቂ ቡድን የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች

**ከሚሴ፣ ጨፋሮቢት እና ሰንበቴ**

በከሚሴ፣ ጨፋሮቢትና ሰንበቴ የኦሮሚያ ዞን በመሆኑ በጊዜው ተቆጣጥሮት የነበረው ኦነግ ሸኔ የተባለው የታጣቂ ቡድን ሲሆን ከህወሀት ጋር በመተባበር የተለያዩ ባንኮች፣ የመንግስትንና የግል መስሪያ ቤቶችን ዘርፈዋል፡፡

**ከሚሴ**

በአማራ በሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን የከ□□ ከ□□ አስተዳደር ሴቶች፣ ህጻናት፣ ወጣቶች እና ሠራተኞች ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ሴ/ህ/ወ/375/2014 በቀን 12/04/2014ዓ.ም ለኢሰመጉ ሰጡት መረጃ መሰረት የተደፈሩ/ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው **6** ፤አካላዊ ድብደባ የደረሰባቸው ሴቶች ብዛት **4**፣ ተባራሪ ጥይት የመታቸው ሴቶች ብዛት **3**፣ የመድፍ ፍንጣሪ የመታቸው ሴቶች ብዛት **1** እና የተለያየ አይነት ዘረፋ የደረሰባቸው ሴቶች ብዛት **4** በአጠቃላይ **18** ሴቶች ዕድሜያቸው ከ14-35 ዓመት የሚሆናቸው ሴቶች የጥቃቱ ሰለባ መሆናቸውን ኢሰመጉ ካሰባሰባቸው መረጃዎች ማወቅ ተችሏል፡፡

የከ□□ ከ□□ አስ□□□□□ ወ□□ ፖ□□ የህ□□□ሰብ አቀፍ ወ□□□ መከላከል ዋና ስራ ሂደት በደብዳቤ ቁጥር 10/14 በቀን 12/4/2014ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጠው መረጃ የወደሙ ሆቴሎች **20** እንዲሁም የመንግስትና የግል ተቋማት ሙሉ በሙሉ መውደማቸውን 400 መኖሪያ ቤቶች መቃጠላቸውን፣3ሰዎች መሞታቸውን፣6ሰዎች የአካል ጉዳት እንደደረሰባቸው እንዲሁም 3ሴቶች ጾታዊ ጥቃት እንደደረሰባቸው ገልጿል፡፡

**ጆሌ ጥሙጋ**

የጅሌ ጥ□□ ወ□□ ፖሊስ ጽ/ቤት የወ□□ል ምርመራ ዋና የስራ ሂደት በደብዳቤ ቁጥር 35/8/2014 ቀን 13/4/2014 ዓ.ም ለኢሰመጉ በሰጡት መረጃ መሰረት የቆሰሉ ወንድ **44**፣ ሴት **7** የተገደሉ ወንድ **88**፣ሴት **6** ሲሆን የመንግስትና የግል ተቋማት ሙሉ በሙሉ መውደማቸውን እና የተለያዩ ባንኮች መዘረፋቸውን ለኢሰመጉ ገልጿል፡፡

**አርጡማ ፋርሲ**

በአብክመ ኦሮሞ ዞን አርጡማ ፋርሲ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር አስ/442/2014 በቀን 12/04/2014 ዓ.ም መረጃ ለኢሰመጉ የሰጡ ሲሆን ነገር ግን ይህ መረጃ እስከ 12/04/2014 ዓ.ም ድረስ የሰበሰቡት መረጃ ብቻ እንደሆነ ገልጸዋል በዚህም መሰረት በጦርነቱ ምክንያት የተፈናቀሉ ሰዎች **2406**፣ የሞቱ ሰዎች **16**፣ የቆሰሉ **6**፣ የወደሙ የግለሰቦች መኖሪያ ቤቶች ብዛት**79**፣ የሞቱ ከብቶች ብዛት **21** መሆናቸውን ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል፡፡

## የህግ ትንታኔ

### የወንጀሉ ምንነት

ጦርነት የሰው ልጅ አንድ የታሪክ ክፍል እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ቀደም ብለው ይደረጉ የነበሩ ጦርነቶች ምንም አይነት መመሪያ መርህ ወይም የሚገዛቸው ህግ ሳይኖር በመቅረቱ በጦርነቶች በርካታ ከጦርነቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች እንዲሁም የሲቪል ንብረቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሲደርስ ቆይቷል፡፡ አንዳንድ ተዋጊዎች ጉዳት ለደረሰባቸው፣ ለሰላማዊ ሰዎች፣ ለሰላማዊ ሰዎች ንብረቶች እንዲሁም በአጠቃላይ ከጦርነቱ ጋር ግንኙነት ለሌላቸው አካላት ርህራሄን ያሳያሉ አንዳንዶች በተቃራኒው ያገኙት ላይ ሁሉ ያለምንም ተጠያቂነት እርምጃን ሲወስዱ ይስተዋሉ ነበር፡፡

የጦር ወንጀሎች ጽንሰ ሃሳብ ጥንታዊ መሰረት ያለው ሲሆን የመጀመሪያው የጦርነት ወንጀል በ1474 በቅድስት ሮማ ግዛት በተቋቋመው ጊዜያዊ ፍ/ቤት የቀረበው ክስ ነበር። ይህም የፒተር ቮን ሀገንባች ክስ በመባል ይታወቃል። በ19ኛው መቶ ክ/ዘመን አለም ለሰብዓዊ መብቶች በሰጠው ትኩረት እና የጦርነትን አስከፊ ውጤት ለመቀነስ በነበረው አላማ ምክንያት የጦር ወንጀሎች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ህጎች ከፍተኛ የሆነ እድገት አሳይተዋል። በተለይም የ1949ኙ የጄኔቭ ስምምነት እና አለም አቀፉ የወንጀለኛ መቅጫ ህጎች ተጠቃሽ ናቸው።

የጦር ወንጀሎች በሚል የሚገለጹት ድርጊቶች አግባብነት ባላቸው ዓለም አቀፍ የጦርነት ሕጎች መሠረት ‹ጦርነት ወይም የትጥቅ ግጭት› (Armed conflict) መሆኑ ብያኔ በተሰጠበት ሁኔታ ውስጥ በሚገኙ ተዋጊዎች ላይም ሆነ ባልታጠቁ ሰላማዊ ሰዎች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ናቸው። በመሆኑም የተፈጸሙት ድርጊቶች የጦር ወንጀሎች ናቸው አልያም አይደሉም የሚያስብለው በአለም አቀፍ ህጎች መሰረት በጦርነት ወይም በትጥቅ ግጭት ሁኔታ ውስጥ የተፈጸመ ድርጊት መሆኑ ነው።

**የወንጀሉ አላባዊያን**

1. ወንጀሉ የተፈጸመበት ነባራዊ ሁኔታ

የጦር ወንጀሎች በአለም አቀፍ ህግ መሰረት የግለሰብ የወንጀል ሃላፊነት የሚያስከትሉ የአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ (ስምምነት ወይም ልማዳዊ ህግ) ጥሰቶች ቢሆኑም ድርጊቱ የተፈጸመበት ነባራዊ ሁኔታ ከዓለም አቀፍ ወይም ዓለም አቀፍ ካልሆነ የትጥቅ ግጭቶች ጋር ተያይዞ መሆን አለበት።

2. ከተጎጂዎቹ ማንነት አንጻር <<…በተጠበቁ ሰዎች ወይም ንብረቶች ላይ….>>

ከዘር ማጥፋት እና በሰብአዊነት ላይ ከሚፈጸሙ ወንጀሎች በተቃራኒ የጦር ወንጀሎች በተለያዩ ተጎጂዎች፣በተፋላሚዎችም ይሁን ተዋጊ ባልሆኑ ላይ እንደየወንጀሉ አይነት ሊፈጸሙ ይችላሉ። በአለም አቀፍ የትጥቅ ግጭቶች ወቅት ተጎጂዎች የቆሰሉ እና የታመሙ የጦር ሃይሎች፣ የጦር እስረኞች እና የሲቪል ሰዎች ይገኙበታል። ዓለም አቀፋዊ ባልሆኑ የትጥቅ ግጭቶች ወቅት ደግሞ የጦር ኃይሎች አባላት ሆነው በአካል ጉዳት፣ በህመም፣ በመቁሰል፣ በእስር ወይም በ"hors de combat" በመሆን መሳሪያቸውን ያስቀመጡትን ጨምሮ ሌላ በማንኛውም ምክንያት የሲቪል ሰዎችን ጨምሮ በጦርነቱ ውስጥ ተሳታፊ ያልሆኑት ሰዎች ይይዛል። በሁለቱም የግጭት አይነቶች ለህክምና እና ለሀይማኖት ሰራተኞች፣ ለሰብአዊ ሰራተኞች እና በመከላከያ ውስጥ ሆነው ሲቪል ሰራተኞች የሆኑትንም ያጠቃልላል። በተጨማሪም የሲቪል ንብረቶች እና ጥበቃ በተደረገላቸው ንብረቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችንም እንዲሁ አካቶ ይዟል፡፡ በመሆኑም በእነዚህ አካላት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች የጦር ወንጀሎች ሊሆኑ ይችላሉ።

3. <<…… ሆን ብሎ…..>>

የዓለም አቀፍ ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንደሚያሳየው የጦር ወንጀሎች ሆን ተብሎ የሚፈጸሙ ጥሰቶች መሆናቸውን ነው። ይህም ድርጊቱ የሚያስከትለውን ወይም ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት ያውቃል ወይም ሊያውቅ ይገባል፣ እንዲሁም ድርጊቱ ተጎጂው ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት እያሰቡ ወይም ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ባለማሰብ በቸልተኝነት መፈጸም የሚሉትን ይይዛል፡፡ ሆኖም ግን እንደተፈጸመው የወንጀል አይነት ሞራላዊ ተጠያቂነቱ ሊለያይ ይችላል።

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የተደረገው የትጥቅ ግጭት አለማቀፋዊ ያልሆነ የትጠቅ ግጭት መሆኑን በዚህ ልዩ መግለጫ "የግጭቱ ምንነት" በሚል አርዕስ በስፋት የተሸፈነ ሲሆን በዚህ የትጥቅ ግጭት ወቅት በርካታ አይነት የህግ ማዕቀፎች ማለትም የሰብዓዊ መብቶች ህግጋቶች፣ የሰብዓዊነት ህግ፣ የልማድ አለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ እና ሌሎችም ሀገር አቀፍ ህግጋቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ ደረጃ ዋና ከሚባሉት ከዘጠኙ የሰብዓዊ መብቶች ህግጋቶች መካከል ሰባቱን ተቀብላ ያጸደቀች ሲሆን በአህጉር አቀፍ ደረጃ አምስት የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችን ተቀብላ አጽድቃለች፡፡ በእነዚህ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች ላይ የተቀመጡ በርካታ መብቶች ያሉ ሲሆን እነዚህንም መብቶች የማክበር፣ የማስከበር እና የማሟላት ሀላፊነትን በመንግስት ላይ ይጥላሉ፡፡

በተጨማሪም በልማድ ገዢ የሆኑ አለም አቀፍ ህግጋቶች ያሉ ሲሆን እነዚህ የልማድ ዓለም አቀፍ ህጎች አንድ ሀገር ፈርማ ተቀብላ ብታጸድቃቸውም ባታጸድቃቸውም በሀገሪቱ ላይ ገዢ የሆኑ የህግ አይነቶች ናቸው፡፡ በትጥቅ ግጭት ወቅት በርካታ የሰብዓዊነት ህግጋቶች የልማድ አለማቀፍ ህግ ደረጃን በማግኘታቸው በሁሉም ሀገሮች ላይ እና ታጣቂ ቡድኖች ላይ ገዢ ይሆናሉ፡፡

የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት በምዕራፍ ሶሰት ላይ በርካታ የሰብዓዊ መብቶችን የዘረዘረ ሲሆን የተቀመጡት ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ ሰነዶች መርሆች ጋር በተጣጣመ መንገድ እንደሚተረጎሙ ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም የህገ-መንግስቱ አንቀጽ 9 ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ህግ አካል መሆናቸውን ደንግጓል፡፡

የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ሌላው በዚህ ልዩ መግለጫ ላይ የሚካተት ህግ ሲሆን ይህ ህግ የጦር ወንጀሎችን አካቶ የያዘ ሲሆን ተያያዥ ቅጣቶችንም እንዲሁ አካቶ ይዟል፡፡

የጦር ወንጀል የምንለው የወንጀል አይነት የጄኔቫ ስምምነቶችን እንዲሁም አለም አቀፍ የሆኑ የልማድ የሰብዓዊነት ህጎችን በመጣስ የሚፈጸም የወንጀል አይነት ሲሆን ይህም የወንጀል አይነት አለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤትን ለማቋቋም የወጣው ሰነድ (rome statute) አንቀጽ 8 ላይ የጦር ወንጀል ማለት በጄኔቫ ኮንቬንሽን ላይ የሚፈጸም ከፍተኛ የሆነ ጥሰት አንዲሁም ሌሎች ዓለም አቀፍ የሆኑ የትጥቅ ግጭት ህጎች እና ልማዶች ላይ የሚፈጸም ከፍተኛ የሆነ ጥሰት መሆኑን ይደነግጋል፡፡

በተጨማሪም ይኸው ሰነድ አለም አቀፍ ይዘት በሌለው የትጥቅ ግጭት ውስጥ የሚፈጸም የጦር ወንጀል የጄኔቫ ኮንቬንሽኖች የጋራ አንቀጽ 3 ላይ የሚፈጸም ከፍተኛ የሆነ ጥሰት መሆኑን እንዲሁም ጥሰቶች ምን ምን እንደሆኑም ጨምሮ ዘርዝሮ ይዟል፡፡ ከነዚህም ጥሰቶች መካከል ጥበቃ በተደረገላቸው ሰዎች ወይም ንብረቶች ላይ የሚፈጸም ግድያ፣ ጾታዊ ጥቃት፣ ማሰቃየት ወይም ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ፣ በሰውነት ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ማድረስ፣ ከአስፈላጊነት መርህ ውጪ የሚፈጸም ከፍተኛ የሆነ የንብረት ውድመት፣ ሆን ተብሎ በሲቪል ሰዎች እና ሲቪል ንብረቶች ላይ የሚሰነዘር ጥቃት፣ በምንም አይነት መልኩ መኖሪያ መንደሮችን፣ ቤቶችን እና ህንጻዎችን ማጥቃት ወይም ማጋየት እንዲሁም ሌሎች በርካታ ጥሰቶችን አካትቶ ይዟል፡፡

ከዚህ ሰነድ (rome statute) ልንረዳ የምንችለው የጦር ወንጀል አለም አቀፍ ወንጀሎች ተብለው ከሚጠቀሱት የዘር ማጥፋት ወንጀል፣ በሰብዕና ላይ የሚፈጸም ወንጀል እና ጥቃት የመፈጸም ወንጀል መካከል አንዱ ሲሆን ይህ የወንጀል አይነት በሁለቱም አይነት የትጥቅ ግጭቶች ማለትም ዓለም አቀፋዊ ይዘት ባላቸው የትጥቅ ግጭቶች እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ይዘት በሌላቸው የትጥቅ ግጭቶች ወቅት የሚፈጸም ወንጀል መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡

የልማድ አለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ ሌላው የህግ ማእቀፍ ሲሆን ይህ ህግ በሁሉም አገራት ላይ እንዲሁም ታጣቂ ቡድኖች ላይ ገዢነት ስልጣን ያለው ነው፡፡ በዚህ የህግ ማእቀፍ ሁለቱም አይነት የትጥቅ ግጭቶች የተሸፈኑ ሲሆን የጦር ወንጀልም በዚሁ የህግ ማእቀፍ ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ኢትዮጵያ የአለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤትን ለማቋቋም የወጣው ሰነድ (rome statute) ፈራሚ አገር ባትሆንም ይህ የልማድ አለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ ግን በሁሉም አገሮች እና ታጣቂ ቡድኖች ላይ ገዢ ስለሆነ በኢትዮጵያም ላይ እንዲሁም በህወኃት ታጣቂ ቡድን ላይ ገዢና ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

በዚህ የልማድ አለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ ደንብ ቁጥር 156 ላይ ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊነት ህግ ጥሰት የጦር ወንጀልን ይመሰርታል ሲል ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም መንግስታት ይህንን የልማድ ዓለም አቀፋዊ የሰብዓዊነት ህግ የመሰረቱ ለሁለቱም ዓለም አቀፋዊ ለሆኑ እና ዓለም አቀፋዊ ላልሆኑ የትጥቅ ግጭቶች ተፈጻሚ እንዲሆን ከማድረግ እሳቤ መሆኑን ይገልጻል፡፡ በዚህ የልማድ ህግ ላይ የጦር ወንጀልን ለመመስረት ከፍተኛ የሚለው ሀሳብን ከግምት ውስጥ ወይም እንደ አንድ መመዘኛ የማይወስድ ልማድ መኖሩን

ይገልጻል፡፡ ይህም ማለት በሰብአዊነት ህጎች ላይ ጥሰት መፈጸሙ ብቻ የጦር ወንጀልን ለመመስረት አንዳንዴ እንደ በቂ ሁኔታ ሊወሰድ ይችላል ማለት ነው፡፡

የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ በርዕስ ሁለት ስር ዓለም አቀፍ ህጎችን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በሚል ርዕስ ከአንቀጽ 270 ጀምሮ የጦርነት ወንጀሎችን ዘርዝሮ ይዟል፡፡ በአንቀጽ 270 ላይ በሰላማዊ ህዝብ ላይ የሚፈጸም የጦርነት ወንጀል የተካተተ ሲሆን እንደ አለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ፣ አለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤትን ለማቋቋም የወጣው ሰነድ እና እንደ የልማድ አለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ ተመሳሳይ ጥሰቶችን አካቶ ይዟል፡፡

ይህ አንቀጽ አለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግን በመጣስ የሚፈጸም ግድያ፣ ማሰቃየት፣ ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ፣ በአካል፣ በአእምሮ እና በጤንነት ላይ ከባድ ስቃይ ወይም ጉዳት ማድረስ፣ ህዝብን በሀይል ከስፍራው ማፈናቀል፣ የዝሙት አዳሪነት፣ የብልግና ድርጊት ወይም የግብረ ስጋ ድፍረት መፈጸም፣ ንብረት መውረስ፣ ማውደም፣ ወይም ለራስ ማድረግ፣ ምግብና ለምግብ ማምረቻ የሚውል የእርሻ ቦታዎችን ሰብልን፣ የቤት እንስሳትን የመጠጥ ውሀ አገልግሎቶችን የመስኖ ስራዎችን የጤና ተቋማትን ወይም ትምህርት ቤቶችን መውረስ፣ ማፍረስ፣ ማጥፋት፣ ከትቅም ውጪ ማድረግ፣ የማምለኪያ ቦታዎችን ማውደም ከአምስት አመት እስከ ሀያ አምስት አመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት ወይም ነገሩ በጣም ከባድ በሆነ ጊዜ በዕሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት እንደሚያስቀጣ እንዲሁም ይህ ቅጣት የጥፋት ድርጊቱን ባደራጀ፣ ትዕዛዝ በሰጠ ወይም ድርጊቱን በፈጸመ ግለሰብ ላይ እንደሚጣል ይደነግጋል፡፡

የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ከዚህ በተጨማሪ በአንቀጽ 273 ላይ ማንም ሰው በጦርነት ጊዜ የሚደረግ ገፈፋ ለወታደራዊ አገልግሎት አስፈላጊ ነው በሚል ሰበብ የባህር ወንበዴነትን፣ የዘረፋን፣ የገፋፊነትን ወይም ህገ ወጥ የሆነ የንብረት ማፍረስን ወይም የመውሰድን ተግባር ያዘጋጀ፣ እንዲዘጋጅ ያዘዘ ወይም ይህንኑ ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ ከአምስት አመት እስከ ሀያ አምስት አመት ሊደርስ በሚችል ጽነ እስራት ወይም ነገሩ በጣም ከባድ በሆነ ጊዜ በዕሜ ልክ ጽነ እስራት ወይም በሞት እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል፡፡

የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሰፋ ያሉ የጦርነት ወንጀሎችን ከአንቀጽ 269-283 በዝርዝር የያዘ ሲሆን ይህ ህግ ከወንጀል ድርጊቱ ጎን ለጎን ድርጊቱን በፈጸሙ አካላት ላይ የሚወሰዱ ቅጣቶችን በዝርዝር አካቶ ይዟል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትን ህጎች እንዲሁም በምርመራ ስራው የተገኙ ግኝቶችን በጋራ በመመልከት በሰሜኑ ኢትዮጵያ ክፍል የነበረው የትጥቅ ግጭት በርካታ ሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ያስከተለ አለም አቀፋዊ ያልሆነ የትጥቅ ግጭት መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡ እንዲሁም ይህ የትጥቅ ግጭት ከላይ በተጠቀሱት ህጎች መሰረት እና ከተዘረዘሩት የምርመራ ግኝቶች የጋራ ንባብ ለመረዳት የሚቻለው የጦር ወንጀል አላባውያን የምንላቸውን የትጥቅ ግጭቱ እውቅና ከተሰጣቸው የትጥቅ ግጭቶች ማለትም አለም አቀፋዊ የትጥቅ ግጭት ወይም አለም አቀፋዊ ያልሆነ የትጥቅ ግጭት መሆኑ፣ ጥቃት የተፈጸመባቸው አካላት እና ንብረቶች ምንነት(ሲቪል ሰዎች፣ ጥበቃ የሚደረግላቸው ሰዎች፣ ሲቪል ንብረቶች እና ጥበቃ የሚደረግላቸው ንብረቶች)፣ እንዲሁም ሊደርስ የሚችለው ጉዳት እየታወቀ የተፈጸመ መሆኑ ወንጀሉን ለመመስረት አስፈላጊ የሆኑትን መስፈርቶች መሟላቱን ምክንያታዊ አመኔታን (reason to believe) የሚፈጥር ነው፡፡

ስለሆነም በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የተካሄደው የትጥቅ ግጭትን ተከትሎ በዚህ ልዩ መግለጫ ላይ በምርመራ ስራ የተካተቱ በርካታ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግጋቶች፣ በዓለም አቀፍ የልማድ የሰብዓዊነት ህግጋቶች፣ ዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤትን ለማቋቋም በወጣው ሰነድ እና በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ መሰረት የጦር ወንጀል የምንለውን የወንጀል አይነት መፈጸሙን ለማመን ምክንያት (reason to believe) የሚሆኑ ማስረጃዎች በመገኘታቸው ይህ ወንጀል ለመፈጸሙ አሳማኝ ምክንያቶች ናቸው፡፡

## መደምደሚያ

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ በሰሜኑ የኢትዮያ የሀገሪቱ ክፍል ተካሂዶ የነበረውን የትጥቅ ግጭት አስመልክቶ በትጥቅ ግጭቱ የተካለሉ በአማራ እና በአፋር ክልል ውስጥ የሚገኙ አካባቢዎች ላይ በመዘዋወር ሰፋ ያለ የምርመራ ስራን አከናውኗል፡፡ በዚህም መሰረት በትጥቅ ግጭቱ ምክንያት ከግጭቱ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ወይም ተሳትፎ የሌላቸው አካላት እና ንብረቶች ላይ ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መፈጸሙን ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

በዚህ የትጥቅ ግጭት ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ የትጥቅ ግጭት ህጎችን በመጣስ በርካታ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የተፈጸሙ ሲሆን እነዚህም ጥሰቶች በግጭቱ ተሳትፎ በሌላቸው ሰዎች፣ ጥበቃ በሚደረግላቸው ሰዎች፣ በሰላማዊ ሰዎች ንብረቶች እና ጥበቃ በሚደረግላቸው ንብረቶች ላይ በመፈጸማቸው እንዲሁም የትጥቅ ግጭት ህግጋቶችን በመጣስ የተፈጸሙ በመሆናቸው የጦር ወንጀልን ለመመስረት ያስችላሉ፡፡

እነዚህ ወንጀሎች በአንዳንድ አካባቢዎች በህወኃት ታጣቂ ቡድን፣ በአንዳንድ አካባቢዎች በሸኔ ታጣቂ ቡድን፣ በአንዳንድ አካባቢዎች በሁለቱ ቡድኖች በጥምረት በተፈጸሙ ጥቃቶች፣ በአንዳንድ አካባቢዎች በመንግስት ታጣቂ ቡድኖች፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ከማን እንደሆነ ባልታወቁ ጥቃቶች መፈጸማቸውን ኢሰመጉ ለመረዳት ችሏል፡፡ ስለሆነም የዚህ ወንጀል ተጠያቂነት በሁሉም አካላት ላይ መውደቁን መረዳት ይቻላል፡፡

መንግስት በአገሪቱ ግዛት ውስጥ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን መርምሮ ህጋዊ ተጠያቂነትን የመመስረት ሃላፊነት እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ስለሆነም በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በነበረው የትጥቅ ግጭት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግጋቶች፣ አለም አቀፍ የልማድ የሰብአዊነት መብቶች ህግጋቶች እና የኢትዮጵያ የወንጀል ህግን በመጣስ በሁሉም የትጥቅ ግጭቱ ተሳታፊ አካላት አባላት የተፈጸመውን የጦርነት ወንጀል በማጣራት የወንጀል ተጠያቂነትን የመመስረት ሀላፊነት አለበት፡፡

## ምክረ ሐሳብ

- በመንግስትና በህወኃት ታጣቂ ቡድን መካከል በነበረው የትጥቅ ግጭት ሰላማዊ ሰዎች ህይወታቸውን አጥተዋል ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፤ ንብረታቸው ወድሟል ስለሆነም መንግስት ለተፈናቀሉ ሰዎች ዘላቂ የሆነ መፍትሄን እንዲያበጅ እና ወደነበሩበት የኑሮ ሁኔታ መልሶ የማቋቋም ስራ እንዲያከናውን፣
- በትጥቅ ግጭቱ ተሳታፊ የሆኑ ሁሉም አካላት ችግሮችን በመፍታት ድጋሚ ይህ የትጥቅ ግጭት እንዳይከሰት ኃላፊነታቸውን በመወጣት የዜጎችን ደህንነት እንዲያስከብሩ፣
- መንግስት በመላ ሀገሪቱ ለግጭቶች መነሻ የሆኑ ምክንያቶችን በማጥናት እንዳይከሰቱ ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርግ፣ ግጭት ሲከሰት ሰላማዊ ዜጎች ላይ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ቅድመ መከላከል ስራን እንዲሰራ፤
- የተለያዩ የሙብት ጥሰቶችን በፈጸሙ አካላት ላይ ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ ዜጎቹን ከስቃይና ከእንግልት የመታደግ ኃላፊነቱን እንዲወጣ፣
- በትጥቅ ግጭቱ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ፣ ንብረት ለወደመባቸው፣ ህገወጥ ግድያ እና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ተጎጂዎችና ቤተሰቦች ተገቢው ካሣ እንዲከፈል፣
- መንግስት የጦርነቱን የስርጭት ባህሪ በመረዳት ተመሳሳይ አይነት ጥቃት በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች እንዳይከሰት መንግስት በቂ ጥንቃቄና ዝግጅት እንዲያደርግ፣
- መንግስት ሰብዓዊ መብቶችን አስመልክቶ ከሚሰሩ ተቋማት ጋር የመተበበር እና አብሮ የመስራት ሀላፊነት እንዳለበት በመረዳት እንደ ኢሰመጉ ያሉ በሰብዓዊ መብቶች ላይ የሚሰሩ ተቋማት መረጃን አስመልክቶ እንዲሁም የምርመራ ስራን ለማከናወን ለሚያቀርቡት ጥያቄ ፈጣን ምላሽ እንዲሰጥ፣
- የትጥቅ ግጭቱን አስመልክቶ የሚደረገው የሰላም ድርድር ሰላማዊና ዘላቂ መፍትሄን እንዲያመጣ ሁሉም ተደራዳሪ አካላት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ እና በሀገር ውስጥም ከሀገር ውጪም ያሉ ሁሉ ይህ የሰላም ድርድር ውጤታማ እንዲሆን ግጭትን ከሚያባብሱ ድርጊቶች እንዲቆጠቡ፣
- የትጥቅ ግጭቱን ተከትሎ በትግራይ፣ በአማራ እና በአፋር ክልል ተቋርጠው የሚገኙ እንደ መብራት፣ ውሀ፣ ትራንስፖርት፣ ባንክ እንዲሁም ሌሎች መሰረተ ልማቶች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲመለሱ እና ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን፣
- የትግራይ ክልልን እያስተዳደረ ያለው ህወኃት በክልሉ የትጥቅ ግጭቱን ተከትሎ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንደ ኢሰመጉ ያሉ ገለልተኛ በሆኑ አካላት እንዲጣሩ ነገሮችን እንዲያመቻች፣
- የትጥቅ ግጭቱን ተከትሎ ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሰዎች በቂ የሆነ ህክምና (የስነ-ልቦና ምክርን ጨምሮ) እንዲሰጥ፣
- የትጥቅ ግጭቱን ተከትሎ በአማራ፣ በአፋር እና በትግራይ ክልል ጉዳት ለደረሰባቸው እንዲሁም ለተፈናቀሉ ሰዎች በመንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ዓለም አቀፍ፣ አህጉር አቅፍ እና ሀገር አቀፍ ረጂ ድርጅቶች የሚሰጡ እርዳታዎች ፍትሀዊ በሆነ መንገድ የእኩልነትን መርህ ተከትሎ ያል አድሎ እንዲከፋፈሉ፣
- የትጥቅ ግጭቱን ተከትሎ በትግራይ፣ በአፋር እና በአማራ ክልል ጉዳት የደረሰባቸው የግል እንዲሁም የመንግስት ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ሆስፒታሎች፣ ፋብሪካዎች እና ሌሎችም መሰረተ ልማቶችን መንግስት እንዲያድስ

እና ዓለም አቀፍ፣ አህጉር አቅፍ እና ሀገር አቀፍ ረጂ ድርጅቶች ከመንግስት ጎን በመቆም እነዚህ መሰረተ ልማቶች ታድሰው ወደነበሩበት እንዲመለሱ የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያደርጉ፣

- የሀይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ አባገዳዎች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች እና ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ለትጥቅ ግጭቱ ዘላቂ መፍትሄን እንዲያፈላልጉ እና ሰላምን በማረጋገጥ ስራው ላይ ምትክ የሌለውን ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል።

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት

  ፖ.ሳ.ቁጥር ፡- 80001፣ ኢ-ሜል፡- national.parliament@telecom.net.et

  ፋክስ ፡- (+251) 011 155-0400፣የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 124-1000፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-

  ፖ.ሳ.ቁጥር ፡- 20122/1000፣ ኢ-ሜል ፡- kumashih@gmail.com

  ፋክስ ፡- (+251) 011 124-1208/011 124-2308፣

  የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 122-3322፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፐሬዝዳንት ጽ/ቤት:-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 23698፣ ፋክስ ፡- (+251) 011 551- 8656፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-8186፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት :-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡-1031፣ ፋክስ፡- (+251) 011 122-6292፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 124-1155፣

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር

  ስልክ ቁጥር +251 115541868 ፋክስ +25115517775

  ኢሜይል MOJMO@ETHIONET.ET

  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሰላም ሚኒስቴር

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 5608፣ ኢ-ሜል፡- mofatr1@yahoo.com

  ፋክስ፡-(+251)011 551-1200፣ የስልክ ቁጥር፡-(+251) 011 515-3204፣

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 2459፣ ኢ-ሜል፡ ombudsmaneth@ethionet.et

ፋክስ፡- (+251) 011 553-2073፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 543-336፣

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን:

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1165፣ ኢ-ሜ፡ hrcom@ethionet.et፣

ፋክስ፡ (+251) 011 550-4125፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 550-4031፣

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀነራል ጽ/ቤት:

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 199፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-2744፣

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለሱማሌ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔጽ/ቤት:

ፖ.ሳ.ቁጥር 392፣ ፋክስ፡- (+251) 25 775-3429፣

የስልክ ቁጥር፡ (+251) 257 75 34 29

ጅግጅጋ፣ ኢትዮጵያ

- ለሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 588 ፋክስ፡- (+251) 025 775-2325፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 775-4038 / 025 775-3241 ጂግጂጋ፣ ኢትዮጵያ

- ለኦሮሚያ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769፣ ኢ-ሜል፡- oromiawiev@ethionet.et

ፋክስ፡- (+251) 011 551-3642 / (+251) 011 551-9633፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 552-4247፣

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769 ፋክስ፡- (+251) 011 552-4247

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 555-0455

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1324፣ ፋክስ፡- (+251) 058 220-2511፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-2659

ባሕርዳር፣ ኢትዮጵያ

- ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 312 ፋክስ፡- (+251) 058 220-1068፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-0924 / 058 220-0499

ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ

- ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

ፖ.ሳ.ቁጥር፡-

የስልክ ቁጥር፡-

ቦንጋ፣ ኢትዮጵያ

- ለሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዘዳነት ጽ/ቤት

ኢ-ሜይል አድራሻ፡-sidaamapoffice@gmail.com

የስልክ ቁጥር፡-

ሀዋሳ፣ ኢትዮጵያ

- ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1546፣ ፋክስ፡- (+251) 046 220-2408፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 046 221-4778/ 046 220-5848፣ ሐዋሳ፣ ኢትዮጵያ

- ለደ/ብ/ብ/ህ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 18 ፋክስ፡- (+251) 046 220-1641፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 046 220-9166

ሃዋሳ፣ ኢትዮጵያ

- ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 44፣ ፋክስ፡- (+251) 057 775-0814፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 055 7775-0109፣

አሶሳ፣ ኢትዮጵያ

- ለትግራይ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 291፣

ፋክስ፡- (+251) 034 441-6564፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 034 441-6563፣

መቀሌ፣ ኢትዮጵያ

- ለጋምቤላ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 25፣ ፋክስ:- (+251) 046 220-2408፣

ጋምቤላ፣ ጋምቤላ

- ለጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 025

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 047 551-154

ጋምቤላ፣ ኢትዮጵያ

- ለሐረሪ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 952 ፋክስ፡- (+251) 025 666-2530፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 666-1723 / 025 666-1746

ሐረር፣ ኢትዮጵያ

- ለሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 272 ፋክስ፡- (+251) 025 666-0666፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 666-1799

  ሐረር፣ ኢትዮጵያ

- ለአፋር ክልል ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት

  ስልክ ቁጥር (+251) 0336660056

  ሰመራ ኢትዮጵያ

- ለድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት

  የስልክ ቁጥር፡ (+251) 025 11 11 358

  ፋክስ፡ (+251) 025 11 19 805

- ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት

  ስልክ ቁጥር (+251) 0118591363